## ስድስተኛው ቃል ኪዳን፡
## ኪዳነ ዳዊት።

ስድስተኛው ቃል ኪዳን፡ እግዚአብሔር፡ ከዳዊት ጋር ያደረገው ሲኾን፡ እርሱም፡ በመለኮታዊው የዘውድ ዙፋን ምልክትነት የሚታወቀው ነው። ከትውልዱ ሐረግ ለሚወለደው ዘሩ፡ የዘለዓለማዊት መንግሥቱን ዘውድ የሚያቀዳጀው መኾኑን፡ እግዚአብሔር፡ በዚህ ቃል ኪዳን አማካይነት፡ ለዳዊት፡ መሐላውን አጽንቶለታል። ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞንና ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ የትውልድ ሐረግ በመገኘቷ፡ የዳዊት ዘር ከኾነችው ከድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ፡ ይህ ቃል ኪዳን ደርሶ የተፈጸመበት ፍሬ፡ እርሱ መኾኑ ተረጋግጦ፡ የዳዊት ልጅ ተብሎ ተጠርቷል።

### *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ማነው?*

ከዕብራውያን ታላላቅ አባቶች መካከል አንዱ የኾነው፡ የአብርሃም የልጅ ልጅና የይስሐቅ ልጅ የኾነው ያዕቆብ፡ ልጆቹን በባረከበት ጊዜ፡ ስለእያንዳንዳቸው ባሰማው የትንቢት ቃል ውስጥ፡ ይሁዳን፡ *"የአሕዛብ መታዘዝ፡ ለእርሱ የሚኾነው ገዢ* (ኢየሱስ ክርስቶስ) *እስኪመጣ ድረስ"*፡ በትረ መንግሥትን ወይም የገዢውን ዘንግ ይዞ የሚቀይ አንበሳን አስመስሎ፡ ተናግሮለታል። የዚህ ትንቢታዊ ጥቅስ ባለቤት ማንነት ሲፈለግና ሲጠበቅ ከቆየ በኋላ፡ እነሆ፡ በራእየ ዮሐንስ መጽሐፍ፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ሥርወ ለዳዊት"* ማለትም፡ *"ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፥ እርሱም የዳዊት ሥር፥ ድል ነሥቶአል"* ተብሎ በተነገረለት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደርሶ የተፈጸመ መኾኑ ተረጋግጦ ታወቀ፤ ተረዳ።

ኢትዮጵያውያን፡ ሕገ መንግሥታቸውን፥ ብሔራዊ መሪያቸውንና የአስተዳደር ሥርዓታቸውን በሚመለከት፡ ያደረጉት ዘለዓለማዊ ምርጫቸው ምን እንደኾነ፡ በአገር ደረጃ ሳይቀር፡ በቀጠለው መለኮታዊ ትውፊታቸው አማካይነት፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ ደጋግመው፡ በይፋ ገልጸዋል። በብሉያቱ ኪዳናት ላይ የተመሠረተውን አዲሱን ኪዳን፡ በጋለ መንፈሳዊ ስሜት መቀበላቸውና እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በልባቸው የጻፈው ሕጉ፡ ሕገ መንግሥታቸው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም ንግሥትነት፡ የምትመራው የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ፡ መንግሥታቸው መኾኑን፡ በፍጹም እምነት አውቀው መከተላቸው፡ የዚህ እውነታ ግዙፍ ማስረጃዎች ናቸው። ብሔራዊ መፈክራቸውና ምልክታቸው አድርገው የሚገለገሉበት፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው የእግዚአብሔር ቃልና ይህንኑ፡ ወደሥዕል በመተርጐም፡ ዘውድ ጭኖ፡ በትእምርተ መስቀል በተከለለ መጸር ላይ የሚውለበለብ፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የተሸከመው አንበሳ፡ ኹለቱም፡ ለዚሁ እውነታ፡ ሌሎቹ፡ ተጨባጭና ጠንካራ ማረጋገጫዎች ናቸው።

ይኸው፡ የአንበሳ ፍካሬና ምስል፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተሰጠ፡ የእርሱ ብቸኛ ሀብቱ ነው! ለሌላ ለማንም ሊኾን አይችልም፤ ሊኾንም አይገባም። ይህም፡ የአዲሱ ኪዳን መታወቂያ ዓርማ፡ በማዕከሉ ላይ ሠፍሮ የሚገኝበት፡ የብሉዩ ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ፡ የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ምልክትና ማኅተም ኾነ!

ኢትዮጵያውያን፡ ከሰሎሞን ለሚበልጠው፡ ለእርሱ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፍጹም እውቅናን ያለመዘግየት ሰጥተውና እንዴት፡ ዝግጁዎች ኾነው፡ ያላንዳች ውልውል እንደሚያምኑበት ለማሳየት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቦ የሚነበበው፡ ሕንደኬ የተባለችው፡ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሃይማኖታዊ አቋምና "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" የተባለው የበኸሮንዲ ፈጣን ሃይማኖታዊ ምግባር፡ የአዲስ ምዕራፍ መክፈቻ ኾኖ፡ በማስረጃነት ሲጠቀስ ይኖራል። የድንግል ማርያም ልጅ፡ ኢየሱስ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥ መሢሕና ዘለዓለማዊው ሊቀ ካህናት ብቻ ሳይኾን፡ ንጉሠ ነገሥትም ነው።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት።

በምድር ላይ፡ በሥጋ የሚዛመደው ወገኑ ካልኾነ በቀር፡ ማንኛውንም ባዕድ፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ በራሱ ፈቃድና ነጻ ምርጫ ተቀብሎና እውቅና ሰጥቶ፡ በላዩ እንዲነግሥ የሚፈቅድ አንድም ሕዝብ ባለመኖሩ፡ ኢትዮጵያውያንም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ንጉሣቸው መኾኑን ያረጋገጡበት፡ ይህ፡ በይፋ ያወጁት፡ ሃይማኖታዊ አቋማቸው፡ የእርሱን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት፡ ማለት፡ በሥጋ ትውልዱ፡ ኢትዮጵያዊ የመኾኑን ምሥጢር አጉልተው ከሚያሳዩት ማስረጃዎች መካከል፤ አንዱ ኾኖ ይቀርባል።

ከዚህ ጋር፡ የአይሁድ አለቆች፡ *"ከአንተ፡ ምልክት ልናይ እንሻለን"* የሚል፡ ተንኰል የተመላበትን የምርምር ጥያቄ ባቀረቡለት ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ንግሥተ ዓዜብ፡ [ኢትዮጵያ] በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ!"* ሲል የመለሰላቸው፡ ትንቢታዊ የተግሣፅ ቃል፡ መድረስና መፈጸም የሚጀምርበት ዘመን፡[፳፭] እነሆ፡ በዚያ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ሃይማኖታዊ ምግባር ተከፈተ።

ኢትዮጵያውያን፡ ስለእግዚአብሔር፥ በመጨረሻም፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው፡ ዕፁብ ድንቅ የኾነው አስተሳሰብ፡ አይሁድ፡ በዚሁ ረገድ ካላቸው አስተሳሰብ፡ ፍጹም የተለየና ተቃራኒው መኾኑ ተረጋግጧል። ይኸውም፡ አይሁድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸው ጥላቻና ተቃውሞ፡ ከመጨረሻው ምልዓት ደርሶ፡ አሰቅለው የገደሉት፡ "ራሱን፡ የእግዚአብሔር ልጅና መለኮታዊው ንጉሥ አድርጎ፡ በገሃድ አሳውቋል" በሚል ክስ ብቻ ሳይኾን፡ በኢትዮጵያዊ ማንነቱ ላይ ባላቸው መራራ ስሜት ጭምር በመኾኑ ነው። *"ልትገድሉኝ ስለምን ትፈልጋላችሁ? ...ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ፡ በመልክ አትፍረዱ!"* ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገራቸው ቃላት፡ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ[፳፯] የነበረው፡ በይበልጥ፡ ከዚሁ ከመልኩ የተነሣ መኾኑን ያረጋግጣል።

በዚህ መልኩ ሲታይ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉ መከራ፡ ቁጥሩ ብዙ የኾነውን፡ የአይሁድን የከፋት ምንጭነትና የባሕርያቸውን ጨካኝነት ለማጋለጥ፡ በመድረክነት አገልግሏል። ከእነዚህ የከፋት አሳቦች መካከል፡ ኹለቱ፡ እዚህ ላይ ተጠቀሰዋል።

እነርሱም፡ ጊዜውን ጠብቆ የሚራመደውን፡ መለኮታዊዉን ፈቃድና ዕቅድ በመቃረን፡ ባልተቋረጠ ይዞታ እየተካኼደ የቆየውን፡ የአይሁድን የዘር ዓመፀኛነት፡ በበለጠ ያባባሱ ነበሩ።

የመጀመሪያው የክፋት አሳባቸው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ኾኖ በቅድሚያ በተገለጠው፡ በሙሴ ላይ፡ አይሁድ፡ አድሮባቸው የነበረው፡ ጠንቀኛ የኾነው ንቀታቸውና ጥላቻቸው ነው። ይህም፡ በኢትዮጵያዊነት ህልውናው ምክንያት የተፈጠረው ነበር። በዚህ ረገድ፡ በሙሴ በኩል የደረሰበት ፈተና ሲታይ፡ ያስደንቃል፥ ያሳዝናልም፤ ምክንያቱም፡ የክፋቱና የዓመፁ ድርጊት ተቀነባብሮ የተፈጸመው፡ "ለምን፡ ኢትዮጵያዊቷን ሲጳራን፡ በሚስትነት አግብተህና ከእርሷ፡ ልጆችን ወልደህ፡ እንደእግዚአብሔር ሕግ፡ በአንድ ትዳር ኖርህ?" ብለው፡ የወንድማቸውን ጋብቻ በማስተሓቀር፡ በተነሣሡበት፡ በራሱ እህት፡ በሚርያምና በገዛ ወንድሙ፡ በአሮን በመኾኑ ነው።

ኹለተኛው የክፋት አሳባቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በላያቸው ትሰፍን ዘንድ፡ በየዘመናቱ የወረደላቸውን፡ የእግዚአብሔርንና የኢየሱስ ክርስቶስን የንጉሥነት ጸጋና ክብር፡ አይሁድ፡ በፈቃዳቸው እንዲቀበሉ፡ በቅድሚያ፡ ነቢዩ ሳሙኤል፡ በዘመነ ብሉይ፡ እየተማጸነ ያቀረበላቸውን ልመና፥ ኋላም፡ በዘመነ ሐዲስ፡ ጴንጤናዊው ጲላጦስ፡ እየገፋፋ የሰጣቸውን መመሪያ፡ ኹለቱንም በመቃወም፡ እስከመጨረሻው የጸኑበት፡ እምቢተኝነታቸው ነው።

መልከ ጼዴቅ፥ ሙሴ፥ ሰሎሞንና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ እያንዳንዳቸው፡ በየመልኩ፡ ቀድመው ወይም ተከትለው የተገለጡ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ጥላዎች ወይም ገጾች ኾነው እንደሚታዩ፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፥ የሙሴ ሚስት ሲጳራ፥ የሳባ ወይም የደቡብ ንግሥት እየተባለች የምትጠራው፡ ኢትዮጵያዊቷ ማክዳና የዘመነ ሐዲሷ፡ የኢትዮጵያውያን ንግሥት፡ ሕንደኬ ደግሞ፡ እያንዳንዳቸው፡ በየመልኩ፡ ቀድመው ወይም ተከትለው የተገለጡ፡ የድንግል ማርያም ጥላዎች ወይም መልኮች ኾነው ይታያሉ።

"ታቦተ ጽዮን" የምትባለው፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት የማክዳና የእስራኤላዊው ንጉሥ የሰሎሞን ልጅ በኾነው፡ በቀዳማዊ ምኒልክና እርሱን በመሰሉት፡ የእስራኤል በኵራት ታጅባ ወደኢትዮጵያ የመምጣቷና በዚህችው ምድር ለመቆየት የመፍቀድዋ ምሥጢር፡ የቅዱሱ ኪዳን አምላክ የኾነው እግዚአብሔር፡ ለዳዊት ከሰጠው የቃል ኪዳን ዘር ጋር፡ በኢትዮጵያውያን መካከል፡ ለዘለዓለም በአካል ተገኝቶ፥ በአገሪቱና በሕዝቡም ላይ ሰፍኖ መኖርን የወደደ መኾኑን በገሃድ ያረጋግጣል።

ከዚህ ጋር፡ በቅዱሱ ኪዳን ዜና መዋዕል'ስትዘከር የምትኖረው፡ ያች መለኮታዊት ድርጊት፡ የከፈተችው ሌላ ምዕራፍ አለ። ይኸውም፡ በፍጻሜ ዘመን የተገለጠውን፡ ዘለዓለማዊዉን ንጉሥ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እስከወለደችው፡ እስከድንግል ማርያም ድረስ ሳይቋረጥ፡ በቀጥታ የቀጠለውና ከቀዳማዊ ምኒልክ በኋላ በተከታታይ የነገሡትን፡ የዘውድ ወራሾች ሲያስገኝ የኖረው፡ የኢትዮጵያ ቤተ መልከ ጼዴቅና የእስራኤል ቤተ ዳዊት የትውልድ ሐረጎች የተዋሃዱበት፡ ዘር፡ በኢትዮጵያ መጀመሩ ነው።

# ኢትዮጵያ፡

በጠቅላላ፡ ስለክርስቶስ፥ በተለይም፡ ቅድሚያ ስላለው፡ ስለትስብእቱና ስለልደቱ የተነገረው ትንቢት ኹሉ፡ ለመጨረሻው ፍጻሜ እንዲበቃ ለማድረግ የሚያስችለውን መሠረት ለመጣል፡ የድንግል ማርያም ቅድመ አያቶች፡ የልጃቸው ተቀዳሚ አርአያ የኾነችውን፡ የንግሥተ ሳባን ፈለግ በመከተል፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደውን ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ የትውልድ ግንዳቸው የኾነው መልከ ጼዴቅ ወደቈረቈራት፡ ቅድስት ሀገር፡ ወደኢየሩሳሌም፡ አደረጉ።

የቅድስት ድንግል ማርያም ልደት፡ በሊባኖስ ተራራ፥ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ደግሞ፡ በቤተ ልሔም በረት፥ እንዲሁም፡ በጻድቁ ዮሴፍ የተጠበቀው ምድራዊ መጠለያቸው፡ በናዝሬት ዋሻ የመኾኑ ምሥጢር፡ ለዚያ ሃይማኖታዊ ጉዟቸውና ለመጻተኛ ኑሮአቸው እውነነት፡ በቂ ማስረጃ ኾኖ ይመሰክራል። "ዮሴፍ" የሚለው ስም፡ በግብፅ ስደተኛ ኾኖ ከኖረው፡ ከመጀመሪያው ዮሴፍ ወዲህ፡ ለስደተኛ ግለሰብ የሚሰጥ መኾኑ፡ እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው ነጥብ ነው።

እናትና ልጇ፡ በተለይ፡ ከሕፃኑ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላና ከጥምቀቱ በፊት፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው የመቆየታቸውን ነገር አበክረው የሚያመለክቱ እውነታዎች፡ በኢትዮጵያዊው ትውፊት ውስጥ፡ በዝተው ይሰማሉ። ይህንኑም፡ በመላዋ የኢትዮጵያ ምድር፡ በስፋትና በምልዓት የሚገኘው፡ ግዙፍና ቁሳዊ የኾነው ማስረጃ፡ በሕያውነት ከሚደመጠው ዜና መዋዕል ጋር ያረጋግጠዋል።

"ልጄን ከግብፅ ጠራሁት!" የሚለውን ትንቢት ለመፈጸም፡ ወደግብፅ ከመኼዳቸው በፊት፡ "ድንግል ማርያምና ሕፃኑ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከዮሴፍና ሰሎሜ ጋር ወደአገራቸው፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው፡ ቆይታ አድርገዋል" የሚለውን፡ ከላይ የተጠቀሰውን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ትውፊት የሚያጠናክሩ፡ ግልጽ የኾኑ የዘመናት ምልክቶች አሉ።

"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግሮቹን መረገጫዎች ያሣረፈባት ናት" ተብሎ የሚታመንባት፡ ለአኵስም ጽዮን ቤተ መቅደስ ትይዩ ኾና፡ ከበስተምሥራቅ የምትገኘው የኵረብታ እናት ሌላዪቱ ናት። እርሷም፡ ለዚሁ የተሰጣትን መታሰቢያነት በማጽናት፡ እስከዛሬ "መከየደ እግዚእ" ማለትም፡ "የጌታ መቆሚያ" ተብላ የምትታወቅበትን ስም እንደያዘች እነሆ ትኖራለች።

ከዋና ዋናዎቹ ምልክቶች መካከል አንደኛው፡ ያ ዘመን፡ በኖኅ ተጀምሮ፡ ሳይቋረጥ የቀጠለው፥ ኢትዮጵያውያንም፡ በአባታቸው በመልከ ጼዴቅ በተቈረቈረችው፡ በኢየሩሳሌምና በእናት አገራቸው፡ በኢትዮጵያ መካከል፡ ያደርጉት፡ የነበረው፡ የተለመደው ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ በላቀ ደረጃ የተካኼደበት ጊዜ መኾኑ ነው። ኹለተኛው ደግሞ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከአሥራ ኹለት ዓመት ዕድሜው በኋላ፡ እስከጥምቀቱ ድረስ፡ ምን ያደርግ እንደነበረ ወይም የት ይኖር እንደነበረ፡ በወንጌላውያን ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ ጨርሶ ያልተወሳ ሲኾን፡ ስለዚያ የዝምታ ጊዜ፡ ኢትዮጵያውያን ባልኾኑ ክርስቲያኖችና በሌሎች ወገኖች ዘንድ ጭምር፡ እስካሁን ምንም ዓይነት መግለጫ ያልተሰጠበት፡ ባዶ ስሌዳ ኾኖ መገኘቱ ነው።

እነሆም፡ እግዚአብሔር፡ ለዳዊት የሰጠው፡ ያ፡ የቃል ኪዳን ትንቢት ደርሶ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፡ ለፍጻሜ ፍሬ መብቃቱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ተረጋገጠ።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምድር ላይ የተመሠረተችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ዘለዓለማዊው ካህንና መደምደሚያው ንጉሥ ሲኾን፥ "እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች" የተባለችው "ኢትዮጵያ"፡ እርሷ መኾኗን በማሳወቅ፡ ይህ ዘለዓለማዊ ስሟና ምግባርዋ፡ በመዝሙረ ዳዊት ትንቢታዊ ቃል፡ ቀደም ብሎ የተነገረላት፡ ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ ንግሥቲቱ ኾነች! በዚህ ምክንያት፡ ስለሰው ፍቅር፡ በበረት ውስጥ፡ በትሕትና ተወልዶና በእንጨት ላይ በመሥዋዕትነት ተሰቅሎ የሞተው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመቃብር፡ በድል አድራጊነት ከተነሣ ወዲህ፡ በኢትዮጵያ መንበረ ዳዊት ዙፋን ላይ የተቀመጡት ኹሉ፡ የቅርቡ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጭምር፡ በቤተ ክርስቲያን ተቀብተው፡ ዘውድ የጫኑት፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር"፡ ማለትም፡ "በእግዚአብሔር የተሾመ" እና "ሐፀየ" "አጬ" ከሚለው፡ የግእዝ ቃል ስለተገኘ፡ "በእግዚአብሔር የታጨ" የሚል ተመሳሳይ ትርጓሜ ባለው፡ "አጼ" በሚለው የማዕርግ ስም ብቻ እንዲኾን ተደረገ:: እንግዴህ፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፡ ንጉሠ ጽዮን ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ"* የሚለው የስያሜና የማዕርግ ሐረግ፡ ለራሱ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእርሱ ብቻ የተሰጠ ስለመኾኑ፡ ምንም ዓይነት አጠራጣሪና [፳፰] አሻሚ ትርጉም ሊኖርበት አይችልም::

እዚህ ላይ፡ *ኢትዮጵያ* ሲባል፡ ቃሉ፡ ምንን እንደሚያመለክት፡ ምሥጢሩን ማስረዳት፡ አስፈላጊና ተገቢ ይኾናል:: ከሦስቱ የኖኅ ልጆች ነገዶች ተወልዶ፥ በቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊ ጸጋ ውስጥ ተጠብቆና በመላው የሰው ዘር ስም፡ እንደመዝሙረ ዳዊቱ ቃል፡ *እጆቿን ወደእግዚአብሔር ለመዘርጋት፡* ከሰው ልጆች መካከል የመመረጥ ብቅዓትን ባገኘችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ተወክሎ፡ በምድር ላይ የሚኖረው እልፍ አእላፋት ሕዝብ፡ "ኢትዮጵያ" ይባላል:: ስለዚህም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አይሁድ ፈሪሳውያን ላቀረቡለት ጥያቄ፡ *"እነሆ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት"* ሲል፡ መልስ በመስጠት፡ የተናገረው መለኮታዊ ቃል፡ በፍጹም መንፈሱና በተሟላ ቅርጹ፡ ለአይሁድ ሳይኾን፡ ለኢትዮጵያውያን የተፈጸመላቸው፥ በእነርሱም፡ እውን ኾኖ፡ እነርሱ ብቻ በግብር ላይ ሊያውሉት የቻሉ፡ የመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች ኾነው ለመገኘት በቅተዋል:: ይህም፡ በየግል ሰውነታቸው ሳይቀር፡ እውን መኾኑን፡ *"በአልባቢነ ናስተማስል፡ አምሳለ መንግሥትከ ቦቱ"* ማለትም፡ *"በየልቦናችን ለፍና፡ በተገለጸችው መንግሥትህ"* በሚለው፡ የዘወትር የኪዳን ጸሎታቸው [፳፱] ላይ እያረጋገጡ፡ ዘወትር ያጸኑታል::

ኢትዮጵያ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለኾነች፡ ማንም መሪ፥ ያለእርሱ ፈቃድ፡ ሥልጣን ሊይዝ አይችልም:: በኢትዮጵያ ውስጥ፡ ባለፉት ዘመናት፡ በቤተ ክርስቲያን ተቀብተው፡ በሕጋዊ ሥርዓት፡ ዘውድ በመጫን ኾነ፡ በዓመፅ፥ በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው ዘርፍ፡ የአመራሩን ሥልጣን የያዙት ኹሉ፡ በእርሱ ዳኝነትና ትእዛዝ፡ የእርሱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መሣሪያዎች ኾነው እንዲያገለግሉት የተመደቡ ነበሩ፤ የዛሬዎቹም ናቸው፤ የወደፊቶቹም፡ ለዚሁ የሚጠሩ ይኾናሉ:: የዚች መለኮታዊት መንግሥት ምስፍና፡ በየትኛውም ህልውና ዘልቆ በመግባት፡ መላውን ፍጥረተ ዓለም የሚያጠቃልል በመኾኑ፡ ይህ ሥርዓት ጸንቶ የሚሠራው፡ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን፡ በምድር ላይ ባለ፡ [፴] በእያንዳንዱ አገር ጭምር መኾኑን፡ ኢትዮጵያውያን ያምናሉ::

## ኢትዮጵያ፡
## የእግዚአብሔር መንግሥት
## የመኾኗ ምሥጢር።

በኢትዮጵያ ሰፍና የምትኖረው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሦስት የአገልግሎት አካላዊ ዘርፎች አሏት። እነዚህም፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና ይባላሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የታነጸበት፡ ይህ የሦስትነት ባሕርይ ምሥጢር፡ *"ሢሦ ለአንጋሽ፥ ሢሦ ለነጋሽ፥ ሢሦ ለቀዳሽ"* በሚለው ኪዳናዊ ይትበሃል፡ የበለጠ ተተርጉሞ፥ ጎልቶና ተብራርቶ ይታወቃል። ይህም ማለት፡ በማናቸውም ረገድ፡ የመንግሥቱ አንድ ሦስተኛ የኾነው ድርሻ፡ የቤተ ሕዝቡ፥ ሌላው አንድ ሦስተኛ የኾነው ድርሻ ደግሞ፡ የቤተ ክህነቱ ሲኾን፥ የቀረው አንድ ሦስተኛ የኾነው ድርሻም፡ የቤተ ምልክናው ይኾናል ማለት ነው። የምሥጢሩን ትርጓሜ አግዝፎ ለማስረዳት፡ በሰብአዊው ተፈጥሮ፡ ቋሚ የኾነችው የነፍስ አካል፡ ሥጋዊ አካልና መንፈሳዊ አካል እንዳሏት ኹሉ፡ የእግዚአብሔር በኾነችውም መንግሥት፡ ቤተ ሕዝቡ፡ እንደነፍስ፥ ቤተ ምልክናው እንደሥጋ፥ ቤተ ክህነቱም፡ እንደመንፈስ አካላት ኾነው ይመደባሉ።

እንግዴህ፡ ግንዱ አካል ለኾነው፡ ለቤተ ሕዝቡ ሥጋዊ ህልውና፡ የሚያስፈልጉትን የአስተዳደርና የአገልግሎት ተግባራት ለማበርከት፡ የኃላፊነቱ ዘርፍ፡ የቤተ ምልክናው ሲኾን፥ ለቤተ ሕዝቡ መንፈሳዊ ህልውና፡ የሚያስፈልጉትን ለማበርከት ደግሞ፡ የኃላፊነቱን ዘርፍ የያዘው፡ ቤተ ክህነቱ ነው ማለት ይኾናል።

በምድራዊው ሥልጣኔ የተራመደው፡ ዘመናዊው ዓለም፡ "የመጨረሻው የሥነ መንግሥት ብቅዓት ነው" ብሎ በሚታመንበት ብሔራዊ የአስተዳደር ሥርዓቱ፡ "ሕግ አውጪ፥ ሕግ ፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ" የሚላቸው ሦስት ዘርፎች፡ ይህን መዋቅር የተከተሉ በመኾናቸው፡ የዛሬው የሰው ልጅ እየተጠቀመበት ያለው፡ ያገርና የመንግሥት አስተዳደር ፍልስፍና፡ ምንጩ፡ ማንና ከየት እንደኾነ፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፤ ይኸውም፡ ከኢትዮጵያውያንና ከኢትዮጵያ መኾኑን ነው።

ኢትዮጵያውያን፡ ህልውናቸውን ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ፡ እነዚህ ሦስት ቤቶች የሚያበረክቷቸው የጸጋ ሥልጣናት፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተሰጡ መብቶች ኾነው፡ በእያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሰውነት ውስጥ ተዋህደውና ሰፍነው የሚገኙ ኾነዋል። ይህም የኢትዮጵያውያን የብቅዓት ማዕርግ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም መምጣትና እነርሱም፡ ለእርሱ ባደረጉት፡ የሃይማኖት አቀባበል፡ ለመጨረሻ ጊዜ ታትሞላቸዋል። በዚህም፡ እንዲህ ብሎ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ተፈጽሟል፡- ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ማንነቱን አውቀው *"ለተቀበሉት ኹሉ፥ በስሙ ለሚያምኑት፡ ለእነርሱ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይኾኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፡ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።"* ደግሞም፡ *"ታርደሃልና፥ በደምህም፡ ለእግዚአብሔር፡ ... ሰዎችን ዋጅተሀ፡ ለአምላካችን፡ መንግሥትና ካህናት ይኾኑ ዘንድ አደረግሃቸው፤ በምድርም ላይ ይነግሣሉ።"* እንዲሁም *"የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይኾናሉ፤ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።"*[፳፩]

## የዓለሙ መፋረጃ!

ይህ የእግዚአብሔር ቃል፡ ያስገኘው የብቅዓት ደረጃ፡ እውነተኛውን ኢትዮጵያዊ፡ በሦስቱም ቤቶች ውስጥ ለሚኖረው ለማንኛውም የመጨረሻ ዝቅተኛ፥ ወይም የመጨረሻ ከፍተኛ የአገልግሎት ኃላፊነት ቦታ፡ ለኹሉም እኩል፡ ብቁና ተገቢ ኾኖ ሊታጭ እንዲችል አድርጎታል። ከዚህም በላይ፡ ይኸው የብቅዓት ደረጃ፡ ማንኛውም "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊ፡ በቤተ ክርስቲያን ተቀብቶና ዘውዱን ጭኖ፡ ወይም ማንኛዪቱም "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊት፡ ተቀብታና ዘውዱን ጭና፡ በመንበረ ዳዊቱ ዙፋን ላይ በመቀመጥ፡ የንጉሠ ነገሥቱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የንግሥተ ንግሥታቱ፡ የድንግል ማርያም እንደራሴ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ዋና አገልጋይና የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶቿ፡ ባለአደራ ተመልካች ለመኾን፡ የሚያስችለውንም ጸጋ፡ ለኢትዮጵያውያን አጐናጽፏል። ይኸውም፡ "አጼ" ወይም "ንግሥት"፡ ማለት "ሥዩመ እግዚአብሔር" ወይም "ሥይምተ እግዚአብሔር"፡ ይህም ሲተረጐም፡ "በእግዚአብሔር ተመርጦ የተሾመ" ወይም "በእግዚአብሔር ተመርጣ የተሾመች" በሚል የማዕርግ ስም የሚከብረው የመጨረሻው ሹመት ነው።

ይህ መሠረታዊ እምነት፡ የኢትዮጵያ ህልውና ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ፡ በተለይም ከክርስቶስ ልደት ወዲህ፡ መደበኛ ሥርዓት ኾኖ፡ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የተቀመጡት ኢትዮጵያውያን ኹሉ፡ የተመረጡበትንና የተቀቡበትን ወግ እየደነገገ ሲመራና ምንጊዜም ሲያስፈጽም ኖርዋል። ይኹን እንጂ፡ በዚህ ዙፋናዊ የዘውድ ሥልጣን ላይ፡ ከዚህ ከመደበኛው ሥርዓት ውጪ፡ የተካኼዱና የሚካኼዱ የዓመፅ ወይም ሌላ የኃይል ተቃውሞዎች መኖራቸው በግልጽ ይታወቃል። ነገሩን በሃይማኖታዊ ዓይን ሲመለከቱት፡ እነዚህን አሳዛኝ ኹኔታዎች ለማስከተል ምክንያት የኾኑት ጠንቆች፡ ምን እንደኾኑ ለመረዳት ከቶ አያዳግትም። ይኸውም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉት፡ ሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ አንዳቸው ወይም ኹሉም፡ የእግዚአብሔርን ቅዱሳት ኪዳናት፡ በክህደት በሚያፈርሱበት ጊዜ፡ ይህ ድርጊታቸው፡ መርገምን የሚያስከትል፡ ርኵሰት ስለሚኾንባቸው ነው! ይህን የመሰለውም ርኵሰት፡ ጽዋው ሲሞላ፡ ከዚህ የተነሣ የሚመጣውን፡ መለኮታዊዉን የቅጣት ቁጣ የሚያቀጣጥሉ፡ የጥፋት ጠንቆች፡ ይፈጠራሉ። ያ ዓመፅ ወይም የኃይል ተቃውሞ፡ የእነዚህ የጥፋት ጠንቆች ውጤት ነው።

ይህንንም ኹሉ፡ ስላለፉት ዘመናት በሚናገረው ዜና መዋዕል (ታሪክ) የተመዘገቡት፡ የየጊዜያቱ ድርጊቶች፥ እንዲሁም፡ በቅርቡ የተከሠቱት እውነታዎች፥ ዛሬም በአገሪቱ ውስጥና በየአህጉሩ ተሠራጭተው በሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ሕይወት ላይ የሚታዩት ኹኔታዎች በይፋ ያረጋግጡታል። ለዚህ ማስረጃ እንዲኾኑን፡ "አያድርስ!" ከሚያሰኙት፡ ከቀደሙት ተመሳሳይ የመከራ ዘመናት መካከል፡ "አሠቃቂዎች ናቸው" የተባሉትን ጥቂቶቹን እጠቅሳቸዋለሁ። እኒህም፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ሕያዋን ዝክሮች ኾነው ሲታወሱ የሚኖሩት፥ ባለፉት አሠርተ ምዕት ዓመታት ውስጥ፡ አልፈው አልፈው እየተነሡ፡ አገሪቱን ያጥለቀለቁት የዓመፅ ማዕበሎችና ከእነርሱ በኋላ፡ በሚያስፈራ መጠን የተከተሉት ታላላቅ የድምሳሴ እልቂቶች ናቸው።

በእነዚህ ዝርዝር ውስጥ፡ ጎልታና ቀዳሚ ኾና የምትታየው፡ “ጉዲት” ወይም “እሳቶ” የተባለችው ስመጥፉዋ ይሁዲት ስትኾን፥ ከእርሷ ቀጥሎ፡ ጨካኙ እስላም አሕመድ ግራኝ ይገኛል፤ እርሱም፡ በአገሪቱ ላይ ካደረሰው፡ ወደር ከሌለው ጥፋት የተነሣ፡ ካቶሊካውያን የወንጌል ልዑካን፡ ኃይል አግኝተው፡ በሕዝቡ መካከል በቀሰቀሱት የሃይማኖት መለያየት ምክንያት፡ የእርስ በርስ ጦርነት ተነሥቶ፡ አያሌ የንጹሓን ደም ሊፈስስ ችሏል:: ከዚያም፡ የቅርቡ ግፈኛው የዘር ጠላት፡ ካቶሊካዊው ፋሺስት መሪ፡ ሙሶሎኒ ይጠቀሳል:: በመጨረሻም፡ በዛሬው ትውልድ ላይ ለደረሰው፡ የበቀል ቅጣት፡ በመሣሪያነት ተመድቦ፡ ተልእኮውን የፈጸመውና “እግዚአብሔር የለም” በሚል የስንፍና እምነት፡ “ኮሚዩኒስት ነኝ” ባዩ፡ የትናንቱ የደርግ መሪ፡ አብዮታዊው (ዓመፀኛው) መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አለ:: (በግእዝ፡ አበየ = ዐመፀ) ከዚህ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ በመንግሥቱ ንዋይ፡ የተፈጸመው፥ የብዙዎች ደም የፈሰሰበትና ውጤት-አልባ የነበረው የአልጋ ማፍረስ ሙከራም፡ እዚህ ላይ ሳይወሳ የሚታለፍ አይደለም::

እኚህ ኹሉ የጥፋት ጠንቆች ተነሥተው፡ ያን ያህል እልቂትንና ድምሳሴን ለምን ፈጸሙ? ይህስ ኹሉ፡ ከጥንስሱ፡ ከመሠረቱ ጀምሮ፡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ ኾነ ይባላልን? እንደኢትዮጵያውያን እምነት፡ አይባልም:: ለዚህም፡ በዚህ ዘመን፡ በመጨረሻ የኾነው፡ ለአብነት ቢጠቀስ ይበቃል:: ይኸውም፡ እንዲህ ነው:-

የኢትዮጵያ መንግሥት፡ የሚመራውና የሚካሄደው፡ በንግሥቲቱ እናት፡ በድንግል ማርያምና በንጉሠ ነገሥት ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለመላው ዓለም፡ እንደገና በይፋ አረጋግጦ ለማሳወቅ፡ እግዚአብሔር፡ “መንግሥቱ፡ የማርያም ኃይል ነው” የሚል መጠሪያ ስም ያለውንና ነገር ግን፡ ርኅራኄ የሌለውን፡ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን አስነሥቶ፥ የተሻለ ሌላ ቦታም ሳይጠፋ፡ በ“በዓታ ለማርያም” ዓፀደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀምጦ፡ ምን እንዲፈጽም እንደፈቀደ፡ በኹሉም ዘንድ በግልጽ የታወቀ ስለኾነ፡ ተጨማሪ ሐተታ አያስፈልገውም::

ከዚህም ቀደም ብሎ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ “የማርያም ኃይል” የተባለው፡ ይህኛው መንግሥቱ፡ ሊያደርስበት ከተዘጋጀው ታላቅ የቅጣት ፍርድ ለመዳን ይችል ዘንድ፡ በጊዜው፡ በቶሎ ንስሓ እንዲገባ፡ እግዚአብሔር፡ የድንግል ማርያምን የቃል ኪዳን የምሕረት አማላጅነት አስቦ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፡ እንደጽኑ ማስተማሪያ፥ ማስጠንቀቂያና ተግሣፅ፥ እንዲሁም፡ እንደመጨረሻ የማንቂያ ደወል አድርጎ እንዲያገለግለው፡ በስምም፥ በግብርም፡ የዚህኛው ሞክሼ የነበረውን፡ “የማርያም ንዋይ” የተባለውን፡ ያኛውን መንግሥቱን በመላክ፡ ያደረገለትን አምላካዊ ቸርነት፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይዘነጋውም::

እዚህ ላይ፡ አሁንም፡ ጥቂት ወደኋላ ራቅ ብለን፡ ደርሶ የነበረውን ብንመለከት፡ ኢትዮጵያን በዕብሪት ለመውረር፥ ኢትዮጵያውያንንም በግፍ ለመጨፍጨፍ፡ የመጡት ባዕዳን ጠላቶች፡ እንዴት ድል ተመትተው እንደጠፉ፥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንም፡ ከእነዚያ ወረራዎችና እልቂቶች ድነው፡ እንዴት ሊተርፉ እንደቻሉ፡ በተለይ ለእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ በቀላሉ መረዳትና ማስረዳት አያዳግትም:: ይኸውም፡ ይህ ኹሉ የኾነው፡ *ከቅዱሱ ቃል ኪዳን የተነሣ መኾኑን፡ በፍጹም ስለሚያምኑ ነው::*

ለዚህም፡ በቅድሚያ፡ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን የኾነው ተአምር፡ ሊጠቀስ ይገባዋል። በዚያን ጊዜ፡ ያለአንዳች ተቀናቃኝ፡ የዓለሙ ብቸኛ ኃያል መንግሥት በመኾን፡ ለቅኝ ግዛት፡ የጋለ ጥማት የነበረው፡ የእንግሊዝ፡ የዘውድ መንግሥት፡ ታላቅ የጦር ሠራዊቱን፡ ከከባድ የጦር መሣሪያው ጋር፡ ወደኢትዮጵያ አዝምቶ ሣለ፡ በተከላካዩ ቆራጥ የአገሪቱ መሪ፡ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ፡ የመጨረሻውን ፍጹም ድል የተቀዳጀ ሲኾን፥ እንደዛሬው ኹሉ፡ ለገናንነቱና ለተስፋፊነቱ፡ "ማስናከያ ድንጋይ" ኾናበት የኖረችውንም ኢትዮጵያን፡ ከእጁ ለማስገባት የቻለ ሲኾን፡ "ልዋል! ልደር!" ሳይል፡ ያለአንዳች ሰብአዊ ግዳጅ፡ እንደጉንዳን ሠራዊት፡ በመጣበት እግርና ጎዳና፡ ሰተት ብሎ ወደአገሩ መመለሱ፡ ዕፁብ ድንቅ አይደለምን? ቀጥሎ፡ በአጼ ዮሐንስ ዘመን የተፈጸመው ሌላው ተአምር፡ ሳይወሳ አያልፍም። በዚያን ጊዜ፡ በሠለጠኑ አሜሪካውያንና በሌሎች ነጮች የጦር አበጋዞች እየተመሩ፥ በተሟላም የጦር ትጥቅ እየታገዙ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ፡ ለአያሌ ጊዜያት ተመላልሰው የዘመቱት፡ የቱርክ፥ የግብፅና የሱዳን እስላማውያን እልፍ አእላፋት የጦር ሠራዊቶች፡ ድል እየተመቱ መመለሳቸው፡ ዕፁብ ድንቅ አይደለምን?

ከዚያ ወዲህ ተከታትሎ፡ በአጼ ምኒልክ ዘመን የተፈጸመውን ተአምር ሲያነሡት፡ ሌላ ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ኃይል ተደርጎ ይታያል። ይህም፡ ቀደም ብለው ለተጠቀሱት ተአምራት ጭምር ማብራሪያ ይኾን ዘንድ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ጋር የሚያያዝበት ሃይማኖታዊ ምሥጢር፡ እንዲህ በሚል ቃል ተገልጾ ይቀርብበታል።

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ፡ በአድዋ ጦርነት፡ በካቶሊካዊው የጣልያን ሠራዊት ላይ የተጐናጸፉትን ድልና ኋላም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በማይጨው ጦርነት፡ በዚያው፡ የጣልያን ተመሳሳይ ሠራዊት፡ የደረሰባቸውን ሽንፈት፡ ኢትዮጵያውያን፡ የኹለቱንም ዕድሎች ምክንያት፡ በቀጥታ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ጋር ያያይዙታል። ይኸውም፡ "እንዲህ ወይም እንዲያ የኾነበት ምክንያት፡ እነዚህ ኹለቱ አጼዎች፡ እያንዳንዳቸው፡ ከነቤተ ሕዝባቸው፥ ቤተ ክህነታቸውና ቤተ ምልክናቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ውስጥ የተመለከቱትን ግዳጆቻቸውን፡ በእውነት አክብረው፡ በትክክል ከመፈጸማቸው ወይም በእውነት ሳያከብሩ፡ በትክክል ካለመፈጸማቸው የተነሣ መኾን አለበት" ከሚለው ሃይማኖታዊ አቋም፡ የሚመነጨው አስተሳሰብ ነው።

አዎን! አጼ ምኒልክና ሕዝባቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ማለትም፡ በቃል ኪዳን አምላካቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በቃል ኪዳን ንግሥታቸው፡ በድንግል ማርያም ላይ፡ ፍጹም እምነትና ሙሉ ትውክልት ስለነበራቸው፡ እነሆ፡ ያን ኃያል የነበረውን፡ የጣልያን ወራሪ ጦር፡ ያለአንዳች፡ የባዕዳን አጋርና እርዳታ፡ እጅግ በሚያስገርም ኹኔታ ድል አደረጉት። በዚህ አንጻር ደግሞ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴና ሕዝባቸው፡ በዠኔቭ በነበረው፡ የመንግሥታት ማኅበር ላይ፡ ፍጹም እምነትን በመጣል፡ በማኅበሩ ቃል ኪዳን በመማጸናቸውና በእርሱ ብቻ በመታመናቸው፡ ይህ አድራጎት፡ ቅዱሱን ኪዳን እንደመካድና እርሱን እንደማርከስ ስላስቆጠራቸው፡ እነሆ፡ በካቶሊካዊው ሙሶሎኒ በሚመራው፡ የጣልያን ፋሺስታዊ ጦር ሠራዊት የመሸነፍ ውርደትን አስከተለባቸው።

# ኢትዮጵያ፡

በቤተ ሕዝቡና በቤተ ክህነቱ፥ በቤተ ምልክናውም መናብርት ላይ ተቀምጠው፥ በክህደት መርገምም ተወግዘውና ተይዘው በሚገኙ፡ ያገር ተወላጆች ተባባሪነት፡ ዛሬ በኢትዮጵያ፡ ሥልጣን በጨበጠውና "ሕዝባዊ አገዛዝ" በተባለው መንግሥት፡ የሚወጠነው ሥር ነቀል የኾነው ኹለንተናዊ አመራርና የሚካኼደው የሥራ አፈጻጸም፡ ባሁኑ ጊዜ ሰፍኖ የሚታይ ሌላው እውነታ ነው።

በዚህ ላይ የቀረበው ሐተታ፡ እንዲህ በሚለው አገላለጽ ይጠቃለላል፡- በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት፡ በቤተ ክርስቲያን ተቀብተውና ዘውድ ጭነው፡ በኢትዮጵያ መንበረ ዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጡ ኢትዮጵያውያን "አጼዎች"፡ ለሕዝቡ በጉነትና ደኅንነት ሲል፡ እግዚአብሔር መርጦና ሹሞ እንደላካቸው እረኞች ተቆጥረው፡ በእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ተገቢውን እውቅናና ተቀባይነት ያገኛሉ። የቅዱሱ ኪዳን ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ አንዳቸው ወይም ኹሉም፡ በቅዱሱ ቃል ኪዳን ላይ፡ ጽኑ የኾነ የድፍረት ወይም የክህደት በደልን በሚያደርሱበት ጊዜ ደግሞ፡ እኒያ፡ ዙፋናዊዉን ሥልጣን፡ በዓመፅና በኃይል የሚይዙት፡ የቁጣ መሣሪያዎች፡ ያ፡ የሕዝቡና የአገልጋዮቹ በደል የሚያስከትለውን የመርገም ቅጣት ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንደተላኩ ተቆጥረው፡ እኒያ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን በትዕግሥት ይቀበሏቸዋል።

በዚህ ረገድ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ በፊት የነበሩት፡ በጣም የቅርቦቹ "አጼዎች" ወይም "የእግዚአብሔር ሹሞች"፡ ዳግማዊ ቴዎድሮስ፥ ተክለ ጊዮርጊስ፥ ዮሐንስ አራተኛ፥ ዳግማዊ ምኒልክና ንግሥት ዘውዲቱ ሲኾኑ፥ "አብዮተኞቹ" ደግሞ፡ አማን፥ ተፈሪ፥ መንግሥቱ፥ ተስፋዬ እና መለስ ናቸው።

እንግዴህ፡ ቅርብ በኾነው ዘመናችን የነበሩትን ለመጥቀስ ያህል፡ እነአጼ ቴዎድሮስ፥ እነአጼ ዮሐንስ፥ እነብፁዕ አባ ጴጥሮስ፥ እነብፁዕ አባ ሚካኤልና እነርሱን የመሰሉት እውነተኞች ኢትዮጵያውያን፡ ለእርሷና እርሷ ለቆመችለት ዘለዓለማዊ ዓላማ ሲሉ፡ ሕይወታቸውን የሠዉላት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ይህች ናት።

እኒህ፡ የቀደሙትና ዛሬም በሕይወተ ሥጋ እየተጋደሉ ያሉት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እስከዚች ቀን ድረስ፡ እርሷን በእውነት ለማገልገል፥ በፍቅር ለመጠበቅና በሕያውነት ለማስተላለፍ፡ የተቀበሉትን ኪዳናዊ አደራ፡ እስከመጨረሻው አክብረው ኖረዋል። ዛሬና ወደፊትም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጸሎታቸውን ተቀብሎ፡ በዘላለማዊ ሕይወት ሰፍናና ገዝፋ በምትኖረው፡ ገናና መንግሥቱ፡ በድል አድራጊነት እስከሚገለጽባት፡ እስከዳግም ምጽዓቱ ድረስ፡ ይህንኑ የፈቃድ ግዳጃቸውን ቀጥለው፡ ከግብ ለማድረስ፡ እንደገና ቃል ገብተው፡ ይኸው ህልውናቸውን ቀጥለዋል።

"ታዲያ፥ እኔስ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"

## ሰባተኛው ቃል ኪዳን፡ ኪዳነ ምሕረት፡፡

እግዚአብሔር፡ ፍጥረቱ ኹሉ፡ ለዘለዓለም እየታደሰ ይኖርበት ዘንድ፡ ከሰው ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን፡ የመጨረሻውና ሰባተኛው ነው፡፡ ያም ቃል ኪዳን፡ እውን የኾነውና የተፈጸመው፡ ዳግማዊው አዳም ተብሎ፡ ከዳግማዊቷ ሔዋን፡ ከድንግል ማርያም በተወለደውና የእግዚአብሔር ልጅ በኾነው በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

## የቅዱስ ቍርባን፡ የመጨረሻ ማኅተምነት፡፡

ይህ አዲስ ኪዳን፡ በምሥጢረ ቍርባን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ይኾን ዘንድ፡ በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ በሚለወጠው፡ ኅብስትና ወይን ገዝፎ በሚቀርበው፡ ቅዱስ መሥዋዕት፡ ለዘለዓለም ሲታሰብና ሲከበር ይኖራል፡፡ አዎን! ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱ፡ ከድንግል ማርያም በወረሰው ሕያው አካል፡ እግዚአብሔር፡ ፍጹም ሰው በመኾኑና እርሱም፡ በዚህ በለበሰው ሰውነቱ፡ በመስቀል ላይ ራሱን በመሠዋቱ፡ ለፍጥረቱ፡ ዘለዓለማዊ ደኅንነትን ስላስገኘ፡ እነሆ፡ አዲሱ የምሕረት ቃል ኪዳን በር ተከፈተ! የሰባተኛው ቃል ኪዳን ሕያው ምልክት የኾነው፡ ይህ ምሥጢረ ቍርባን፡ ከላይ ቀደም ብለው ለታተቱትና ለዚህኛው፥ ባጠቃላይ ለሰባቱም ቅዱሳት ቃል ኪዳናት፡ የመጨረሻው ማኅተምና ዘውድ ነው፡፡

እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ ፈጣሪያቸውንና እናቱን፡ ቀንና ሌሊት፡ በውዳሴ፥ በዝማሬ፥ በቅኔና በቅዳሴ በማመስገንና ስለእነርሱ ሐሤት በማድረግ፡ በየዕለቱ በሚያካኺዱትና በሚፈጽሙት ቋሚ ሥርዓታቸው፡ ቅዱስ ቍርባንን፡ ያለማቋረጥ ይቀበላሉ፡፡ በዚህም አድራጎታቸው፡ ለአምላካቸውና ለመድኃኒታቸው፥ ለዘለዓለማዊው ሊቀ ካህናታቸውና ንጉሠ ነገሥታቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እንዲሁም፡ ለዘለዓለማዊት ንግሥታቸውና ቅድስት እናታቸው፡ ድንግል ማርያም ያላቸውን የሃይማኖት ታማኝነትና የምግባር ግዳጅ፡ ዘወትር እያጸደቁና እያረጋገጡ ይኖራሉ፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ራሳቸውን፡ እንዲህ፡ ባልተቋረጠ ንስሓ እያነጹና እያጸደቁ፡ ይህን ቅዱስ ቍርባን፡ ዘወትር ስለሚቀበሉ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ ለመለኮታዊው የዘውድ መሪያቸውና ለንግሥት እናቱ፥ እንደዚሁም፡ ለየራሳቸውና ለሰብአውያን ወገኖቻቸው ያረጋግጣሉ፡፡

## ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ የአዲስ ኪዳኑ "አቤሜሌክ"፡፡

ሰባተኛውን ቃል ኪዳን፡ ከዜና መዋዕል ሥፍራው አግጣጫና በተለይ፡ ለኢትዮጵያውያን ካለው አግባብ ጋር አያይዘው ሲመለከቱት፡ ያ፡ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ፡ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ያዘጋጀለትን መንገድ በመከተል፡ በጥምቀት አማካይነት፡ ከኪዳነ አሪት፡ ወደኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ በጥምቀት ተሸጋግሮ፡ ሉዓላዊት ለኾነችው፡ ለክርስትና እምነት የበቃባት ያች ዕለት፡ እጅግ አስደናቂ ድርጊት የተከናወነባት ታላቅ ቀን መኾኗ፡ ሊታበል ከቶ አይቻልም፡፡

ምክንያቱም፡ ያ፡ በመልከ ጼዴቅ ቃል ኪዳን የተገኘው ኢትዮጵያዊነት፡ ከአዲሱ ኪዳን ጸጋ የተነሣ፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አዲስ ሰውነት፡ እንደገና ታድሶ የጎለበተው፡ በዚያች ዕለት በተፈጸመው ተአምራዊ ክዋኔ በመኾኑ ነው። ይህም፡ በሌላ መልክ ሲገለጽ፡ በዚያች ዕለት፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሕይወት ላይ የታየው፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ለውጥ፡ ያን፡ በመለኮታዊው ዕቅድ መሠረት፡ "ምሉዕ ኢትዮጵያዊ" ለመኾን የሚያበቃውን፥ ማለትም፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና የተባሉት፡ እኒህ የእግዚአብሔር መንግሥት ሦስት አካሎች ተዋህደው፡ በአንድ ሕያው ሰውነት ውስጥ እንዲያድሩ የሚያደርገውን የዕድገት ሥርዓት፡ ከፍጹምነት ደረጃ አደረሰው ማለት ይኾናል።

በዚህ ኹኔታ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ የአዲሱ ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር፡ አቅኚና መሪ የኾነው ይህ፡ የተባረከ ኢትዮጵያዊ፡ "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" ብቻ እየተባለ በግብር ስም ከሚጠቀስ ይልቅ፡ ከዚህ የዜና ዓምድ አንሥቶ፡ እንደትውልድ ሓረግ፡ ተወራራሽ ኾኖ፡ ከእርሱ በደረሰው፡ "አቤሜሌክ" በሚለው የማዕርግ ስም ሊጠራ ፍጹም ተገቢነት አለው ቢባል ትክክለኛ አስተያየት ይኾናል። ምክንያቱም፡ ከእርሱ ቀደም ብሎ፡ በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነትና በፍጹም እርአያነት ተገልጸ የታየ፡ ምሳሌውና ጥላው የኾነው፡ የብሉዩ ኪዳን ኢትዮጵያዊ፡ በዚሁ "አቤሜሌክ" በሚለው ስም ይታወቅ ስለነበረ ነው። ይህ፡ የፊተኛው "አቤሜሌክ"፡ በይሁዳው ንጉሥ፡ በሴዴቅያስ ቤተ መንግሥት ባለሟል ኾኖ፡ በኋለኛው፡ ማለትም፡ የንግሥት ሕንደኬ ቤተ መንግሥት አዛዥ በነበረው፡ በ"ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" ተመሳሳይ ሥልጣን፡ የሚያገለግል ነበረ።

እርሱም፡ በነቢዩ ኤርምያስ ላይ የተሰጠውን የግፍ ፍርድ፡ ወዲያው ከንጉሡ አማልዶ፡ በምሕረት ለማስለወጥ በመቻሉ፡ ኢትዮጵያዊነት ምን እንደኾነ፡ በምግባር አረጋግጦ ለማሳየት የበቃ ስመጥር ኾኗል። ስለዚህ፡ የኹለቱም "ጃንደረቦች" ኢትዮጵያዊ ሕይወት፡ በአካልና በግብር ብቻ ሳይኾን፡ "አቤሜሌክ" በሚለው ስምም እንደሚመሳሰል፡ በሃይማኖት በማረጋገጥ፡ "ስመ-ሞክሼነታቸውና ቡሩክነታቸው፡ ለኹለቱም ሊጸድቅላቸው የሚገባ ነው" ያሰኛል። "አቤሜሌክ"፡ በግእዝ፡ "የንጉሥ አባት"[፷፱]፥ "ኤቤድሜሌክ" ደግሞ፡ "የንጉሥ አገልጋይ" ማለት ነው።

እንግዴህ፡ "ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ" እየተባለ በሚጠራው፡ በአዲሱ ኪዳን "አቤሜሌክ" አማካይነት፡ ኢትዮጵያውያን፡ ይህን ከመሰለው፡ ከመጨረሻው ሃይማኖታዊ ብቅዓት ስለደረሱ፡ ከዚህ በኋላ፡ "በቃ! ተመለሱ! ውጡ!" ወደማይባሉበት፥ በምድር ላይ፡ በዘለዓለማዊ ፍጹም ፍሥሓ ወደሚኖሩባት፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት "ግቡ!" ለመባል በቅተው፡ እነሆ! ህልውናቸውን፡ በእርሷ ሕይወት ውስጥ ቀጥለዋል። በዚህም፡ ዘለዓለማዊው ንጉሥ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እውነት እውነት እልሃለሁ! ሰው፡ ከውኃና ከመንፈስ፡ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም"* ሲል ለኒቆዲሞስ አረጋግጦ[፸]፡ እጅግ በሚያስተማምን ቃሉ፡ ባሰማው አዋጅ ተፈጽሞላቸዋል።

## ለብፅዕና የሚያበቃው፡ ኢትዮጵያዊው ሃይማኖት።

ኢትዮጵያውያን፡ ማናቸውንም መከራ በትእግሥት ተቋቁመው፡ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ድረስ ያሉትን፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት፡ በሕይወታቸው በማግለጥ+ በመጠበቅና ከትውልድ ወደትውልድ በማስተላለፍ ያሳዩት ያልተበገረ ጽናት፡ ምንጊዜም ሳይናወጽ እንደነበረ ቀጥሏል። በረዥሙ ህልውናቸው ጉዳና ላይ የገጠማቸውንም፡ እያንዳንዱን የፈተና ዘመን፡ እያሸነፉ ሊያልፉ የቻሉት፡ ለብልሃቱም ኾነ ለመፍትሔው፡ ሰብአዊው ጥበብ በፈለሰፈው፡ በረቂቁና በግዙፉ የኃይል መሣሪያ በመጠቀም ሳይኾን፡ የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ኃይል በመተማመን ብቻ ነበር።

ኢትዮጵያውያን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ሲሉ የፈጸሙት፡ ይህን የመሰለው፡ መንፈሳዊ ግዳጃቸው፡ እንዲህ፡ እንደብረት ሰንሰለት ተጠናክሮ ሳይቋረጥ ሊቀጥል የቻለበት ምክንያት፡ ሥውር አይደለም፤ *"ካላየሁትና ካልዳሰስኩት አላምንም"* ላለው ለደቀ መዝሙሩ፡ ለቶማስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"አንተ ሰላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያመምኑ፡ ብፁዓን ናቸው!"* ብሎ የተናገረው ቃሉ፡ ይህን እውነታ ገልጾና አረጋግጦ ያስረዳል።

ይህ የጌታ ቃል፡ እውን ኾኖ ሲፈጸም ለማየት፡ ረዥም ጊዜን አልወሰደም። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ "አቤሜሌክ"፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ቀደም ብሎ እያስተማረው ካገኘው እውቀት+ በእርሱም መሪነት፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመጽሐፍ ካነበበውና ከፊልጶስ እንደበት፡ በቃል ተነግሮት ከሰማው በቀር፡ በአካል ገዝፎ ያየውና የተመለከተው አንዳች ነገር ሳይኖር፡ የፈጸመው፡ ትንግርታዊ የሃይማኖት ምግባር ነው።

ይኸውም፡ *"ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ አምናለሁ"* ሲል የሰጠው ፈጣን የሃይማኖት መልስና የጥምቀቱ ሥርዓት፡ እዚያው እመንገዱ ላይ እንዲፈጸምለት፡ ለሐዋርያው ፊልጶስ፡ ወዲያው ያቀረበው ጥያቄ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የጌታ ቃል፡ በገሃድ ለመድረሱ፡ ፍጹም ማስረጃ መኾኑ ነው። ደግሞም፡ ይህ ኢትዮጵያዊ፡ እግዚአብሔር እንደቃል ኪዳኑ፡ ለሚያምኑበት በሰጠው ጸጋ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ሲያያዝ የደረሰውንና ይዞት የኖረውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖቱን፡ አሁን፡ የራሱ፡ ኢትዮጵያዊ ወንድሙ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ባስገኘለት አዲስ ኪዳን አድሶና አጽንቶ ሊቀጥል የቻለው፡ በሰው ትምህርትና ኃይል ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነትና አጋዥነት መኾኑን፡ ይኸው ኹናቴ ያረጋግጣል።

ይህ እውነታ የማይታበል መኾኑንም፡ ያን የመሰለው የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሥራ፡ እንኳንስ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት፡ ከእግዚአብሔር ጋር ተሣሥረው ለኖሩት ኢትዮጵያውያን ቀርቶ፡ ለአሕዛብ ጭምር የተፈጸመላቸው መኾኑን፡ *"ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ኹሉ፡ ከተገረዙት ወገን የኾኑ ምእመናን፡ በአሕዛብ* (በእነቆርኔሌዎስ) *ላይ ደግሞ፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ!"* የሚለው የመጽሐፍ ቃል [፴፱] ያስረዳል።

# ኢትዮጵያ፡

እንዲህ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ለምልሞና አብቦ የኖረውን፡ "አቤሜሌክ" የተባለውን፡ የዚህን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ፡ ሕያው ሰውነት መድረክ አድርጎ፡ እግዚአብሔር፡ ለዘለዓለም ፍሬ ያበቃውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ከሐዋርያው ቶማስና ከአይሁድ ሃይማኖታውያን ምግባራት ጋር ሲያነጻጽሩት፡ በምንም መልኩ፡ ሊመዝኑት ያዳግታል፤ ይኹን እንጂ፡ እጅግ የራቀና የከፋ ከኾነው፡ ከአይሁድ ይልቅ፡ የቶማስ ሃይማኖት፡ የተሻለ ኾኖ ይገኛል።

"ታዲያ፥ እኔስ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን ቃል ኪዳን አክብሬ ፈጽሜአለሁ?"




ኪዳነ መልከ ጼዴቅ፤ (ሐተታው፡ በገጽ ፳፱-፴፩ ይገኛል።)

# ምዕራፍ ፫

## የመከራ ዘመናት እና መለኮታዊው ጥበቃ።

የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት፡ በተለይ፡ ክርስትና ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ ለፍጹምነት ደረጃው ከበቃበት ጊዜ አንሥቶ፡ በታላላቅ መከራዎች እየተፈተነ ኖርዋል፤ ይህም፡ በየዘመናቱ፡ የኢትዮጵያውያንን ሕይወት እያጥለቀለቀ ባለፈው ማዕበል፡ ተፈጽሞ ታይቷል። በእነዚያ፡ በመጀመሪያዎቹ የክርስትና መዋዕል ምዕት ዓመታት፡ በአገሪቱ ላይ፡ አልፎ አልፎ ይሰፍን በነበረው የክህደት ጊዜያት እንኳ፡ ኹሉንም ዓይነት ችግር ተቋቁሞና ከመጥፋት ድኖ፡ ይኸው፡ በህልውናው ሊቀጥል ችሏል።

ያን የመሰለውም፡ አሳዛኝ ብሔራዊ የጥፋት ቁጣ፡ እነሆ ዛሬ እንደገና ብቅ ብሎ፡ መዓቱን ሲያወርደው ይታያል። ይኸውም፡ በ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. "አልቦ እግዚአብሔር" በሚሉ፡ የጋርዮሽ አማኞች (communists ኮሚዩኒስቶች) መሪነት በፈነዳውና "አብዮት" በተባለው የዓመፅ ንቅናቄ፡ በተቋቋመው ፀረ ክርስቶስ መንግሥት ተከሥቶና አሁንም ማንነቱን በሌላ መልክ ለውጦ፡ ይኸው፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ ላይ እያወረደበት ያለው ታላቁ መከራ ነው። ያለፈው የኢትዮጵያ ዜና መዋዕል እንደሚያስረዳው፡ ይህን የመሰለው የዓመፅና የአገር ማፈራረስ ኹኔታ፡ እንዲህ ባሉ ከሃድያን መሪነት ሲደርስ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አካሎች የኾኑት፡ የሦስቱ ቤቶች፡ ማለትም፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ሥሉስ ኃላፊነት፡ ቀድሞ በብሉይ ኪዳኑ፡ "ሊቀ ካህናት"፥ ኋላ፡ በአዲስ ኪዳኑ፡ዘመነ ክርስትና፡ "ንቡረ እድ" በተባለውና በጊዜው "የአኵስም ጽዮን ባለመንበር" በኾነው፡ "የእግዚአብሔር ሹም" ሕያው ሰውነት ተጠብቆ ይቆያል።

### "ንቡረ እድ" ምንድር ነው?

"ንቡረ እድ" የሚለው የማዕርግ ስም፡ የመልከ ጼዴቅን የቃል ኪዳን በረከትና ጸጋ ለተቀበለና በ"አኵስም ጽዮን" ለሚሾም፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ በኢትዮጵያ ብቻ የሚሰጥ ነው። እርሱም፡ በመላው፥ በተለይም በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ ጭምር፡ መሰልና አቻ የሌለው ልዩ ኾኖ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ፥ ተከብሮና ተጠብቆ የኖረ፡ የቅዱሱ ኪዳን የትውፊት ቅርስ ነው።

ይኸው የማዕርግ ስም፡ ቃል በቃል ሲተረጐም፡ "እጅ መጫን" ማለት ሲኾን፡ በዚህ ማዕርግ የከበረው፡ ይህ ግለሰብ፡ በቀድሞው ጊዜ፡ የመላዋ ኢትዮጵያ ሊቀ ካህናት ወይም የመለኮታዊው መንግሥት፡ መንፈሳዊው ዘርፍ፡ የበላይ ኃላፊ በመኾኑ፡ እንዳስፈላጊነቱ፡ ተመርጠው በሚቀርቡለት፡ በበቁ እጩዎች ላይ "እጁን በመጫን"፡ በቅብዓ ክህነት እና/ወይም በቅብዓ ምልክና፡ ለሌሎች፡ የሥልጣን ሹመትን ይሰጥ ነበር። እርሱን ራሱን፡ መርጠውና ቀብተው ለመሾም፡ ከሦስቱ የመንግሥቱ ቤቶች ተወክለው የሚመጡት የመራጩ ምርፋቅ አባሎችም፡ እርሱን ይሾሙ የነበሩት፡ በዚሁ ሥርዓት፡ "እጆቻቸውን፡ በእርሱ ራስ ላይ በመጫን" ነበር። ስለዚህ፡ ትርጉሙ፡ "ራሱ፡ እጅ በማኖር የተሾመና እርሱም፡ ሌላውን፡ እጅ በማኖር የሚሾም"፥ በባዕዳኑ አጠራር፡ "ጳጳስ፥ ሊቀ ጳጳስ" ማለት ነው።

ኢትዮጵያውያን፡ ገና ከመጀመሪያው አንሥተው እስከሰባተኛው ባሉት ቃል ኪዳናት አማካይነት፡ በቀጥታ ከወረሷቸው ከሦስቱ የሥልጣን ሀብታት መካከል አንዱ፡ ክህነት ኾኖ ይገኛል። የቀሩት ኹለቱ ደግሞ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነትና ምልክና ናቸው። እነዚህ ሦስቱም የሥልጣን ሀብታት፡ ከእነርሱ ደርሰው ሊረከቧቸው የቻሉት፡ ራጉኤል የተባለውን ዮቶርን (የሙሴን አማት) በመሳሰሉት፡ የመልከ ጼዴቅ ተከታታይ ወራሾች በኩል፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉና እየተጠበቁ በመቆየታቸው ነው። እነዚህ የመልከ ጼዴቅ ወራሾች የተባሉት ግለሰቦች፡ ኹሉም፡ በዚያ፡ በኪዳኑ ልቦና የአምልኮ ዘመናቸው፡ ለኢትዮጵያዊነት የተቀደሰ ዓላማ፡ የድል ጀግኖችና የብረት ድልድዮች ኾነው አገልግለዋል።

ይህ የተቀደሰ ውርስ፡ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ከንግሥት ማከዳ ደርሶ፡ በእርሷ ዘመን፡ የቤተ ክህነቱ ባለመንበር የነበረው፡ ኢትዮጵያዊው ሊቀ ካህናት ተረከበው። በዘመኗም፡ ልጇ፡ ቀዳማዊ ምኒልክ፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት የኾነችውን "ታቦተ ጽዮን"ን አስይዞ፡ ወደኢትዮጵያ በገባ ጊዜ፡ ከሌሎቹ የእስራኤል የበኵር ልጆች ጋር አብሮት የመጣውና ለኢትዮጵያዊነት የበቃው፡ ሊቀ ካህናቱ አዛርያስም፡ በኪዳኑ አሪቱ የተጠናከረው፡ የዚሁ ኢትዮጵያዊ ውርስ ተካፋይ ኾነ። እነዚህ ሊቃነ ካህናት፡ ኹለቱም፡ የኪዳኑ አሪቱ ዘመን፡ ገና ከተወጠነበት ጊዜ አንሥተው፡ ለዚያው፡ ለተረከቡት፡ የኢትዮጵያዊነት የተቀደሰ ዓላማ፡ ከቀደሙት ጋር የተመሳሰለውን አገልግሎታቸውን አበርክተዋል።

በመጨረሻ፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ "አቤሜሌክ" መንፈስ ቅዱስ ጠርቶ በላከው በፊልጶስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ፡ ወዲያው፡ በእርሱ ሰውነት፡ ይኸው፡ የተቀደሰው ሕያው ውርስ፡ በአዲስ ኪዳኑ ቅዱስ መንፈስ ታድሶ፡ የትንሣኤ ሕይወትን አገኘ! በእነዚያ በቀደሙት፡ የአዲስ ኪዳን ዓመታት ውስጥ፡ እንዲህ፡ በክርስትና እምነት ጸድቆና ለምልሞ፡ በኢትዮጵያ መስፋፋት ከጀመረ በኋላም፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባና ተከታትለው በተነሡት ትውልዶች አማካይነት እየተላለፈ፡ እነሆ፡ ከኢትዮጵያዊው ሊቀ ካህናት፡ ከእንበረም ደረሰ። እንበረም የተባለው፡ ይህ ጻድቅ፡ በአራተኛው ምዕት ዓመታተ ምሕረት፡ በአኵስም ጽዮን መንበር ላይ ተቀምጦ፡ "ንቡረ እድ"፡ ማለትም፡ የኢትዮጵያ ሊቀ ካህናት በመኾን፡ ተልእኮውን የፈጸመ። በዚህ ሥልጣኑም፡ በክርስትና እምነት የተረከበውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሕያው ውርስ፡ በእውነት በማገልገል፡ በበኩሉ ያለውን የኃላፊነት ከፍተኛ ድርሻ፡ በተለየ ጥሪ ያከናወነ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር የተመደበ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነበር። እንግዴህ፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ "አቤሜሌክ" እና የአኵሱሙ ንቡረ እድ፡ እንበረም፡ በአዲሱ ኪዳን የክርስትና እምነት፡ ለፍጹምነት የበቃውን፡ ይህን የኢትዮጵያዊነት ሕያው ዓላማ፡ በላቀ ታማኝነት በማገልገል፡ ግዳጃቸውን የፈጸሙ፡ የኢትዮጵያ እውነተኞች ልጆች ኾነው ይኖራሉ።

ንቡረ እዱ ከሚያከናውናቸው፡ ከሦስቱ የኃላፊነት ተግባሮቹ፡ ማለትም፡ ከቤተ ሕዝቡና ከቤተ ምልክናው ጋር አንዱ የኾነው፡ ክህነታዊ ሥልጣኑን በሥራ ላይ የሚያውልበት፡ የቤተ ክህነቱ ተልእኮው፡ በዚህ መንበሩ ላይ ተጠቃልሎ ይገኛል። ይህም፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በዓለም አቀፉ ቤተ ክርስቲያን፡ የአገልግሎት እርከን፡ ጳጳስ፥ ሊቀ ጳጳሳት ወይም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓትሪያርክ) እየተባሉ የሚጠሩት፡ መንፈሳውያን ባለማዕርጎች፡ ከሚፈጽሙት ጋር ይመሳሰላል።

በእንበረም ተጠብቆና ጸንቶ የቀጠለው፡ ይህ፡ "ንቡረ እድ ዘአኵስም ጽዮን" የሚለው የማዕርግ ስም፡ ለኢትዮጵያ ሊቀ ካህናት፡ ብቸኛ መታወቂያ የመኾኑ ነገር፡ እነሆ÷ ኹለት አማናውያን ፍሬዎችን አስገኝቶለታል፡፡

ከእነዚህም፡ የመዠመሪያው ፍሬ፡ መንበሩ፡ በአኵስም የኾነው፡ የኢትዮጵያው ሊቀ ካህናት፡ በአዲሱ ኪዳን ዘመነ ምሕረት ታድሶ የተሰጠውን አጠቃላይ የኃላፊነት ተግባር፡ የጠላት ኃይላት በሠለጠኑባቸው ጊዜያት እንኳ ሳይቀር፡ አቀነባብሮ ለመሸከም÷ በሕያውነት አቀይቶ ለማስተላለፍና በሥራ ላይ አውሎ ለመፈጸም ይችል ዘንድ፡ ከላይ በተገለጠው መልክ፡ የመንበሩ ሥልጣን ተስተካክሎ እንዲጠናከርለት ያደረገ በመኾኑ ነው፡፡

ኹለተኛው ፍሬ፡ ጥንታዊትና ኪዳናዊት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ ማለትም፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ በአቤሜሌክ፡ ወደክርስትና ከተሸጋገረች የቆየችው የብሉዩ ኪዳናት ቤተ ክህነት፡ በዕድገቷ ረገድ ያከናወነችው ጉዞ፡ ከምልዓት ደርሶ፡ የማንነቷ አቋም፡ በአዲሱ ኪዳን፡ ለፍጹምነት ደረጃ መብቃቱ የተረጋገጠበት መኾኑ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው፡ የንቡረ እዱን መንበር፡ ከሌሎቹ ኹሉ ፈጽሞ የተለየ የሚያደርገው፡ ብቸኛ ባሕርይ አለው፤ ይኸውም፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" የመኾኗን እውነታ፡ በአነስተኛ መጠን አግዝፎ በማቆየት፡ የሦስቱ ቤቶች፡ ማለትም፡ የቤተ ሕዝቡ÷ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ሥሉስ ኃላፊነቶች፡ በአንድነት ተዋህደውና በተሟላ ይዞታ ተጠብቀው የተገለጹበት አካል መኾኑ ነው፡፡ ይህም ኹኔታ፡ ምንጊዜም፡ ሕያው ኾኖ ኖርዋል፤ ዛሬም፡ በገሃድ የታወቀ ኾኖ እየሠራ ይገኛል፡፡

የመለኮታዊው መንግሥት ሦስት ቤቶች ሥሉስ ሥልጣናት፡ እንዲህ፡ በአንዱ፡ የንቡረ እድ ሰውነት ተዋህደውና የእርሱ ሀብታት ኾነው፡ በእርሱ እንዲሠራባቸው የሚያደርገው ሥርዓት፡ በዚህ መልክ፡ ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰው ትውፊት፡ እስካሁን ተጠብቆና ጸንቶ ተገኝቷል፤ ይህንኑም፡ ለአያሌ ምዕት ዓመታት፡ በቋሚ ምልክትነት ጸንቶ ሲያገለግል የኖረውና ህልውናውን ዛሬም የቀጠለው፡ ይኸው የንቡረ እዱ መንበር ያረጋግጣል፡፡ ለዚህ እውነታ፡ ባሁኑ ሰዓት እየደረሰ ያለው ዘመነ ዐጸባ (የመከራ ዘመን) እስከተከሠተበት ጊዜ ድረስ፡ ከቤተ ሕዝቡ÷ ከቤተ ክህነቱም ኾነ ከቤተ ምልክናው፡ ማንም ሹም የማይገባበትና ነጻ በኾነ በንቡረ እዱ ሥልጣን ብቻ የሚተዳደር አውራጃ፡ በአኵስምና በዙርያዋ ክልል መኖሩ፡ የሚበቃ ማስረጃ ነው፡፡

በኢትዮጵያ፡ በተለይ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተቃዋሚው ወገን፡ የገዢነትን ሥልጣን፡ በኃይል በሚይዝባቸው የችግር ዘመናት፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ሥርዓት፡ ማለትም፡ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው አቋም፡ በሕያውነት ለመቀጠሉ፡ መተማመኛ ይኾን ዘንድ፡ ይህ፡ የንቡረ እዱ መንበር መኖር፡ ያለው አስፈላጊነት፡ እጅግ የላቀ መኾኑ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ፡ የመንበሩ ህልውና፡ በተቃዋሚዎቹ ኃይል ሳይወገድ፡ እንደነበረ እንዲቀጥል ለማድረግ በመቻሉ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ምስጋናውን ለፈጣሪው ከማቅረብ ጋር፡ ይኸው መንበር፡ እንዳይጠፋ፡ ምንጊዜም እውቅና ሰጥቶ፡ በአክብሮት ሲጠብቀው እነሆ ይታያል፡፡

አልፎ አልፎ፡ የአጼው ዙፋን፡ ባዶ በኾነባቸው፥ ወይም፡ የዘውዱ ሥልጣን፡ በዓመፀኞች ከሃድያን እጅ በወደቀባቸውና ዛሬ፡ በገሃድ እንደሚታየው ኹሉ፡ አገሪቱ፡ በአጠቃላይ፡ በከህደት መርገም ውስጥ በተዘፈቀችባቸው፡ በእነዚያ አሥጊና የችግር ጊዜያት፡ በመንበሩ በተቀመጠው፡ የዘመኑ ንቡረ እድ ሰውነት፡ ሕያው ኾና ተገልጻ፡ ተግባርዋን የምትፈጽመው፡ በኢትዮጵያ የሰፈነችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በዚህ መለኮታዊ ጥበብና ጸጋ አማካይነት፡ ህልውናዋን ለመቀጠልና ቢያንስ ቢያንስ፡ በመንፈሳዊው በኩል ያለውን ግዳጇን ለማካኼድ እንድትችል መደረጉን፡ በቀላሉ መመልከት፡ ለማንም አያዳግትም፡፡

"አልቦ እግዚአብሔር" በሚል የሰነፎች እምነት፡ ለቅጣትና ለጥፋት ተነሥቶ የነበረው፡ "ደርግ" የተባለው፡ አብዮታዊ የጦር ኃይሎች መንግሥት፡ በሥልጣን ዘመኑ ሣለ፡ በመጀመሪያዎቹ ባለሥልጣኖች እሥረኞቹ ላይ፡ በግፍ ከፈጸመው ግድያ የተረፈው፡ የመጨረሻው ንቡረ እድ፡ በሕይወተ ሥጋ ቆይቶ፡ ከእሥራት ለመፈታት መብቃቱ፥ ባሁኑ ጊዜም፡ ይህን የምስክርነት ቃል፡ ለሕዝብ በይፋ በመስጠትና የዚህን መጽሐፍ መልእክት፡ ለሚመለከታቸው ኹሉ በማድረስ፡ ሊፈጽመው በቁርጥ ተነሣሥቶበት የነበረውን ተልእኮውን ለማከናወን መቻሉ፡ ከላይ ለተብራራው፡ ለመለኮታዊው የቸርነት ጸጋ፡ ፍጹም እውንነትና ጽኑ አስተማማኝነት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከነእናቱ፡ የተመሰገነ ይኹንና! በቂ ማረጋገጫ ኾኖ ሊቀርብ ይቻላል፡፡

ይህ፡ መለኮታዊ፡ የቸርነት ጸጋ፡ ለአኵሱሙ ንቡረ እድ ብቻ ተወስኖ ወይም ተመድቦ የተሰጠ አይደለም፤ ነገር ግን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው፡ የዘለዓለም ደኅንነት አማካይነት፡ እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ወይም እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን ጭምር፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በፍጹም ተድላ ደስታ፡ ይሳተፍበት ዘንድ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ለኹሉ የተሰጠ የሕይወት ጸጋ ነው እንጂ፡፡

ጥንታዊው፡ የኢትዮጵያ ዜና መዋዕል እንደሚያዘክረው፡ የአጼው ሥርዓት፡ ወደቀደመ ህልውናው ተመልሶ፡ የመለኮታዊቷ መንግሥት አመራር፡ እንደገና፡ በአግባብና በገሃድ በሚካሄድበት ጊዜ፡ ንቡረ እዱ፡ በሦስቱም የመንግሥቱ ቤቶች ላይ ይዞት የቆየው ሥሉስ ሥልጣን፡ በአኵስም አውራጃው ብቻ ይወሰንና በዚህ ረገድ፡ በመላዋ አገሪቱ ላይ ሰፍኖ የነበረው ብሔራዊው የሥልጣን ባለአደራነቱ፡ ያለአንዳች ርክክብ፡ ወዲያው፡ በዙፋኑ ላይ ወደተቀመጠው፡ ወደአዲሱ አጼ ይተላለፋል፡፡

ይኹን እንጂ፡ የኋላ ኋላ፡ ቤተ ክህነቱን እንዲወክል የተደረገው፡ "ሐፄጌ" ወይም "አጼጌ"፡ ማለትም፡ በመንፈሳዊ ሥልጣኑና ክብሩ ምክንያት፡ ከአጼው ጐን የመቀመጥ መብት ያለው፡ ኢትዮጵያዊው "እጨጌ" የተባለው ባለማዕርግ በማይኖርበት ጊዜ፡ የአኵስሙ ንቡረ እድ፡ ከላይ ከተጠቀሱት፡ የእርሱ፡ የብቻው ከኾኑት ሥልጣናት ጋር፡ በተጨማሪ፡ የእጨጌውን ነጠላ ሥልጣን ብቻ በብሔራዊ ደረጃ፡ ይዞ ይሠራል፡፡

የአገሪቱ መናገሻ ከተማ፡ ከአኵስም ወደሌሎቹ የታወቁ፡ ጊዜያዊና ቋሚ ቦታዎች በተዘዋወረባቸው፡ በኋለኞቹ ዘመናት፡ ኹለት መንበሮች እንዲኖሩ ያደረገው ትውፊት፡ በመለኮታዊቷ መንግሥት ውስጥ ተመሠረተ፤ ይኸውም፡ አንዱ መንበር፡ በአኵስም ለሚቀመጠው የንቡረ እዱ ሲኾን፥ ኹለተኛው ደግሞ፡ በማናቸውም ጊዜና ኹኔታ፡ ከአጼው ሳይለይ፡ እርሱን አጅቦ፡ ከቦታ ወደቦታ የሚዘዋወረው፡ የእጨጌው ነው፡፡

## አኲስምና ዜናዋ::

"አኲሽም"፡ ቃሉ ሲተነተን፡ "አ"፡ መጀመሪያ፥ ጥንት፥ ርእስ ማለት ሲኾን፡ "ኲሽም" ደግሞ፡ ኹሻውያን፥ የኲሽ ልጆች፥ ሕዝበ ኲሽ፥ ነገደ ኲሽ ማለት ስለኾነ፡ አጠቃላይ ስሙ፡ ጥንታዊት፥ ቀዳማዊት፡ የኩሻውያን (የኢትዮጵያውያን) መዲና (ዋና ከተማ) ማለት ነው::

አኲስም፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በሰብአዊ ጥበብ አቋሟና ይዞታዋ ረገድ፡ የቀደመ ገናንነትዋ የማይታይባት፥ በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል የምትገኝ፡ ትንሽ ከተማ ናት:: በግዘፍ ኹለንተናዋ፡ እንዲህ ትኹን እንጂ፡ በመንፈሳዊው አቋሟና ህልውናዋ ረገድ፡ ካለፈውም ኾነ ከዛሬው ዜና መዋዕሏ አኳያ፡ ያለችበት እውነተኛ ገጽታ፡ በሃይማኖት ዓይን ሲታይ፡ የዚህ ተቃራኒው ኾኖ ይገኛል፤ ይኸውም፡ በተለይ፡ ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከተው ሕያው ትውፊት፡ አኲስም፡ ይዛው የኖረችው፥ ዛሬ የያዘችውና ለወደፊቱም የምትይዘው ሥፍራ፡ ያው የነበረውን፥ ያለውንና የሚኖረውን ታላቅነቷንና ገናንነቷን የሚያንጸባርቀው ነው::

ኢትዮጵያ፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር ሃይማኖቷ፡ "አሓዱ አምላክ" በሚለው፡ የኪዳን ልቦና መሠረት ላይ ተወጥኖ፡ ዕድገቱ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ህልውናዋ ዘመን ኹሉ፡ አኲስም፡ የአገሪቱ መናገሻ ከተማነቷንና የመለኮታዊቷ መንግሥት መዲናነቷን እንደያዘች ቀይታለች:: ይኸው ማዕርጓ፡ ኋላ፡ በኪዳኑ አሪቱ ዘመን፡ ወደኹለተኛው ደረጃ ከፍ ሲል፡ በፍጻሜው ደግሞ፡ በዘመነ ክርስትና፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ ለመጨረሻው ክብር ሊበቃ ችሏል፤ ይኸውም፡ አገሪቱ ለቀመችበት፡ ለእግዚአብሔር አምልኮት፡ በመካከሏ የታነፀው፡ የመጀመሪያው፡ የኪዳኑ ልቦና ቤተ መቅደስ፡ በቅድሚያ፡ ወደቃል ኪዳኑ ታቦት ማደሪያነት፥ ተከታትሎም፡ ወደቅድስት ማርያም ጽዮን ቤተ ክርስቲያንነት በማደግ፡ ክልሏን፡ "ዙርያው እሳት" ማዕከሏንም፡ "መኻሉ ገነት" ለማሰኘት በመቻሉ ነው:: አኲስም፡ እንዲህ እንደመኾኗ፡ በኢትዮጵያ፡ ጸንታ ለኖረችው ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ ብሔራዊ ማዕከል፥ ይህም ማለት፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና ለተባሉት፡ ለዚችው መንግሥት፡ ሦስት ዘርፎች ውኅደት፡ ምልክት ኾና ኖራለች::

ከላይ እንደተብራራው፡ ይህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕያው ውርስ፡ ከሃድያንና ዓመፀኞች በሠለጠኑባቸው ጊዜያት ሳይቀር፡ በግዙፍ እና/ወይም በመንፈሳዊ ባሕርዩ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተሳለፈ፡ ለዘመናት ተጠብቆ ሊኖር የቻለው፡ በዘመነ ብሉይ ኪዳን፡ በኢትዮጵያዊው ሊቀ ካህናት፥ በዘመነ ሐዲስ ኪዳን ደግሞ፡ በአኲስም ጽዮኑ ንቡረ እድ እና/ወይም በእጨጌው መንበር አማካይነት ነበር::

ዳሩ ግን፡ ይህን የመሰለው ጥንታዊ ትውፊት፡ "ህልውናው፡ እንግዴህ ደግሞ ሊያበቃ ይኾን?" ተብሎ የተሠጋበት ሰዓት፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደርሶ ሲካሄድ፡ እነሆ ይታያል:: ይኸውም፡ ባዕድ በኾነውና "አልቦ እግዚአብሔር" በሚለው፡ የጋርዮሽ ፍልስፍና የተመራው፡ የደርግ ወታደራዊ መንግሥት፡ በኢትዮጵያ የኖረውን፡ መለኮታዊዉን የዘውድ አስተዳደር፡ በዓመፅ ተክቶ፡ ሥልጣን ከያዘበትና የክህደቱን አገዛዝ፡ በአገሪቱ ላይ በይፋ ካወጀበት፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. አንሥቶ፡ እየተፈጸመ ያለው ድርጊት ነው::

## ኢትዮጵያዊው እንበረም፡፡

ኢትዮጵያውያን፡ ለቃል ኪዳን አምላካቸው፡ ያላቸውን የታማኝነት ግዳጅ በመፈጸም ረገድ፡ እጅግ ከፉና መራራ የኾነው የዓመፀኞች የክህደት አገዛዝ በሠለጠኑባቸው ዘመናት እንኳ ሳይቀር፡ ያሳዩት የማይበገር ጽናት፡ አዲስ የተቀበሉትን የክርስትና ቃል ኪዳን፡ በጠለቀና በተጠናከረ ኹኔታ ጠብቀው ለማቆየት ብቻ ሳይኾን፡ ከትውልድ ወደትውልድ፡ በሕያውነት ለማስተላለፍ ጭምር እንዲችሉ አድርጓቸዋል፡፡

ይህ ደገኛ አዝማሚያ፡ በልዩ ልዩ ፍሬያማ መንገዶች፡ በበለጠ እየጐለበተ፡ ዕድገቱን ቀጠለ፡፡ ይህም የኾነው፡ ምንጊዜም፡ ከኢትዮጵያውያን ያልተለየው መንፈስ ቅዱስ፡ የተለመደ የቸርነቱን ጸጋ ስላላቋረጠባቸው ነበር፡፡ ከእነዚህ የዕድገት ፍሬዎች መካከል፡ ጉልህ ከኾኑት ጥቂቶቹ፡ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል፡፡

በዚያን ጊዜ፡ ቀዳሚ ኾኖ የተገኘው ተግባር፡ በተለይ፡ ቤተ ክህነቱን በሚመለከት ጉዳይ፡ ኢትዮጵያውያን ልኡካንን፡ ከቅድስቲቱ መዲና፡ ከአኵስም፡ በመካከለኛው ምሥራቅ ወደሚገኙት፡ ወደአዲሶቹ አብያተ ክርስቲያናት መላክ ሲኾን፡ ይህም ግዳጅ የተፈጸመው፡ በዘመኑ፡ የኢትዮጵያ ሊቀ ካህናት፡ ወይም የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ በነበረው፡ በኢትዮጵያዊው "እንበረም" ፈቃድና ትእዛዝ ነበር፡፡ እኒህ ልኡካን፡ ጉዟቸውን፡ ወደኢየሩሳሌምና ወደሌሎቹ የመካከለኛው ምሥራቅ አህጉር ሳይቀጥሉ፡ በግብፅ ብቻ እንዲወሰን ካደረጉ በኋላ፡ ተልእኳቸውን፡ በዚያው ፈጽመው፡ ወደአገራቸው ተመልሰዋል፡፡ ሲመለሱም፡ የተቀበላቸው፡ አስቀድሞ የላካቸው፡ ያው፡ ሊቀ ካህናቱ እንበረም ነበር፡፡

እንደሚታወቀው፡ ኢትዮጵያ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በቅዱሱ ኪዳን ተመሥርቶ የኖረውን፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር እምነቷንና ሥርዓቷን፡ ከሌሎቹ ኹሉ ቀድማና በክርስትና ጥምቀት አጽንታ ሣለች፡ ነገር ግን፡ እስከዚያን ጊዜ ድረስ፡ ገና፡ ወደእርሷ ሳይደርሱ የዘገዩባት፡ ምሥጢረ ቁርባንን የመሰሉ፡ አንዳንድ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ፡፡ ምሥጢረ ቁርባኑንም ቢኾን፡ ኢትዮጵያ፡ በኪዳኑ መልከ ጼዴቅ፡ የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዓ በረከት መሥዋዕቷ አማካይነት፡ ጠብቃ ስትሠራበት ስለኖረች፡ ይኸው፡ ምሥጢረ ቁርባኑ፡ ለእርሷ፡ እንግዳ ሥርዓት ሊኾንባት አልቻለም፤ ይኹን እንጂ፡ ከጣዖት አምልኮ፡ ወደአምልኮተ እግዚአብሔር፡ ማለትም፡ ከአረማዊነት፡ በቀጥታ ወደክርስቲያንነት የገቡት፡ ግብፃውያንን የመሰሉት ወገኖችና በዚሁ፡ የክርስትና ሃይማኖት ተመሥርተው፡ መኰኼድ የጀመሩት፡ አዲሶቹ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት፡ እነዚያን ምሥጢራት፡ በአዲሱ ኪዳን ሥርዓት፡ ሲሠሩባቸው ስላገኟቸው፡ ኢትዮጵያውያኑ ልኡካን፡ እነዚሁኑ፡ ይዘው ለመመለስ ችለዋል፡፡

"የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድ" በሚል ማዕርግ የከበረው "እንበረም"፡ ልኡካኑ፡ ከግብፅ ይዘዋቸው የመጡትን፡ መልካም የኾኑትን ነገሮች ኹሉ፡ በሊቀ ካህናትነቱ ሥልጣን፡ ቡራኬውን ሰጥቶ ስላጸደቃቸው፡ በኢትዮጵያ፡ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን አግኝተው ኖረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡ በአዲሲቱ የዓለም ቤተ ክርስቲያን የማዕርግ እርከን ውስጥ፡ ከእርሱ ሥልጣነ ክህነት ጋር ተወዳዳሪ እንዲኾን ታስቦ፡ ወደኢትዮጵያ የገባው፡ "ጳጳስና" የተባለው፡ ከፍተኛው የባዕዳን የክህነት ሥልጣን፡ አንዱ ነው፡፡

## የዓለሙ መፋረጃ!

ይህን: ባዕድ የኾነውን: የሹመት ማዕርግ ይዞ የተመለሰው ሰው: በዘሩ: የሶርያ ተወላጅ የነበረው፥ በሶርያዊ ስሙም: ፍሬምናጦስ የተባለው ሰው መኾኑ አይዘነጋም:: እርሱም: ገና በልጅነት ዕድሜው: እግዚአብሔር በሚያውቀውና ባዘጋጀው: ባልታሰበ አደጋ ምክንያት: ወደኢትዮጵያ መጥቶ: በመኖሩ: የኢትዮጵያዊነትን ጸጋ ተቀብሎ: "እውነተኛ ኢትዮጵያዊ" ኾኗል ብሎ በማመን: ኢትዮጵያዊው ሊቀ ካህናት: እንበረም: ታማኝ መልእክተኛው አድርጎ ወደግብፅ እንደላከው፥ ከዚህም የተነሣ: ኢትዮጵያውያን: "ሰላማ" የሚል ስያሜ እንደሰጡት ይታወሳል::

ይህ: "ጵጵስና" የተባለው: የባዕዳን መንፈሳዊ ሹመትና ሥልጣን: በዚህ መልክ: ወደኢትዮጵያ እንዲገባ የተደረገው: በሰብአዊ ዕቅድ: ኾን ተብሎ: ለተንኰል መኾኑን ለመገንዘብ: ለሊቀ ካህናቱ እንበረም: ረዥም ጊዜ አልፈጀበትም:: ጠንቁ: የኋላ ኋላ የተከሠተው ይህ ደባ: "እጨጌ" የሚለውን: የቤተ ክህነት የማዕርግ ስምና "ንቡረ እድ" የሚለውን: የአኵስም ጽዮንን በትረ ሥልጣን አጣምሮ በያዘው: በእርሱ: በኢትዮጵያዊው ሊቀ ካህናት ላይ ተፎካካሪ የኾነ: ሌላ ባዕድ ባላንጣን በማስቀመጥ: የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው ኢትዮጵያ: መጀመሪያ: ቅሬታን፥ ቀጥሎ: ክርክርን፥ ከዚያ ፀብን፥ በመጨረሻም: ሁከትን ለመፍጠር መኾኑን ተረዳው:: ስለዚህ: ለእርሱ: የንቡረ እድነቱን መንበር ብቻ አስቀርቶ: እስከዚያን ጊዜ ድረስ: የእርሱ: የነበረውን "እጨጌነቱን": ለጊዜው: በፈቃዱ: ለአዲሱ "ጳጳስ" በመስጠት: ችግሩን: በትህትና፥ በትእግሥትና በጥበብ አስወገደው::

ይኹን እንጂ: ይህን በመሰለው ኢትዮጵያዊ መንገድ: እንዲህ ተስተካክሎ: ሥርዓት እንዲይዝ የተደረገው: የሥልጣን ክፍፍልና ድልድል: እንደጸና ሊቀጥልም ከቶ አልቻለም:: ቀጥሎ ባለው ሐተታ ተብራርቶ እንደሚነበበው: ይህ ክፍፍልና ድልድል: ከጊዜ በኋላ: በባዕዳን ኃይል: ከውጭ በሠረገ ጣልቃ ገብነትና የግል ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ: ከውስጥ ኾነው: ሥውር ተባባሪነታቸውን: ለባዕዳኑ ባበረከቱ የአገር ተወላጆች ሴራ ተቃወሰ፤ በሌላ ጠንቀኛ ልማድ፥ ይኸውም: የኢትዮጵያዊነት ባሕርይ በሌለው ባዕድ ሥርዓት እንዲተካ ተደረገ:: ይህ ሙከራና ተግባር: የድርጊቱ እጅግ አሳዛኝና አስከፊ፥ አሳፋሪም ገጽታው ነበር ማለት ይቻላል::

ይኹን እንጂ: ኢትዮጵያውያን: ከጊዜ በኋላ: የእጨጌነቱን መንበር: ለራሳቸው መልሰው ይዘው፥ የጵጵስናውን ሹመትና አጼውን የመቀባት መብታቸውን: ያጠቃለለውን: ክህነታዊ ሥልጣን ግን: ለግብፃዊው ጳጳስ ትተው: ህልውናቸውን ቢቀጥሉም: ባልተቋረጠ ገድል ጭምር: ወደፈጣሪያቸው ሲያቀርቡት የኖሩት የልመና ጸሎታቸው መልስ አግኝቶ: ባለፉት ቅርብ ዓመታት ውስጥ: የዚህ ኹሉ ችግራቸው መንሥዔ የነበረው የተፅዕኖ ኃይል: በመለኮታዊው ውሳኔ ስለተወገደላቸው: የቅዱሱ ኪዳን ፍጹም በረከት ተካፋዮች መኾናቸውን አረጋግጠዋል:: ይኸውም: የባዕዳኑ የጵጵስና ክብር፥ ሥልጣንና ሢመት: ወደነበረበት: ወደኢትዮጵያዊው እጨጌ እንዲመለስ የማድረጉ ትግላቸው ተፈጽሞ: በመጨረሻ የድሉን አክሊል ለመቀዳጀት በመቻላቸው ነው::

## ከዔዛናና ሳይዛና:
## ወደአብርሃ ወአጽብሐ::

በእንበረም የሥልጣን ዘመን ከተፈጸሙ ታላላቅ ቁም ነገሮች መካከል: ቀዳሚ ኾኖ የሚወሳው: ከስመ ጥሩዎቹ: አብርሃ ወአጽብሐ: ኢትዮጵያውያን አጼዎች ጋር የተያያዘው ዜና መዋዕሉ ነው::

በዚያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ትውልድ: እንደዛሬው ኹሉ: በቅዱሱ ኪዳን ላይ ያደረሰው: የክህደትና የዓመፅ ኃጢአት: ጽዋው ስለሞላ: ከዚያ የተነሣ: መለኮታዊውን የዘውድ አስተዳደር እስከማጣት ደርሶ: የመሪነቱን ሥልጣን: "ዔዛናና ሳይዛና" እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት አረማውያን: በኃይል ይዘውና በቦታው ተተክተው ይገዙት ነበር::

እነርሱም: በእውነተኛው መምህር: በእንበረም አማካይነት: ስለክርስትና ሃይማኖት፥ ምግባርና ሥርዓት: በትክክል አውቀውና በዝርዝር ተረድተው: ይህንኑ: የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት: በሥርዓተ ጥምቀት ከተቀበሉ በኋላ: ቅዱሱን ቅብዓት ተቀብተውና በመንበረ ዳዊቱ ዙፋን ላይ ለመቀመጥ በቅተው: በአጼነት ማዕርግ: መንግሥታዊ ሥልጣናቸውን: በበለጠ ሥጋዊ ልዕልናና መንፈሳዊ ኃይል ሊሠሩበት ቀጠሉ!

በትውልዱ ላይ የታዘዘውን የቅጣት ፍርድ ለመፈጸም ; ቀድሞ በአረማዊ ገዢነት ተልከው የነበሩት፥ ኋላ ግን: በክርስትና ስማቸው: "አብርሃ ወአጽብሐ" ተብለው የተሠየሙት እኒህ: አዲሶቹ አጼዎች: በኢትዮጵያዊነታቸው እንዲህ አድርገው: የእግዚአብሔርን ልጅነት በማግኘታቸው: የቅዱሱን ኪዳን የክርስትና ሃይማኖት: ወደነበረበት: ብሔራዊነቱ: በአዋጅ መልሰውታል:: ይህን የመሰለውም: ግዝፈት ያለው: ብሔራዊ ሙያቸው: ኢትዮጵያዊነት: በውስጥና በቅርብ ከነበሩት ከክልሉ ወገኖች አልፎና ተርፎ: በአካባቢና በአፍአ በነበሩት ዘንድ ሳይቀር: በበለጠ እንዲስፋፋና እንዲያድግ ለማድረግ የነበረውን ዕድል: እጅግ አጠናክሮለታል! አፋጥኖለታልም::

ይኹን እንጂ: በዚያን ዘመን የተከናወነውና በመልካም ሲዘከር የሚኖረው: ያን የመሰለው: ፍሬያማ ተግባር: በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ገድል የተገኘ መኾኑ ታውቆ: ለእግዚአብሔር ገናና ክብር ሊሰጥበት የሚገባ ሲኾን: ኢትዮጵያውያን ያልኾኑ: ነገር ግን: "የሃይማኖት ወገኖች ነን" የሚሉ ባዕዳኑ ግብፃውያን: በተንኰል ዓላማ ተነሣሥተው: ለራሳቸው ዝናና ጥቅም ማዳበሪያ ሲሉ: የእግዚአብሔርን እውነት: በዲያብሎስ ሐሰት ሊለውጡት ሲሞክሩ መመልከቱ: በብርቱ ያሳዝናል! ያስተዛዝባልም::

## ኢትዮጵያ:
## የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን
## ስትፋረድ!

ኢትዮጵያውያን ባልኾኑት: በእነዚያ ባዕዳን ግብፃውያን: (የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጳጳሳት) በግልጽና በግዘፍ የተፈጸሙት: የስሕተትና የጥፋት በደሎች: ምንነታቸውን: ራሳቸው የሚናገሩ ስለኾኑ: ጥቂቶቹ ከዚህ እንደሚከተለው ሠፍረዋል::

## ሐሳዊው ይትበሃልና "ኦርቶዶክስ" የሚለው ቃል ጠንቅ!

በቅዱሱ ኪዳን ጸንታ የኖረችው: ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ: ቀደም ብላ: ከኪዳነ ልቦና ወደኪዳነ ኦሪት ተሸጋግራ ከቆየችበት እምነቷ: ለክርስትና እምነት የበቃችው: ከክርስቶስ ልደት በኋላ: ዓርባ ዓመት እንኳ ሳይሞላ መኾኑ እየታወቀ: በወንጌል ያመነችውና ቤተ ክህነቷ: "ቤተ ክርስቲያን" ተብላ: እንደአዲስ የተቋቋመችው: ከክርስቶስ ልደት በኋላ: በአራተኛው ምዕት ዓመታት እንደኾነ የሚያስመስል: የሐሰት ይትበሃል ሠርጎ እንዲገባ ተደርጓል:: ይህ ታላቅ ስሕተት: እንደእውነት ተቆጥሮ: የመጨረሻው የዘውድ ባለአደራ በነበሩት: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በተጻፈው ሕገ መንግሥት ውስጥ: አንቀጽ ይዞ በጽሑፍ መሥፈሩ: እውነተኞች ኢትዮጵያውያንን: በይበልጥ ሳያስገርምና ሳያሳዝን እንዳልቀረ: እሙን ነው:: እንዲህ ያለውን የፈጠራ ሥራ: አጠቃልሎ ይዞ የነበረው: ያ: ሰው ሠራሽ ሕንፃ: ቋሚነት ያለው መስሎ እንዲታይ ለማድረግ: በዚያ የብልጠት መልክ እየተገነባ እንዲቆይ ቢሞከርም: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ: አገሪቱን: ድንገት ደርሶ ባጥለቀለቃት የቁጣና የቅጣት ማዕበል ተመትቶ: ከመሠረቱ በፈራረሰ ጊዜ: እነሆ ሕንፃው ብቻ ሳይኾን: በውስጡ የተከማቸውን የሰውና የመሣሪያ ሀብት፥ ጥበብና ኃይል ጭምር እንደያዘ: አብሮ ተደምስሷል!

"Coptic" "ኮፕቲክ" እና "Orthodox" "ኦርቶዶክስ" የተባሉት የግብፅና የግሪክ የሃይማኖት መለያ ቃላት: "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" በሚለው፥ መደበኛ በኾነውና በታወቀው ስያሜ መኻል: ተቀጽላ ኾነው እንዲገቡ: ወይም ያንን ስም እንዲተኩ ተደርጓል:: ይኸውም: "የኢትዮጵያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን" ወይም "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን" የሚለው አጠራር ነው::

ይህ አጠራር: የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ "የግብፅ ወይም የኦርቶዶክሳውያን: ማለትም: የግብፅ ወይም: የግሪክ: ከኹለቱ: የአንደኛቸው: ቅጂ" መኾኗን ለማረጋገጥና ባዕድ የኾነውን የግል ዓላማ: በቀላሉ ከግብ ለማድረስ እንዲያመች: ኾን ተብሎ በዕቅድ የተደረገ መኾኑ ግልጽ ነው:: ከዚህ ድርጊት: የተነሣ: በቅዱሱ ኪዳን ጸንታ: ለዝንተዓለም በኖረችው: በቀዳማዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ላይ: የእውነተኛ ማንነቷን፥ የህልውና ዕድሜዋንና የምሥጢረ ሃይማኖቷን መሠረታዊ አቅዋም በሚመለከት: ጠንቁ እስካሁን ሊወገድ ያልቻለ: እጅግ አሳሳችና አደናጋሪ፥ አሳፋሪም የኾነ: ከባድ ችግር መፈጠሩን: በግብር ደርሶ ከሚታየው ኹኔታ: በማስተዋል መመልከቱ አያዳግትም::

የዚህ ችግር መንሥኤ: የእነዚህ ባዕዳን ቃላት: በስሟ መካከል መጨመር ሲኾን: ችግሩንም ከባድ ያደረገው: የቃላቱ መታከል: በቀላሉና በአጭሩ ሊነቀሉ የማይቻሉ: ኹለት ዓበይት ጠንቆችን ተክሎ ስለኼደ ነው:: እርግጥ: "Coptic" "ኮፕቲክ": "ቅብጥ" ወይም "ግብፅ" ማለት ስለኾነ: በግብፅ ቋንቋነቱና የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የኾነውን: ማናቸውንም ነገር የሚመለከት በመኾኑ: ጉዳት የለበትም! "Orthodox" "ኦርቶዶክስ": የሚለውም ቃል: ግሪክኛ ኾኖ: "የቀናች ሃይማኖት" ማለት ስለኾነ: በግሪክኛነቱና በቃሉ ትርጉም ላይ ምንም ዓይነት ቅሬታ ሊኖር አይችልም:: ጉዳቱና ቅሬታው ግን: ከዚህ: እጅግ የተለየና የረቀቀ ኾኖ ይገኛል::

ለጠንቆቹ፡ መንሥኤ የኾነው፥ ጉዳትንና ቅሬታንም ያስከተለው፡ የባዕዳኑ ቃላት የፈጠሩት ከባድ ችግር፡ ትቷቸው ያለፉት፡ ኹለቱ ዐበይት ጠንቆች፡ የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ዓቢይ ጠንቅ፡ "Orthodox" “ኦርቶዶክስ” ወይም "Coptic" “ኮፕቲክ” የሚለው፡ ይህ፡ ባዕድ ስያሜ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንት፡ በአበው ልቦና መሥርቷትና በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት አጽንቷት፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የፈጸማትን፥ ከዚህም የተነሣ፡ በዓለም ላይ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ ቀድማና ለብቻዋ እጅግ ጥንታዊት ኾና የኖረችውን፥ አንዲት የኾነችውን፡ የኢትዮጵያን ቤተ ክህነት፡ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ባለው፡ በአራተኛው ምዕት ዓመት ግድም፡ በዚሁ ስም ተለይተው በታወቁት፡ በግሪክ፡ ወይም በኮፕት (በግብፅ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርታ እንደተቋቋመች ማስመሰሉ ነው፡፡

ከጠንቆቹ መካከል፡ የሚከፋው ኹለተኛው ደግሞ፡ ከዚሁ፡ “ኦርቶዶክስ” ከሚለው ቃል የተነሣ፡ ኢትዮጵያ፡ በነገረ መለኮት ሃይማኖታዊ አቋሟ፡ ከካቶሊኮች ጋር ተመሳሳይ በኾነው፡ በግሪኮች ኦርቶዶክሳዊ እምነት ላይ እንደተመሠረተች ያስቆጠራት መኾኑ ነው፡፡

የኋላ ኋላ ግን፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሃይማኖታቸው የቆመበትን ጥንታዊ መሠረት፡ ለጊዜው፡ ከዚህ ታላቅ ስሕተት ለማዳን ይችል ይኾናል ብለው በማሰብ፡ “ተዋህዶ” የሚለውን የግእዝ ቃል፡ ቢቸግራቸው፡ በመጠሪያ ስሟ መካከል ተጨማሪ እንዲኾን አድርገዋል፡፡ ይኸውም፡ “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን” የሚለው አጠራር ነው፡፡

አዎን! እነሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ በፍጹም ሰውነት ስለመገለጡ፡ ቤተ ክህነታቸው ያላትን፡ “የምሥጢረ ሥጋዌ ሃይማኖታዊ አቋም፡ በትክክል ያስረዳልናል፤ ለዚህም ችግር መፍትሔ ሊኾነን ይችላል” ብለው ያከሉት፡ ይህ፡ “ተዋህዶ” የሚለው ቃል፡ እውነትም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተገለጸው፡ የትስብእትና የመለኮት የውህደት ምሥጢር፡ ፍጹም የኾነውን ትርጉም፡ ያለምንም ሕፀፅ፡ በተሟላ ኹኔታ ሊያስተላልፍ የቻለ መልካም ምርጫ መኾኑ ታምኖበታል፡፡ ይኸውም፡ “ተዋህዶ” የሚለው፡ ይኸው ቃል፡ ተቀዳሚና ተከታይ ሳይኖረው፡ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ የተፈጸመውን፡ የእግዚአብሔርን ሰው የመኾን መለኮታዊ ምሥጢር፡ በሚበቃ ግልጽነት የሚያስረዳ በመኾኑ ነው፡፡

ይህም ማለት፡ “ተዋህዶ” የሚለው ቃል፡ በሥጋና በነፍስ ተፈጥሮዋ ምክንያት፡ ፍጹም ሰው ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋን፥ ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ፡ በፍጹም ሰውነት የተወለደው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ የሰውነቱና የመለኮቱ፡ ኹለት አካላትና ኹለት ባሕርያት፡ በፍጹም ተዋህደው፡ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ የኾነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማስገኘታቸውን ያብራራል፡፡ ኢትዮጵያውያን፡ የቀናና የጠራ ትርጉም ባለው፡ በዚህ ቃል አማካይነት፡ በያዙት፡ በነገረ መለኮት ትምህርታቸው፡ ትስብእትና መለኮት፡ አማናዊውን ውህደት ያደረጉበትን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን የሥጋዌ ምሥጢር፡ በትክክል ለማስረዳት ችለዋል፡፡ እንዲህ፡ ረቂቅ የኾነውን፡ የሃይማኖት ነገር፡ አጉልቶና አግዝፎ፥ ምሥጢር የኾነውንም ገልጾና ተርጉሞ የሚገልጽ በመኾኑ፡ ለዚህ “ተዋህዶ” ለሚለው የተሟላ ኢትዮጵያዊ ቃል፡ ሌላ ባዕድ የኾነ ደባል አያስፈልገውም፤ ራሱ ብቻውን በቂ ኾኖ ይገኛል፡፡

ባዕዳን ግን፡ ያንኑ፡ ጠንቀኛ ተግባራቸውን አሁንም ሳያለዝቡ፡ ይህንኑ "ተዋህዶ" የሚለውን ቃል፡ ሌላ የትርጓሜ ሐተታ እንዳለው በማስመሰል፡ ሊያማስኑት ሲሞክሩ ይታያል። ይኸውም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸው፡ በአንድ የመለኮት ባሕርይ ብቻ ነው" ለሚለው፡ ለአውጣኪስ የኑፋቄ ትምህርት የተሰጠው፡ "Monophysite" "ሞኖፊዚት" የሚባለው ይትበሃል፡ ከዚሁ ከ"ተዋህዶ" ቃል ጋር "ተመሳሳይነት አለው" እያሉ በሚያስፋፉት የሐሰት ትርጓሜያቸው ይታወቃል።

እንግዴህ፡ ባዕዳን ሕዝቦች እንደሚያደርጉት፡ በኢትዮጵያ በኩል፡ በቤተ ክህነቷ፥ በቤተ ምልክናዋና በቤተ ሕዝቧ መካከል መለያየትና መከፋፈል ስለሌለ፡ ለኢትዮጵያ "ቤተ ክርስቲያን"፡ ሌላ ተጨማሪ መለያ ስያሜ ከቶ አያስፈልጋትም። ያው መደበኛ የኾነው የታወቀው ስሟ፡ እንዳለ፡ ማንነቷን፡ ራሱ ስለሚናገር፡ እርሱ ይበቃታል፤ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ስሟ ማለት ነው፤ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" ራሷ፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" ናትና!

## በጳጳሳት አሿሿም ላይ፡
## የተፈጸመ፡ የማይረሳ ደባ።

ኢትዮጵያ፡ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር በጀመረችው ሃይማኖታዊ ግንኙነት ምክንያት፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከግብፃውያን እጅግ ቀደም ብለው፡ ከአራት ምዕት ዓመታት በፊት፡ "የሐዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካይነት የተቀበሉትን ሐዋርያዊ ውርስ፡ በበለጠ አጠናክረው ለመቀጠልና ከክርስትና ተዋህዶ ሃይማኖታቸው ሳይነዋወጹ፡ በዚያው በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርታቸው ጸንተው ለመገኘት ይችሉ ዘንድ፡ ያገዛቸው መኾኑ አይታበልም። እንዲያውም፡ ጥንታዊት ቤተ ክህነታቸው፡ በዓለም የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አንድነት ውስጥ የበለጠ እውቅና እንድታገኝና ሰፊ ተሣትፎ እንዲኖራት ረድቷል ሊባል ይቻላል።

ይኹን እንጂ፡ ትሑትና ቃሏን ጠባቂ፥ የባለአደራዎቿንም ፈቃድ አድራጊ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ በተለይም፡ በቤተ ክህነቷ ላይ፡ በዚያን ዘመን፡ ተደማጭነት በነበራቸው፡ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትም ኾነ ወይም በግብፃዊቷ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኩልም ቢኾን፡ የተፈጸመው የትምክህትና የማናለብኝነት በደል፡ በኢትዮጵያዊ ወይም በክርስቲያናዊ ሕሊና አመዛዝነው ሲመለከቱት፡ ምናልባት፡ በይቅርታ ሊታለፍ የሚቻል ቢኾን እንኳ፡ ምንጊዜም፡ "ተገቢና ትክክል ነው" የማይባል ኾኖ ይኖራል።

ይህም፡ ኦርቶዶክስና ካቶሊክ የሚለው መከፋፈል ገና ሳይመጣ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ "አሓቲ"፡ "አንዲት" በነበረችበት፡ በ፬ኛው ምዕት ዓመት፡ ቁጥራቸው ፫፻፲፰ የኾነ መሪዎቿና ሊቃውንቷ፡ አርዮስን ለማውገዝ፡ በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በኒቅያ ተሰብስበው ሣሉ፡ ባዘጋጁትና በዘመኑ ለነበረው ንጉሥ፡ ለቆስጠንጢኖስ አቅርበው ባስጸደቁት፡ "ፍትሐ ነገሥት" በተባለው የቀኖና፡ ማለትም፡ የሃይማኖታዊ ሕግ መጽሐፍ ውስጥ፡ ተጽፎ ይነበባል። ያለኃፍረትና ያለይሉኝታ፡ በገሃድ ድፍረት፡ ሥርዋፅ ወይም እመጫት ኾኖ እንዲገባ የተደረገው፡ ይኸው አጠያያቂና አጠራጣሪ የኾነው፡ ቃል፡ በዚሁ መጽሐፍ፡ ቀዳማዊው ክፍል በኾነው፡ በፍትሐ መንፈሳዊ፡ አንቀጽ ፬፥ ቁጥር ፳፯ (፵፪) ላይ፡ እስከዛሬ ሠፍሮ የሚገኘው ነው።

ቃሉም፡ እንዲህ ተብሎ ይነበባል፡- "የኢትዮጵያ ሰዎች፡ ከአዋቂዎቻቸው መካከል፡ ሊቀ ጳጳሳት አይሹሙ! ከሌላ የሚኾነውን (ግብፃዊዉንም) እንኳ ቢኾን፡ በራሳቸው ፈቃድ አይሹሙ! (ግብፃዊው) ጳጳሳቸው፡ ከእስክንድርያው (ከግብፁ) ሊቀ ጳጳሳት ሥልጣን በታች ነውና፤ ከወገኖቹ ግብፃውያን መካከል፡ ሊሾምላቸው የሚገባው፡ እርሱ ነውና:: በሊቀ ጳጳሳት ስም የተጠራውና በኢትዮጵያውያን ላይ የተሾመው፡ ይህ ግብፃዊ ጳጳስ፡ ጵጵስና በተሾመ ጊዜ፡ ሌሎቹ ሊቃነ ጳጳሳት፡ ጳጳሳትን እንደሚሾሙት ዓይነት፡ ጳጳስ የመሾም ሥልጣን የለውም፤ ይህን የመሰለው፡ የመሾምና የመሻር ሥልጣን ሳይኖረው፡ 'ሊቀ ጳጳስ' በመባል ብቻ፡ በስም ይከበር እንጂ::"

እንግዲህ፡ እንደመንፈስ ቅዱስ ቃል ሲከበር የኖረው፡ ይህን የመሰለው የሰዎች ውሳኔ ነው:: አይገርምም? በእርግጥ፡ ይኼ ቃል÷ ይኼ ሕግ፡ "ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው" ተብሎ፡ በመጽሓፍ ሲጻፍ ይቅርና፡ በአንደበት እንኳን ከቶ ሊነገር ይገባል? ያውም በእግዚአብሔር አምልኮ፡ ከዓለም ሕዝቦች ኹሉ ቀዳሚዎች ኾነው ለሚገኙትና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ለኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ ይህን የመሰለ ሕግ፡ "ፍትሕ መንፈሳዊ" ተብሎ፡ ከግብፃውያን ሲሰጥ፡ በኢትዮጵያ በኩል፡ ሕጉን አጽድቀው በሥራ ላይ ያዋሉት ወገኖች፡ "በዚያን ጊዜ፡ ምን ዓይነት ዓላማ ቢኖራቸው ነው፡ ይህን የውርደት ግዴታ በፈቃደኛነት የተቀበሉት" አያሰኝምን?

አዎን! ይህ፡ በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ የተጠቀሰው አንቀጽ፡ በቤተ ምልክናው በኩል፡ "የሰሎሞን ዘር በመኾናችን፡ 'የዘውዱ ባለቤቶች እኛ ነን'" የሚሉት፡ እኒያ፡ ወገኖች፡ አንድ የተለየ፡ የግል ዓላማ እንደነበራቸው፡ በተጨባጭ የሚያስረዳ፡ በቂ ምስክር ኾኖ መገኘቱን፡ ማንም ሊጠራጠር አይችልም::

በዚህ ሥርዋፅ ምክንያት፡ ኋለኛዪቱና ታናሿ እህት የኾነችው፡ የአዲስ ኪዳኗ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን፡ ታላቂና የበኵር እህት በኾነችው፡ በብሉይ ኪዳኗ ጥንታዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ላይ፡ ለአያሌ ምዕት ዓመታት፡ በአምባገነን የበላይነትና በማናለብኝነት ሥልጣን፡ ያሻትን ስትፈጽም እንድትኖር ያስቻላትን፡ ልዩ የኾነ ሃይማኖታዊ መብትና ኃይል ተጎናጽፋ ኖራለች:: ግብፃዊቷ ቤተ ክርስቲያን፡ ይህን በመሰለ መልክ ከተቀዳጀችው ሙሉ መብትና ሥልጣን የተነሣ፡ በትውልዳቸው፡ ግብፃውያን የኾኑትን፡ የራሷን ጳጳሳት እየሾመች ወደኢትዮጵያ በመላክ ለመኖር ስትችል፡ ኢትዮጵያውያን ግን፡ ለዚህ ማዕርግ የሚበቃ ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን፡ ከመካከላቸው መርጠው እንዳይሾሙ፡ በፍጹም ታግደዋል፤ ተከልክለዋልም::

ይህ ብቻ ሳይኾን፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን፡ ቀብታ እንድትሾምላቸው፡ ኢትዮጵያዊ የኾነውን እጩ ቀርቶ፡ ያንኑ ግብፃዊዉን እንኳ፡ መርጠው የማቅረብ መብታቸውን ጭምር ተገፍፈው ቀይተዋል:: ግፉ በዚህ ብቻ አላበቃም፤ ያ ግብፃዊው ጳጳስ፡ የሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ቢኖረውም እንኳ፡ ምናልባት፡ በአገር ርቀትና በጊዜ ርዝመት ምክንያት፡ ከኢትዮጵያውያን ጋር ተወዳጅቶ፡ ከመካከላቸው፡ ወገኖቻቸውን፡ ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ እንዳይሾም ለማድረግ ሲባል፡ የሊቀ ጳጳስነት፡ ስሙንና ክብሩን ብቻ እንጂ፡ ለማንኛውም ሊቀ ጳጳሳት በተሰጠው መንፈሳዊ ሥልጣን፡ ኤጲስ ቆጶሳትን የመሾምና የመሻር ሥልጣን እንዳይኖረውም ተደንግጓል::

በዚህም ገደብ፡ ያ፡ ወደኢትዮጵያ ይላክ የነበረው ግብፃዊ ሊቀ ጳጳስ፡ በዓለም ላይ ከተሾሙት፡ ከኹሉም ሊቃነ ጳጳሳት መካከል፡ ብቻውን ተለይቶ፡ የዚህ አድላዊ ድንጋጌ ሰለባ ኾኖ ኖርዋል።

ይህ ድርጊት፡ ለኢትዮጵያውያንና ለሌላው ተመልካች ቀርቶ፡ ለራሳቸው ለግብፃውያን ጭምር፡ እንዴት ያስገርማቸው! የቱን ያህልስ ያሳዝናቸው! ያሳፍራቸውስ!

አንዳንድ ወገኖች፡ ይህን፡ ከእግዚአብሔር እውነት የራቀ አሠራር፡ ትክክለኛ አስመስለው ለመቀበል ሲሉ፡ አባ ሰላማ፡ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ተሹሞ ወደኢትዮጵያ የተላከ፡ የመጀመሪያው የግብፅ ጳጳስ ነው ለማለት ይደፍራሉ። አዎን! አባ ሰላማን፡ "ግብፃዊ ነው" ብለው ከተቀበሉት፡ ይህ አባባላቸው፡ ትክክል ሊኾን ይችላል። ነገር ግን፡ ከላይ እንደተብራራው፡ አባ ሰላማን፡ በኢትዮጵያዊነቱ የወሰድነው እንደኾነ፡ ኢትዮጵያ፡ ከጥንት ጀምራ፡ ይዛ በኖረችው የሊቀ ካህናትነት ሥልጣኗ ምክንያት፡ ለጵጵስናው ማዕርግ ያላትን ቀዳሚ ባለቤትነት ሊፋለማት የሚችል ሌላ ተቀናቃኝ ስለሌለ፡ ጥንታዊና ቀዳማዊ የኾነውን ሥልጣነ ክህነቷን፡ በዚያ ስያሜና መልክ፡ ለዓለም አሳውቃ፡ በይዞታዋ ቀጥላለች ቢባል፡ አግባብነት ሊኖረው የሚችል ይኾናል። እውነቱና ትክክሉም ይህ ነው።

ይኸውም፡ የሊቀ ካህናትነቱ (ወይም በዘመናዊው አጠራር፡ የ"ጵጵስና"ው) መንበር፡ በዘመነ ኪዳን ልቦና፡ ከአዳምና ከኖኅ፡ ሲወርድ ሲዋረድ፡ በእነመልከ ጼዴቅ፥ ኋላ ደግሞ፡ በዘመነ ኪዳን ኦሪት፡ በእነአዛርያስ፥ በመጨረሻም፡ በዘመነ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ፡ በእነአቤሜሌክ (በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ) እና በእነእንበረም ተይዞና ተጠብቆ የኖረ በመኾኑ ነው። አባ ሰላማም፡ የዚህ መንበር ተካፋይ ለመኾን የበቃው፡ ፳፱ በኢትዮጵያዊነቱ መኾኑ፡ ቀደም ብሎ በተሰጠው ሐተታ ተመልክቷል።

እንግዲህ፡ ያ ሥርዋፅ አንቀጽ ያስከተለውን በደልና ግፍ ተሸክሞ መቀጠል፡ ለሰብአዊ ተመልካች፡ የማይቻል መስሎ ቢታይም፡ ኢትዮጵያውያን ግን፡ ይህ ዕድል፡ መለኮታዊዉን በረከትና ጸጋ የሚያስገኝ ፈተና ይኾንላቸው ዘንድ፡ ከእግዚአብሔር እንደተፈቀደና እንደታዘዘ በመቁጠር፡ ኹሉንም በትሕትናና በጽሞና ተቀብለው፡ ተስፋ ያደረጉት የፍርድ ቀን የሚደርስበትን ጊዜ፡ በሃይማኖት ትእግሥታቸው ጸንተው እየተጠባበቁ ኖረዋል።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና፥ በመጨረሻ፡ ኢትዮጵያውያን፡ የመንፈሳዊ ብልህነታቸው ፍሬ በኾነው፡ ትእግሥታቸው በመጠቀም፡ በቅርቡ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ሰላማዊ ስምምነት አድርገው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ተገቢ የኾነውን፡ የጥንቱን የቅድምና ደረጃዋን ለማጽናት የበቃችበትን ሽግግር፡ በሠመረ ኹኔታ አከናወኑ። በዚህም፡ እነሆ፥ ያ፡ የረዥም ዘመን፡ የፈተና ጽዋ፡ የክብር አክሊልን በተቀዳጀ የጨዋነት ሥርዓት፡ ከመልካም ፍጻሜ ደረሰ!

ይህ ብቻ አይደለም! በእነዚያ ፈታኝ ዘመናት፡ ኢትዮጵያውያን፡ በቤተ ክህነታቸው በኩል የገጠማቸውን፡ ያን የተወሳሰበ ችግር፡ እንዴት አድርገው በብልሃት እንደተቋቋሙትና መፍትሔ አግኝተው እንዳስወገዱት፡ በማስተዋል መመልከቱ ያስደንቃል። ይኸውም፡ ይህን የድል አክሊል ለመቀዳጀት የሚችሉበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ፡ በዚህ ረገድ፡ ይዘውት የኖሩትን፡ ያልተቋረጠ ነጻነታቸውን ጠብቀው የቆዩበት አቋማቸው ነበር።

በዚያ አቋማቸው፡ በኋላ ዘመን፡ ግብፃውያን፡ "ጳጳስ"፥ "ሊቀ ጳጳስ" እና/ወይም "ፓትርያርክ" ከሚሏቸው የክህነት ማዕርጋት ጋር ተነጻጻሪ የኾኑት፡ "ሊቀ ካህናት"፥ "ንቡረ እድ" እና/ወይም "እጨጌ" የተባሉት፡ የቀደሙት የኢትዮጵያ የክህነት ማዕርጋት፡ ከነስማቸውና ከነክብራቸው፥ ከነመንበራቸውና ከነሥልጣናቸው፡ ሳይቋረጡ፡ በኢትዮጵያውያን ተሿሚዎች ላይ ሕያዋን ኾነው እየተሠራባቸው፡ እንዳሉ ተጠብቀው፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉና እየተወረሱ እንዲቀጥሉ አድርገዋል፡፡ ይህም፡ የሚደነቅ ብልህነታቸውን ያሳያል፡፡

## ኢትዮጵያ፡<br>"ፍትሐ ነገሥት" ስለተባለው መጽሐፍ<br>ስትፋረድ!

በመጨረሻ፡ ይህን የመሰለውን አጠያያቂና አጠራጣሪ አንቀጽ ይዞ ስለተገኘው፡ "ፍትሐ ነገሥት" ስለተባለው፡ ስለራሱ ስለመጽሐፉ፡ የሚባለው ምንድር ነው? እውነተኛ ምንጩ ከየት ነው? በእርግጥ መቼና በእነማን ተዘጋጀ? በዚህ ረገድ፡ የፍትሐ ሥጋዊውን አንቀጾች ብቻ ሳይኾን፡ የፍትሐ መንፈሳዊውን አንቀጾችንም እንኳ ጨምረው ቢመረምሩዋቸው፡ ስንቶቹ ተጠብቀዋል? ተከብረዋል? "ኹሉም መከበር፥ መጠበቅ አለባቸው!" ከተባለ ደግሞ፡ ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ በምሳሌነት በመጥቀስ፡ ውግዘቱ ፈርሶ፡ ከዚሁ አንቀጽ ውጪ ተሹመው የነበሩትና ዛሬ በሹመቱ ላይ ያሉት፡ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዴት ሊኾኑ ነው? በፍትሐ ነገሥቱ መሠረት፡ ሹመታቸው ሊወገዝ ይገባዋል? ወይስ ሊጸና የሚገባው ነው? ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች፡ መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

"ፍትሐ ነገሥት"፡ ስሙ ራሱ እንደሚያስረዳው፡ በዘመነ ምሕረት፡ በ፲ኛ ምዕት ዓመት ለነበሩ ክርስቲያኖች ነገሥታት፡ ለሥጋዊና መንፈሳዊ የዳኝነት አስተዳደራቸው አስፈልጓቸው፡ የተዘጋጀ የሕግ መጽሐፍ መኾኑ የታወቀ ነው፡፡ "ፍትሐ መንፈሳዊ" እና "ፍትሐ ሥጋዊ" በተባሉ አርእስት ለኹለት የተከፈለው ይህ መጽሐፍ፡ በየጊዜው የተሻሻለ መኾኑን ለማረጋገጥ፡ ዛሬ፡ በአገራችን፡ የሚገኝበትን ኹኔታ ገምግሞ ውጤቱን መመልከቱ ይበቃል፡፡ የዚህ መጽሐፍ፡ ኹለተኛ ክፍል የኾነው ፍትሐ ሥጋዊ፡ በፍትሐ ብሔርና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች መተካቱ፡ ለዚህ እውነታ ቀዳሚው ማስረጃ ነው፡፡

በፍትሐ መንፈሳዊ ውስጥ ከሚገኙት አንቀጾች መካከል ደግሞ፡ ምን ያህሉቹ ናቸው በይፋ ተከብረው ያሉት? ወይስ በይፋ ተሽረው የሚታዩት? ሳይሻሩ፡ ተከብረውና ጸንተው የሚገኙት የትኞቹ ናቸው? የምእመናኑ ሕይወት? የጋብቻው ሥርዓት? የትዳሩ አቋምና የቁርባኑ አቀባበል ነው ያልተሻረው? ወይስ የትምህርቱና የክህነቱ አሰጣጥ? የመነኮሳቱና የጳጳሳቱ አስተዳደርና አኗኗር? የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያኑ አያያዝና አፈጻጸም? የቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና የጽላት አፈቃቀድ ነው ያልተሻረው? የትኛው ተወስቶ፡ የትኛው ይቀራል? "የመጽሐፉ አንቀጾች፡ በሙሉ መከበር አለባቸው!" እንደሚሉት ወገኖች አስተሳሰብ ከኾነ፡ እነዚህኑ አንቀጾች፡ አክብረን ባለመፈጸማችን፡ በውስጡ የተጻፉት ውግዘቶች ኹሉ፡ ጸንተውብን ቢኾን ኖሮ፡ የውግዘቱ ቀምበር፡ ዓይነቱ፡ ከመብዛቱና መጠኑ፡ ከመክበዱ የተነሣ፡ መሸከም አቅቶን፡ እስካሁን ወዳድቀን በጠፋን ነበር፡፡

ደግሞም: በአሁኑ ጊዜ: አንዳንድ ወገኖች: "ሊከበሩ ይገባቸዋል!" ብለው እንደሚሟገቱላቸው: የዚህ መጽሐፍ አንቀጾች ዓይነት: ያም: ኢትዮጵያውያን: ራሳቸው: ጳጳስ ኾነው እንዳይሾሙ፥ ሌላውንም: እንዳይሾሙ: የሚያዝዘው አንቀጽ: "ሊሻር አይገባም!" እያሉ: ቀደም ብለው ይከራከሩ የነበሩ መኖራቸውን ማስታወስ ምን ይደንቅ? ከተሻሩት አንቀጾች መካከል: በኢትዮጵያውያን ላይ ስለሚሾመው: ስለግብፃዊው ሊቀ ጳጳሳት አመራረጥና አሿሿም: ከላይ በተጠቀሰው በአንዱ አንቀጽና ቁጥር: የተጻፈውን: ያንኑ ቃል: እስቲ: በመጠኑም ቢኾን እንመርምረው!

እንግዲህ: አንዳንዶች: "ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ አይቻልም፤ ግዝቱም መከበር አለበት!" የሚሉት: ይህ መጽሐፍ: ይህን የመሰለውን አንቀጽ የያዘ መኾኑንና ይህንኑ: መንፈሳዊ ሕግ: አክብረው ሊያስከብሩ: ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው የሚባሉት ባለሥልጣኖች: ሕጉን: ማሻሻልና መለወጥ ብቻ ሳይኾን: ራሳቸው: የሻሩትና ውግዘቱን ያፈረሱ መኾናቸው: በእውን ተረጋግጦ ሲታይ: ምን ሊባል ነው? አዎን! ይህ አንቀጽ: ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በተሾሙባት ዕለት: በገሃድና በይፋ ተሽሩዋል:: ከዚያን ቀን ጀምሮ: እስካሁን የተሾሙት: ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ብዛት: ምናልባት: ከመቶ በላይ ሳይኾን አይቀርምና: እነኚህ ኹሉ ጳጳሳት: እያንዳንዳቸው: በነፍስ ወከፍ: ለዚህ አንቀጽ መሻሻር: ግዙፉንና ሕያዋን ማስረጃዎች መኾናቸው አያከራክርም::

ታዲያ፥ የፍትሐ ነገሥቱ ቃል: በምንም ምክንያት ሊሻር ወይም ሊለወጥ ፈጽሞ እንደማይቻል አድርገው በመቁጠር: በዚህ አቋማቸው: ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩት ወገኖች: ከዚህ: ከተጠቀሰው: ከፍትሐ ነገሥቱ አንቀጽ ውጪ የተሾሙትንና በውግዘቱ የተያዙትን: እኒህን ኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት፥ ቀጥሎም: በእነርሱ እጅ የተሰጠውን ሥልጣነ ክህነት፥ እንዲሁም: ከእነርሱ ጀምሮ በተዋረድ የተፈጸሙትን: ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን: እንዴት ሊያደርጓቸው ነው? በፍትሐ ነገሥቱ መሠረት: ይህ ኹሉ ሕገ ወጥ የኾነና "ውግዘት" ያለበት አሠራር: የጸና ሊኾን ነው? ወይስ የተሻረ? ይህ ነገር ደግሞ: ሃይማኖትን የሚነካ ስለኾነ: ዝም ተብሎ: ሊታለፍ አይቻልምና: ጉዳዩ የሚመለከተው: ቤተ ሕዝቡ: ለዚህ የተወሳሰበ ችግር: አንድ ዓይነት መፍትሔ ሊሰጥበት ይገባል:: ማለትም: ፍትሐ ነገሥቱ: ወይ: "ሕጉና ውግዘቱ: በሙሉ እንደጸና መቀጠል አለበት!" ወይ: "ሕጉም፥ ውግዘቱም ኹሉ መሻር አለበት!" ወይም: "እንዲህ፥ እንዲህ ያሉት አንቀጾች ተሽረው: በዚህ፥ በዚህ አንቀጾች ተተክተዋል፤ የቀሩትም: እንደጸኑ ይቀጥላሉ!" ተብሎ: ቤተ ሕዝቡ፥ ቤተ ክህነቱና ቤተ ምልክናው: በአንድነት: መክረውበትና ተስማምተውበት: አንድ ሕጋዊ ውሳኔ: በቃለ ዓዋዲ መታወጅ ይኖርበታል::

እንግዲህ: ለጥቅም እንዲውል ሲፈለግ: የሚጸና፥ ሳይፈለግ ደግሞ: ያለሕጋዊው ሥርዓት: በዘፈቀደ ብቻ: እንዲህ እየተሻረ የሚጣል ሕግ: እንኳንስ በመንፈሳዊው ሕይወት ይቅርና: በሥጋዊዉም አስተዳደር ቢኾን: ሕጋዊነቱ: አጠራጣሪ ስለሚሆን፥ ፍትሐ ነገሥትም: ከላይ እንደተመለከተው: ከሰዎች በደረሰበትና በሚደርስበት ጥቃት ምክንያት: ይህን የመሰለው: የሃይማኖት ሕፀፅና የአፈጻጸም ቀውስ እየተገኘበት: ሲቆነጻጸል የኖረ በመኾኑ: የእግዚአብሔር ወይስ የሰው ሥራ ሊባል ይገባው እንደኾነ: ውሳኔውን: ለእያንዳንዱ አስተዋይ ተመልካች: የሕሊና ዳኝነት እተወዋለሁ::

## ኢትዮጵያ፡
## ስለትርጓሜዎቿ መዛባት፡ ግብፃውያንን
## ስትፋረድ!

የሃይማኖት ወገኖቻችን በኾኑት፡ በባዕዳን አብያተ ክርስቲያናት፡ በተለይም፡ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን የተጽዕኖ ኀይል ሠርገው ገብተው፡ መሠረት ከያዙትና እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያውያን የእምነት ባህል ላይ ሰፍነው ከሚታዩት፡ ረቂቃን ደባዎች መካከል፡ ጥቂቱን፡ እስቲ፡ አልፎ አልፎ፡ ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት! ይህም፡ ለምሳሌ ያህል፡ በውዳሴ ማርያም የትርጓሜ ሐተታና በቅዳሴ ጸሎታችን ውስጥ ከሚነገረው የተዛባ ታሪክና ጎጂ ሥርዓት፡ የተውጣጣ ነው።

### ኢትዮጵያዊዉን ካህን፡ ዮቶርን በሚመለከት።

*"አንቲ ውእቱ ዕፅ፡ ዘርእያ ሙሴ በነደ እሳት፡ ወኢትውዒ"፡ "ነደ እሳት ሠፍሮባት፥ በነደ እሳት ተከብባ፡ ሳትቃጠል፡ ሙሴ፡ በደብረ ሲና ያያት ቍጥቋጠ አንቺ ነሽ"* በሚለው፡ በማግሰኞ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ውስጥ፡ የሙሴ ታሪክ ይነገራል፤ እዚህ ላይ፡ ሙሴ፡ ከቍጥቋጦዋ ሲቀርብ፡ *"የምትቆምባት ምድር የተቀደሰች ናትና፡ ጫማህን አውልቅ!"* ሳለው፡ ለጌታ ቃል፡ "ከግብፅ ስትመለስ፡ በደብረ ሲና የምትሠራልህ ሕግ፡ ክብርት ናትና፡ ልማደ ዮቶርን ተው ሲለው ነው፤ ፋል የሚባል ጥንቆላ ተምሮ ነበርና።" ተብሎ፡ የአንድምታ ሐተታ ተሰጥቶበታል፤ ይህም፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ጋር ፈጽሞ አይስማማም።

ሙሴ፡ ሊተወው የሚገባ "ልማደ ዮቶር" ከቶ ምን ኖርዋል? ፋል የሚባለውንስ ጥንቆላ የተማረው፡ የት ኖርዋል? የዮቶር ልማድማ፡ በሕገ እግዚአብሔርና በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ እንደነበረ፥ ሙሴም፡ ጥንቆላውን የተማረው፡ በግብፅ እንደነበረ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ አሥፍረው ተናግረውታል።

ሴት ልጁን፡ ሲጳራን፡ ለሙሴ የዳረለት፡ ኢትዮጵያዊው ዮቶር፡ ወይም ራጉኤል የተባለው፡ ይኸው ሰው፡ የእግዚአብሔር ካህን በመኾኑ፡ ቀደም ብሎ፡ በግብፅ ምድር፡ በጣዖት አምልኮ፥ በጥንቆላና በአሕዛብ ሥርዓት አድጎና ሠልጥኖ የኖረው ሙሴ፡ ተሰድዶ ወደኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ፡ በቤቱ ተቀብሎና አስተናግዶት፡ አብሮት ሲኖር ሣለ፥ ኋላም፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ አውጥቶና የኤርትራን ባሕር አሻግሮ እየመራ በተመለሰ ጊዜ፡ በምድረ በዳ ሲቀበለው፡ ይኸው ካህኑ ዮቶር፡ በኢትዮጵያዊነቱ፡ ከአባቱ፡ ከመልከ ጼዴቅ የወረሰውን፡ የቤተ ሕዝብን፥ የቤተ ምልክናንና የቤተ ክህነትን ሥርዓታት አዋህዳ ስለያዘችው፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥትና በውስጧ ስለሚካሄደው፡ ስለእውነተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር፡ ለሙሴ፡ ተገቢውን ትምህርትና መመሪያ እንደሰጠው፡ ዓለም የተቀበላቸው፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በይፋ ይመሰክራሉ።

ይህ መኾኑ እየታወቀ፡ የኋለኞቹ የግብፅ ክርስቲያኖች፡ በዚያን ጊዜ፡ ጣዖት አምላኪዎች የነበሩት፡ የቀድሞዎቹ ግብፃውያን ወገኖቻቸው እንኳ እንዳይነኩባቸው፡ የእነሱንና ያገራቸውን ስም ለመጠበቅ ሲሉ፡ የእነርሱ የኾነውን ክፉውን ኹሉ፡ የእግዚአብሔር አምላኪና አገልጋይ ካህን ለኾነው፡ ለንጹሑ ኢትዮጵያዊ፡ ለዮቶር አዛውረው በመስጠት፡ እርሱን፡ እንደጣዖት አምላኪና እንደልማደኛ ጠንቋይ መቁጠራቸው ሊያስደንቅ አይችልም፡፡
የሚያስደንቀውስ፡ ይህ ጥፋትና ስሕተት፡ ጥቃት በማይሰማቸውና ለባዕዳን ተፃራሪዎቻችን፡ የበደሉ ተባባሪዎች በኾኑ፡ በራሳችን፡ ሊቃውንትና ካህናት፡ ዛሬም በይፋ እየተነገረ መቀጠሉ ነው፡፡

## ኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ ማክዳን በሚመለከት፡፡

በዚሁ በማግሰኞ የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ፡ *"ተፈሥሒ ኦ መድኃኒታ ለሔዋን"፡ "የሔዋን ደኅንነቷ ሆይ! ደስ ይበልሽ!"* በሚለው አንቀጽ፡ ስለሰሎሞን በሚነገረው የታሪክ ሐተታ ውስጥ፡ ሰሎሞን፡ "በፍጻሜ ዘመኑ፡ ንስሓ ቢገባ፡ 'አይዞህ! መርገም ያልወደቀባት ንጽሕት ዘር፡ ከአዳም ባሕርይ ተከፍላ፡ በእሴት አካል ተቀርፃለች፤ ከዚያ ሲወርድ ሲዋረድ' እያለ ይቀጥልና፡ 'በዳዊት አካል ተቀርፃለች፤ ከዳዊትም፡ ባንተ (በሰሎሞን)፥ ካንተም፡ በሮብዓም ተቀርፃለች፤ ከእርሷም፡ አምላክ ይወለዳል፤' ይላል፡፡ በቅዳሴ ማርያም ትርጓሜም ላይ፡ "ቡራኬሁ ለሴም፡ ወክፍል ሎቱ"፤ "የሴም፡ ምርቃቱ፥ በረከቱ፡ ደግሞም ዕድል ፈንታው፥ ጽዋ ተርታው አንቺ ነሽ" በሚለው ሐተታ ውስጥ፡ "እመቤታችን የተወለደች፡ ከሴም ወገን ነው" የሚል ቃል' ይገኛል፡፡

ከሦስቱ የኖኅ ልጆች፡ ማለትም፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት የውህደት ነገድ በመወለዱ፡ በዘርና በትውልድ፥ በሥልጣንና በተልእኮ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌና የኢትዮጵያውያን አባት ስለኾነው፡ ስለመልከ ጼዴቅ፡ በዚህም ኾነ በማናቸውም ትርጓሜ፡ እምብዛም የማይነገረው፡ ለምን እንደኾነ ግልጽ ነው፡፡ ያው፡ እውነተኛው የኢትዮጵያዊነት ምሥጢር እንዳይወጣ ለመከላከል አይደለምን? እንግዴህ፡ ይህ እውነታ ሳይዘነጋ፡ እዚህ ላይ፡ የራሳችን ስለኾነው፡ በቅድሚያ፡ በብሉያቱ፡ ከሰሎሞን ጋር ስለተያያዘው፡ ንግሥተ ሳባ ስለምትባለው፡ ስለንግሥት ማክዳና እርሷም፡ ከእርሱ፡ ከሰሎሞን ስለወለደችው፡ ስለምኒልክ ታሪክ ለምን አልተወሳም? ከዚያ ጋር አያይዞም፡ በሐዲሳቱ ስላለው፡ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እውነተኛ ማንነትስ እንዴት አልተገለጸም? እኛ ኢትዮጵያውያን ያልገለጽነው ማን ሊገልጸው ነው? እንግዴህ፡ የእኛ ሙያ፡ ባዕዳን የሚሉትን ኹሉ፡ በጭፍን "አዎን" እያልን ማስተጋባት ብቻ ኾኖ ሊቀር ነውን?

በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተውን እውነተኛ ታሪካችንን ኹሉ፡ ባዕዳን፡ "ተረት ነው" እንደሚሉት ኹሉ፡ የእኛም፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ ያንኑ ማጽደቃቸው ይኾን? ለነገሩማ፡ ባላጋራዎቻችን፡ ይህችኑ፡ ስመጥሩዪቱን ኢትዮጵያዊት ንግሥታችንን፡ "አረማዊት"፥ "ፀሐይ አምላኪ"፥ "ለዘንዶ የምትሰግድ"፥ "እግሩዋ እንደእንስሳ ሰኰና የነበረ" እያሉ የጻፉባትን ዘለፋ፡ ከራሷ፡ ከልጆቿ መካከል፡ በቃል ብቻ ሳይኾን፡ በጽሑፍ ጭምር የሚያስተጋቡ፡ ጥቃት የማይሰማቸው፡ ሐሞተቢሶች አሉ አይደለምን?

ይህስ: እንደፍትሐ ነገሥቱ ኹሉ: በግብፃውያን: አበጋዝነት እየተስተካከለ በተዘጋጀው: በክብረ ነገሥቱ ውስጥ ሳይቀር: ተጽፎ ይገኝ የለምን? ታዲያ: ከሕዝቧ ጋር በአምልኮተ እግዚአብሔር የነበራት ፍቅር: እንደእሳት የሚያቃጥልና በመንፈሳዊ ቅንዓት የተመላ ከመኾኑ የተነሣ: ስለሰሎሞንና እርሱ: በእግዚአብሔር ላይ ስለነበረው ሃይማኖት በሰማች ጊዜ: *"በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ"*: እስከኢየሩሳሌም ድረስ: ረዥሙን አታካች ጉዞ እንዳደረገች አረጋግጦ በሚናገረው: ዓለም በተቀበላቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ዓምድ ላይ የተመዘገበውን፥ በራሱም በኢየሱስ ክርስቶስ: የወንጌል ቃል: የተሰጠላትን ምስክርነት እንዴት ሊያደርጉት ነው? ዘንግተውት፥ ወይስ በንቀት አቃልለውት ይኾን?

ይህን በሚመለከት፥ እንዲሁም ስለእመቤታችን: ቅድስት ድንግል ማርያም ማንነት: ይኸውም: ኢትዮጵያዊት ከሚያሰኛት: ከሴም፥ ከካምና ከያፌት የውህደት ዘር ስለመገኘቷ: "ኢትዮጵያዊው: በማንነቱ ፍለጋ!" በሚለው መጽሓፌ፥ አልፎ አልፎም: በዚህኛው መጽሐፍ ውስጥ: በቂ ማብራሪያ የተሰጠበት ስለኾነ: እዚህ ላይ መድገሙ አላስፈለገም:: ባጭሩ ለማመልከት ያህል ግን: ይህንኑ የእመቤታችንን: ኢትዮጵያዊነት ለማረጋገጥ: ወንጌላዊውያኑ ማቴዎስና ሉቃስ: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት ለማስረዳት ሲሉ: ያለወንድ ዘር የወለደችውን: የእመቤታችንን የድንግል ማርያምን ሳይኾን: የቅርብ ወገኗ በመኾኑ: እጮኛዋ ተብሎ እንዲጠብቃት: ከእግዚአብሔር የተመረጠውን፥ በታማኝነቱ: "ጻድቅ"፥ በስደተኛ ነዋሪነቱም: ስሙ: "ዮሴፍ" የተባለውን ኢትዮጵያዊ: የትውልዱንና የዘሩን ሐረግ ዘርዝረው በጻፉበት መጽሓፋቸው ውስጥ እንኳ አረጋግጠው የሰጡትን ምስክርነት መመልከቱ ብቻ ይበቃል::

ይኹን እንጂ: ይህን: የእግዚአብሔርን እውነት: አምኖ ለመቀበል: የወንጌላውያኑን ቃል: በባዕዳት ዓይን ሳይኾን: በቅዱሱ ኪዳን በታነጸው: በእውነተኛው የኢትዮጵያዊ መንፈስ: ማለትም: መንፈስ ቅዱስ ባደረበት ልቡና ኾኖ ማስተዋል ይገባል:: አለዚያ: በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግሞ እንደተብራራው: የሴምን ነገድ ብቻ ሳይኾን: የካምንና የያፌትንም ነገዶች ጨምሮ የሚያጠቃልለውን: የኖኅን: ማለትም: መላውን የሰውን ፍጥረት ለማዳን: ሰው የኾነው: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን: ያለወንድ ዘር: በድንግልና የወለደችው: እመቤታችን: ቅድስት ድንግል ማርያም: የተገኘችው: ከሴም ወገን ብቻ ሳይኾን: ከካምና ከያፌት ወገኖች ጭምር መኾኑን የሚያረጋግጠውን: የወንጌላውያኑን ቃል: በቀላሉ: በሃይማኖት ተረድቶ ለመገንዘብ ያዳግታል:: "ኢትዮጵያዊ" የሚያሰኘው: አንዱ መሥፈሪያም: ከሦስቱ: የኖኅ ልጆች ነገዶች: ከሚገኘው የዘር ውህደት መወለድን የሚጠይቅ መኾኑ: ሊታወስ ይገባል::

ታዲያ: እውነቱ ይህ ከኾነ: ያ: የወንጌላውያኑ ቃል: "እመቤታችን የተወለደችው: ከሴም ወገን ነው" በሚል የትርጓሜ ሐተታ: እንዴት ሊሻርና ሊለወጥ ይቻላል? ፈጽሞ አይቻልም::[፸፰]

## ኢትዮጵያውያኑን አቤሜሌክንና ባሮክን በሚመለከት።

አሁንም፡ በዚሁ በማግሰኞ የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ፡ *"ኮንኪ አጽቀ ንጹሐ"፡ "ሐሩረ ፀሓይ ያልወደቀባት፥ ነፋስ ያልወዘወዛት፥ "ለታብቁል" ባለው ቃል፡ ከልምላሜ፥ ከጽጌ፥ ከፍሬ የተገኘች ዐጽቀ ሠሉስ አንቺ ነሽ። "አንድም፡ አጽቀ አቤሜሌክ አንቺ ነሽ!"* ካለ በኋላ፡ ስለኤርምያስ መተረክ ሲጀምር፡ "ለኤርምያስ፡ አቤሜሌክ፥ ባሮክ የሚባሉ ደቀ መዛሙርት ነበሩት፤ የምድያም ሰዎች ናቸው" ይላል። ባዕዳኑ፡ *"ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ"* የሚለውን፡ የቅዱሳት መጻሕፍቱን አጻጻፍ ተከትለው፡ *"አቤሜሌክና ባሮክ፡ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤"* በማለት ፈንታ፡ "የምድያም ሰዎች ናቸው" ያሉት ለምን እንደኾነ፡ መረዳት አያዳግትም። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያውያን የሚለው ስያሜ፡ በቃል እንዳይነገር፥ ከመጻሕፍትም እንዳይነበብና በማናቸውም መልኩ እንዲሠረዝ፥ እንዲጠፋና እንዲደመሰስ፡ ፍላጎታቸው፡ ዛሬ ብቻ ሳይኾን፡ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የነበረ መኾኑ፡ በዚህ ጭምር ይታወቃል። የሚያስገርመው፡ በምቀኝነት ላይ የተመሠረተውን፡ የእነርሱን አሳሳች ድርጊት፡ ከእኛም፡ ከኢትዮጵያውያን መካከል፡ አጽድቀን የቀጠልን መኖራችን ነው።

ነቢዩ ኤርምያስን፡ እስከመጨረሻው ሳይለዩት፡ በታማኝነት የተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ፡ እኒሁ ኹለቱ ኢትዮጵያውያን፡ አቤሜሌክና ባሮክ ብቻ የመኾናቸውን ነገር፡ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ፡ ለኤርምያስ ሲል፡ በራሱ ላይ ከባድ አደጋን ሊያስከትልበት የሚችለውን የትድግና ሥራ፡ በቆራጥነት ካከናወነበት ግዳጁ ጋር በማስተዋል ሲመለከቱት፡ የኤርምያስን ኢትዮጵያዊነት ሳይቀር የሚያሳይ ምልክት ይገኝበታል። የዚህም ነገር፡ እውነተኛነት፡ ኤርምያስ፡ ከአይሁድ ብርቱ ጥላቻ የተነሣ፡ በተለይ በካህናቱ በኩል የደረሰበት ግፍና በደል፡ ፊት፡ በዘመነ ብሉይ፡ በሙሴ፥ ኋላም፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ከተፈጸመው ኹኔታ ጋር ተመሳሳይ በመኾኑ ሊረጋገጥ ይቻላል።

## የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በሚመለከት።

በረቡዕ የውዳሴ ማርያም ትርጓሜ፡ *"አንቲ ዘበአማን ደመና፡ እንተ አስተርአይኪ ለነ ማየ ዝናም"፡ "የዝናም ውኃን ቋጥረሽ የታየሽልን፡ እውነተኛ ደመና አንቺ ነሽ! ...አንድም፡ ደመና ኖኅ አንቺ ነሽ!"* ካለ በኋላ፡ ስለኖኅ መተረክ ሲጀምር፡ *"እሠይም ቀስትየ በውስተ ደመናት፡ ከመ ኢያማስና ለምድር ዳግመ በማየ አይኅ!"* የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ያቀርባል። የዚህ ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ፡ *"ዳግመኛ፡ ምድርን፡ በጥፋት ውኃ የማላማስናት (የማላጠፋት) መኾኔን አስታውቅ ዘንድ፡ ቀስቴን በደመና አሳያለሁ!"* ማለት ሲኾን፥ ጉልተው የሚታዩት የቀስተ ደመናው ዓበይት ቀለማት ደግሞ፡ ሦስቱ፡ ማለትም፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ሲኾኑ፡ የውዳሴ ማርያሙ፡ የአንድምታ ትርጓሜ ግን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሌለውን፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ ትርጉምና ሐተታ ሰጥቶ፡ ሲያብራራ እናገኘዋለን። ትርጉሙና ሐተታውም እንዲህ ይላል፡- "ደመና በዞረ ጊዜ፡ ዐራት ኅብር አድርጌ፡ ቀርጩ አሳይሃለሁ፤ ይኸውም፡ ነጭ፥ ቀይ፥ ብጫ፥ ጥቁር ነው።" በማለት፡ ስለአራቱ ቀለማት ምሥጢር መግለጡን ይቀጥላል።

ሰ

ኢትዮጵያ፡

እንዲህ፡ ዓለሙ ጭምር በተቀበለው፡ በራሷ የኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቦ ለሚገኘው፡ ለእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል፡ ፈጽሞ የሌለና የተሳሳተ ትርጉም ፀመስጠት፥ ደግሞም፡ መላው ፍጥረተ ዓለም፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ኾኖ፡ በጉልህና በገሃድ የሚያየውን የቀስተ ደመናውን ኅብረ ቀለማት፡ በጥቁርና በነጭ በመለወጥ፡ እስከዚህ ድረስ ዓይን ያወጣ፡ የሐሰት ድርጊት፡ በድፍረት የተፈጸመው ለምንድር ነው? እንደዛሬው ኹሉ፡ ባዕዳን የኢትዮጵያ ፀሮች፡ ካገር ተወላጆች ከሃዲዎች ጋር በመመሣጠርና በመተባበር፡ ያው፡ ኢትዮጵያና እውነተኞች ልጆቿ ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው ጋር፡ በቅዱሱ ኪዳን የተሣሠሩበትን፡ ከሰባቱ ኪዳናት፡ አንዱ ምልክታቸውና የማንተማቸው አንዱ ክፍል የኾነውን፡ ሰንደቅ ዓላማቸውን፡ የሃይማኖት ደብዛው ሳይቀር ፈጽሞ ለማጥፋት መኾኑ ሊታበል አይቻልም። በኹሉም የሰልፍ አውድማ ላይ፡ አሸናፊው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ፡ ዲያብሎስ ባለመኾኑ፡ ያ እኩይ ዓላማቸው፡ ይኸው፡ እንዳልሠመረላቸው፡ ማንም የሚመለከተው ነው። አረንጓዴ፥ ብጫ፥ ቀይ የኾነው የቀስተ ደመና ምልክት፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን መኾኑን በማረጋገጥ፡ በድል አድራጊነት፡ በየልባችን ይዘነውና በየትከሻችንም አንግበነው ስናውለበልበው እንታያለፀጮኾኑ፡ ይህ ቅዱሱና ዘለዓለማዊው ቅርሳችን፡ ታሪኩ ተዘርዝሮ፥ ምሥጢሩም ተፍታትቶ ሊነገር የሚገባው፡ መቼና የት፥ በማንስ ነበር? በዚሁ፡ የውዳሴ ማርያሙን በመሰለው ትርጓሜ ላይ፥ የሃይማኖታችን ቅርስ ጠባቂ በኾኑችው በቤተ ክህነትና በካህናት አልነበረምን? ነገር ግን በሃይማኖት አንድነት ሰበብ፡ ሠርገው የገቡብን የወዳጅ ጠላቶቻችንና ባላንጣዎቻችን፡ ግብፃውያን፡ እንዴት አድርገው፡ ሲገዘግዙን እንደኖሩ፥ እኛም፡ ጥቃት የማይሰማን፥ ሃይማኖታዊ ቅንዓት የጐደለንና ሐሞተ ቢሶች ኾነን፡ ዝም ብለን አኅብድደን፡ ግፉን ስንቀበል እንደኖርን፡ ይህ ኹኔታ፡ በሚበቃ እያስረዳ ይመሰክርብናል።

## የኢየሱስ ክርስቶስን
## የልደት ቀን በሚመለከት።

በዚሁ፡ በረቡዕ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ማብቂያ ላይ፡ *"አድኅነ ነፍሳቲነ በምጽአቱ ቅዱስ"*፡ *"በልዩ አመጣጡ መጥቶ አዳነን"* ለሚለው ቃል፡ "የቀደመው የረድዔት ነው፤ የዛሬው የኩነት ነውና!" የሚል አጭር ሐተታን ከሰጠ በኋላ፡ በቀጠለው አንድምታ፡ *"በጽኑ ቀጠሮው መጥቶ አዳነን፤ 'በጽኑ ቀጠሮው አለ!' አምስት ሽህ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም፡"* ቀጠሮውን፡ ማለትም፡ በድንግል ማርያም ማኅጸን ተጸንሶ፡ ከእርሷ የተወለደባትን ጊዜ፡ *"ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፈምና!"* ብሎ የምሥጢር ፍቺውን ያቆማል።

"ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፋትም" የተባለችው ጊዜ፡ የትኛዋ ናት? መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፡ "ትጸንሻለሽ" ብሎ ድንግል ማርያምን አብሥሩዋት፥ እርሷም፡ "እንደቃልህ ይኹንልኝ" ብላ ብሥራቱን እንደተቀበለች፡ ወዲያው፡ በዚያች አፍታ፡ ጽንሰቱ የተፈጸመባት ናት? ወይስ የተወለደባት?

"ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፋትም" የተባለችው ጊዜ፡ ከጽንሰቱ ይልቅ፡ ከማሕፀን የወጣበትን ልደቱን ይመለከታል ማለቱ ትክክለኛ መስሎ ይታያል፤ ምክንያቱም፡ ብሥራቱ፡ የእመቤታችንን፡ ለአምላክ እናትነት መመረጥ ለማስታወቅ፡ በመልአኩና በእርሷ መካከል፡ በምሥጢር የተካሄደ ንግግር ሲኾን፡ ልደቱ ግን፡ የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት በይፋ የተነጋገሩበትና *"ለዓለሙ ኹሉ የሚኾን ታላቅ የደስታ ምሥራችን"* የተሳተፉበት በዓል ስለኾነ ነው፡፡ ይህም፡ *"በዚያም ምድር፡ መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ፡ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ፡፡ እነሆም የእግዚአብሔር መልአክ፡ ወደእነርሱ ቀረበ! የእግዚአብሔር ክብርም በዙሪያቸው አበራ! ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ! መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ 'እነሆ፥ ለእናንተና ለዓለሙ ኹሉ የሚኾን፡ ታላቅ የደስታ ምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ! ዛሬ በዳዊት ከተማ፡ መድኃኒት፡ እርሱም ቡሩክ ክርስቶስ፡ ጌታ የኾነ፡[፳፱] ተወልዶላችኋልና!'* በሚለው የመልአኩ ቃል ተረጋግጦ ይታወቃል፡፡

በዚህ ቃልና እስካሁን ጸንቶ በቀጠለው፡ በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት፥ እንዲሁም፡ "ጽኑ ቀጠሮውን፡ ለአንዲት ሰዓት እንኳ አላሳለፈም" በሚለው፡ በውዳሴ ማርያሙ ትርጓሜ መሠረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደባት ጊዜ፡ በጳጉሜ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም፡ ከሌሊቱ ልክ ፮ ሰዓት ሞልቶ፡ አንዲት ካልዕት ለማትሞላ አፍታ፡ ጥቂት እልፍ ብላ በነበረችው ቅጽበት ውስጥ መኾኑ ነው፡፡ በዘመነ ሐዲሱ የአዝማናት አከፋፈል፡ ዘመኑ፡ ዮሐንስ ይኾናል፡፡ መስከረም ፩ ቀን፥ ፩ ዓመተ ምሕረት ተብሎ፡ የዓመተ ምሕረት ዘመን አቆጣጠር የጀመረውም፡ ከዚያች፡ የዓመተ ኵነኔ፡ ወይም የዓመተ ፍዳ ማብቂያ ከኾነችው፡ ከጳጉሜዋ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም፡ ከሌሊቱ ፮ ሰዓት በኋላ ከነበረችው ቅጽበት ጀምሮ ኾኗል!

ኢትዮጵያውያን፡ "ዓመተ ምሕረት ገባ! ተጀመረ!" ብለው፡ በታላቅ ደስታና ምስጋና፡ የሚያከብሩት ዋናው የዐውደ ዓመት በዓላቸው፡ እስከዛሬ፡ እስከ፲፱፻፺፫ ዓመተ ምሕረት ድረስ፡ ይኸው፡ መስከረም ፩ ቀን መኾኑ፥ ዘመኑንም፡ ዓመተ ፍዳ ተወግዶ፡ ዓመተ ምሕረት መተካቱን ለማጠየቅ፡ "ዓመተ ምሕረት" አሰኝቶ፥ ዓመቱንም፡ ፩ ብሎ እንዲጀመር ያደረገው፡ ይኸው የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት መኾኑ፡ ሊታበል የማይቻልና ሕያው ኾኖ፡ በገሃድ ሲፈጸም የሚታይ ቋሚ እውነታ ነው፡፡

ለዓመተ ምሕረት የጊዜ አቆጣጠራችን፡ መሠረቱ፥ ለዓመተ ፍዳም፡ ድምድማቱ፡ "ቃል፡ ሥጋ ኾነ!" ማለትም፡ "አምላክ ሰው ኾነ!" የተባለበት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን ከኾነ፥ የተወለደባት ቀን ደግሞ፡ በጳጉሜ ፭ ቀን፥ ፭ሺ፭፻ ዓመተ ዓለም፡ ከሌሊቱ ልክ ፮ ሰዓት ላይ ከኾነ፥ ከዚህም በቀር፡ ሳይወለድ፡ "ዓመተ ምሕረት ገባ! ወይም ተጀመረ!" ማለት ስለማይቻል፥ በአጠቃላይ፡ እውነታው፡ ይህ ሲኾን ሣለ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተወልዶበታል! እርሱ፦፡ በየዓመቱ ታኅሣሥ ፳፱፥ በየአራት ዓመቱ ደግሞ፡ በታኅሣሥ ፳፰ ቀን ይውላል!" ተብለን እንድናከብረው የተደረግነው፡ የገና ወይም የልደት በዓል፡ ታዲያ ከየት መጣ? "በጽኑ ቀጠሮው፡ አንዲት ሰዓት እንኳ ሳያሳልፍ ተወለደ!" ብለን እያወጅን፡ እንዴት፡ ከመስከረም ፩ ቀን በኋላ፡ አራት ወሮችን ቆይተንና አሳልፈን፡ በታኅሣሥ ፳፰ ወይም ፳፱ ቀን ተወለደ ብለን፡ እንደገና በዓሉን እናከብራለን?

ይህን ግዙፍ ስሕተት የፈጸመ ማነው? ግብፃውያኑ ድሜጥሮስና አቡሻህር የተባለው የቁጥር ሊቃቸው? ወይስ ሌላ? ወይስ፡ በእነርሱ ኾነ በሌላ፡ ኾን ተብሎ፡ በተንኰል የተደረገብን ሴራ ነበር? ሊኾንና ሊታረቅ የማይችለውን፡ ይህን፡ ምስቅልቅል ድርጊት፡ እንግዴህ፡ ለማቃረብና ለማስማማት የሚሞከረው እንዴት ነው? የሚሞከረውስ ማነው? እኛ ራሳችን፡ ኢትዮጵያውያን? ወይስ የሌሎችን፡ የባዕዳንን መምሪያ እንጠብቃለን?

ይህ አንሦ ኖርዋል? ግብፃውያን ባመጡብን ጣጣ፡ የልደቱን ቀን፡ በየአራት ዓመቱ፡ በዘመነ ዮሐንስ፡ ከታኅሣሥ ፳፱፡ ወደኋላ፡ ወደታኅሣሥ ፳፰ ቀን "ይመለስ" እየተባለ የሚፈጠረው ውዝግብ እንዲጨመር የተደረገው? ይህን ድርጊት "ትክክል ነው" ብለው አምነው የተቀበሉ ወገኖች ካሉ፡ ታዲያ ለምንድነው፡ በዚያው ዓመት ውስጥ ተቀምረው የተወሰኑትን፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ የጌታንና የእመቤታችንን በዓላት፡ በየአራት ዓመቱ፡ ወደኋላ፡ በአንድ ቀን እንዲቀነሱ ያላደረጉት? የጌታ የልደት በዓል ቀን፡ እንዲህ፡ በአንድ ቀን ተቀንሶ፡ ከታኅሣሥ ፳፱፡ ወደኋላ፡ ወደታኅሣሥ ፳፰ ቀን ከተመለሰ እኮ፡ ሌሎቹ ኹሉ፡ የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት፡ እንዲሁ፡ በአንድ ቀን፡ በግድ፡ ወደኋላ መሸጋሸግ አለባቸው። ስለዚህ፡ ከዚህ ኹሉ የማያስፈልግ ውዝግብና ችግር ለመዳን፡ ሊኾን የሚገባው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው፡ አንድ ጊዜ ብቻ ስለኾነ፥ ተወልዶም፡ ተልእኮውን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ስለፈጸመ፥ በየዓመቱ የሚከበረው፡ የልደት በዓሉም፡ በመታሰቢያነትና ለመታሰቢያነት ብቻ ስለኾነ፡ በየአራት ዓመቱ፡ አንድ ቀን እየተቀነሰ እንዲከበር ማድረጉን መተውና በዚያው በታኅሣሥ ፳፱ ቀን እንዲጸና፥ ወይም፡ "ተገቢ ነው" ተብሎ፡ ወደፊት የሚወሰን ቢኾን፡ በመስከረም ፩ ቀን እንዲውል ማድረግ ብቻ ነው።

ታዲያ፡ ሊቃውንቶቻችን፡ "የልደት በዓል፡ በየአራት ዓመቱ፡ በታኅሣሥ ፳፰ ቀን ሊውል ይገባዋል" በሚለው፡ አወዛጋቢ ውሳኔ ምክንያት፡ የተፈጠረውን፡ ይህን ትንሹንና ቀላሉን ጉዳይ፡ ከላይ በተገለጸው መልክ፡ ለባዕዳኑ ግብፃውያን አለቀቃቸው፡ በትክክል አስረድተው መቋቋም ሲችሉ፡ ይህን ማድረግ ያቃታቸው ከኾነ፡ ይህን ትልቁን፡ የዘመን መለወጫ የኾነው የልደቱ ቀን፡ እንደጥንቱ፡ "እንደኢትዮጵያኑ ሥርዓት፡ በመስከረም ፩ ቀን መጽናት አለበት" ብለው፡ እንዴት ሊያስረዱና ሊያስተካክሉ ይችላሉ?

## ኢትዮጵያ፡
## ስለዘመን አቆጣጠርዋ
## ግብፃውያንን ስትፋረድ!

እግዚአብሔር የሠራውንና ኢትዮጵያውያን፡ በቃል ኪዳን ታማኝነታቸው ጠብቀው ያኖሩትን ሥርዓት ለማናጋት መሞከር፡ ውጤቱ ይህን የመሰለውን ዝብርቅርቅ ኹኔታን ማስከተል ነው፤ ስለዚህ ነው፡ ይህ ችግር የተፈጠረው። ይህንንም ችግር የፈጠሩት፡ የወዳጅ ጠላቶቻችን፡ ግብፃውያን መኾናቸው፡ ስለባሕረ ሓሳቡ፡ በዋቢነት የሚጠቀሰው ድሜጥሮስ፡ ራሱ ያስረዳል። ይኹን እንጂ፡ እርሱም ቢኾን፡ በተለይ፡ የጌታን የልደት ቀን በሚመለከት፡ በተፈጸመው ስሕተት፡ ራሱን፡ ከተጠያቂነት፡ ነጻ አድርጎ የሚገኝበትን ምክንያት፡ ዝቅ ብለን እንመለከታለን።

በሌሎቹ ሥራዎቻቸው የምናደንቃቸው፡ የእኛ ሊቃውንት ግን፡ የዛሬዎቹ ጭምር፡ ይህንኑ ስሕተት ተቀብለው፡ እንዲህ ሥር ሰድዶ ይቀጥል ዘንድ፡ ዝም ብለው በመመልከታቸው፡ ከወቀሣው ሊያመልጡ የሚችሉ አይመስለኝም።

ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው የተቀበሉት፡ በቃል ኪዳን የጸናውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠውን ሃይማኖታቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ሥርዓታቸውን ጭምር ስለኾነ፡ እኒህን፡ ሕያዋን ቅርሶቻቸውን፡ በሰውኛ እውቀትና ብልሃት ሊያሻሽሉ፡ ወይም ሊለውጡ ቀርቶ፡ ከቶ ሊያስቡትም አይሞክሩትም። እንደህልውናቸው ኹሉ፡ በዘመን አቆጣጠር ስልታቸውም፡ በሌሎቹና በጥንቶቹ ግብፃውያን ላይ ሳይቀር፡ ቅድሚያ ያላቸው መኾኑ፡ ጠብቀው በኖሩት፡ የትውፊትና የቅርስ ይዞታቸው ይታወቃል። ለዚህም፡ ግዙፉ ማስረጃ፡ የጥንቶቹ ግብፃውያን፡ የዘመን አቆጣጠራቸውን ባህል፡ የመሠረቱት፡ በታላቁ የዓባይ ወንዝ ውሃ ምልዓትና ጉድለት ላይ መኾኑ ነው።

የዓባይ ወንዝ ምንጭ ባለይዞታዎች፥ ጠባቂዎችና ባለአደራዎች የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ በአዳምና ሔዋን ከሚጀምረው ህልውናቸው አንሥቶ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ ፭ሺ፭፻ኛው ዓመተ ኵነኔ እስከተፈጸመባትና አዲሱ ዓመተ ምሕረት እስከተተካባት ቅጽበት ድረስ፥ ከዚያም ወዲህ፡ ሰዓታቸውን፥ ቀናቸውን፥ ሳምንታቸውን፥ ወራቸውንና ዓመታቸውን ለመቁጠር፡ አንድ ብለው የሚነሡበት ምልክት፡ የዓባይ ውኃ፡ በክረምቱ ዝናብ ምክንያት፡ ከመጨረሻው ምልዓቱ ደርሶ፡ የመቀነስ ርደቱን ማሳየት የሚጀምርበትን ዕለት ነበር። ያንንም ዕለት፡ "መስከረም ፩ ቀን" ብለው ሠይመው፡ ዓመቱና ወሩ፥ ዕለቱና ሰዓቱ የሚብቱበት (የሚጀምሩበት) እንዲኾን ወስነውታል።

በግብፃውያን ምድረ በዳ እየፈሰሰ፡ ሕዝቡን የሚመግበው፡ ይኸው፡ በኢትዮጵያ የዝናብ ውኃ የሞላው፡ የዓባይ ወንዝ፡ ከመልካው አፍ አልፎ መፍሰሱን፡ መቀነስ የሚጀምርበት ጊዜ፡ ይኸው ቀን በመኾኑ፡ እነርሱም፡ ከኢትዮጵያውያን ባገኙት እውቀት፡ የአዲስ ዓመታቸው መግቢያ፡ በዚሁ ዕለት እንዲኾን አድርገዋል።

እዚህ ላይ፡ ኢትዮጵያ፡ እንደዛሬው ሳይኾን፡ በዚያን በጥንቱ ጊዜ፡ ስፋትዋ፡ እስከአስዋን ደርሶ፡ የዛሬዪቱን ግብፅ የምትዋሰን፡ ድንበረተኛ ብቻ ሳትኾን፡ ራስዋን፡ ግብፅንም ጭምር ጠቅልላ ታስተዳድር እንደነበረ፡ ማስታወስ ያሻል፤ በቅርቡ የተፈጠረችውን ሱዳንን ትቶ ማለት ነው። ስለዚህ፡ ከዚያ ወዲህ የደረሰውን፥ በዛሬዎቹ የሃይማኖት ወገኖች በተባሉት ግብፃውያንም የተፈጸመውን እንተወውና፡ በዚህ፡ በዘመን አቆጣጠር ሥርዓት ረገድ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በግብፃውያን ላይ ቅድሚያ እንደነበራቸው፡ ቀደም ብሎ የተገለጸው ቃል ያመለክታል።

ይህ፡ የኢትዮጵያውያን አቋም፡ እስከዛሬ ጸንቶ የኖረውና ዛሬም የማይናወጸው፡ ምክንያቱ፡ ይኸው፡ የሰዓትና የቀን፥ የሳምንትና የወር፥ የዓመትና የዘመን አቆጣጠራቸው፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚገኘውን፡ የእግዚአብሔርን የተፈጥሮ ሥርዓት ሳይለቅ በመቀጠሉ ነው። እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፡ ከዚህ አቋሙ እንዲነዋወጽ ለምን ተደረገ? ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ያው የታወቀውና የተለመደው ሲኾን፡ እርሱም፡- "ኢትዮጵያን፡ ቀደምት የሚያደርጓትን የማስረጃ ምልክቶች ኹሉ፡ ደብዛቸውን ሳይቀር፡ ጨርሶ ለማጥፋት ነው!" በሚል፡ አጭር ቃል ይጠቃለላል።

ይህን እውነት ለማረጋገጥ: አንድ: ሊያስተሐቅሩት የማይቻለውን: ዛሬም ቆሞ የሚጮኸውን ምስክር ማቅረብ ይቻላል:: ያም: በኢየሩሳሌም: ዐፅመ ርስት የኾነውን: የኢትዮጵያውያን ይዞታ: በኃይልና በሐሰት ነጥቀው ወስደው: ለሚሞግቱን: የሃይማኖት ወገኖች ለተባሉት አብያተ ክርስቲያን: ቀንደኛ መሪ የኾኑት እነማን ናቸው? እኒሁ: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ካህናት፥ ጳጳሳትና መሪዎቻቸው አይደሉምን?

ስለዚህ: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተጠሪዎች: ኢትዮጵያ: በኢየሩሳሌም የዓጽመ ርስት ይዞታዎቿና በዚያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ: እስካሁን ሲፈጽሙት የኖሩትን፥ አሁንም: እየፈጸሙት ያለውን ክፋት፥ ጥፋትና በደል ሲመለከቱት: በየሌሎቹ ዘርፎች: በየመልኩ ካደረሱት በላይ: በዚህ በዘመን አቆጣጠር ረገድ በተፈጸመው ስሕተትም: ከፍተኛውን የተፅዕኖ አስተዋጽዖ "አላደረጉም!" ሊባል ከቶ አይቻልም::

## ኢትዮጵያ:
## ስለባሕረ ሓሳቧና ስለጌታ የልደት ቀን:
## ግብፃውያንንና ክርስቲያኑን ዓለም ስትፋረድ!

ይህን: እየቀጠለ ያለውን: ግብፃውያን: በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያካኼዱትን: ግልጽ የማጥቃት ሥራ: በቋሚ ማስረጃነቱ እንዲመሰክር: እዚህ ላይ: ባጭሩ ልግታውና: ስለተነሣንበት: ስለጌታ የልደት በዓል ቀን: ሦስት ቁም ነገሮችን ወደማውሳቱ ልመለስ!

## የጌታ የልደቱ ቀን "አይታወቅም" በሚል ምክንያት:
## ከአረማውያኑ የበዓል ቀን ጋራ ተጣምሮ መከበሩ::

በአንደኛው ቁም ነገር እጀምራለሁ! የዓለሙ መድኃኒት: ኢየሱስ ክርስቶስ: በእውነተኛው: የኢትዮጵያውያን ቀን: ይኸውም: መስከረም ፩ ቀን: ከድንግል ማርያም ስለተወለደ: "ዓመተ ፍዳ ተሽሮ: ዓመተ ምሕረት ተተካ!" ብለን፥ ታላቅ የዐውደ ዓመት በዓልም አድርገን: ለዚህ ሳበቃን አምላክ: ከአራሲቱ ቅድስት እናቱና ከጠባቂዋ ጻድቅ ዮሴፍ፥ ከመላእክትና ከእረኞች፥ ከሰብአ ሰገልና ከእንስሶች ጋር: በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ ኾነን፥ በምሥራች ዝማሬና በሐሴት ቃል: የደስታ ምስጋናችንን ካቀረብን በኋላ: ለአራት ወራት ቆይተን: በታኅሣሥ ፳፱ ቀን: እንደገና እንድናከብረው ስለተደረገው በዓል: እስቲ ጥቂት ጠለቅ ብለን እንመልከት!

በአሁኑ ጊዜ: የጌታ የልደት በዓል: በመላው ዓለምና በቤተ ልሔም የሚከበረው: በታኅሣሥ ወር በአንድ: በተወሰነ ቀን ሳይኾን: በዚሁ ወር መጨረሻና በጥር ወር መጀመሪያ ባሉት ቀኖች አካባቢ: በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት: ቢያንስ ቢያንስ: በአራት የተለያዩ ዕለታት ነው:: በዚህም: የሃይማኖት ወደረኞቻችን: አይሁድም፥ እስላሞችም፥ አረማውያንም፥ ሃይማኖተ ቢሶችም እንደሚያፌዙብን ይነገራል፤ ይታያልም::

ምዕራባውያንና አብዛኛዎቹ ምሥራቃውያን ክርስቲያኖች፡ የልደትን በዓል የሚያከብሩት፡ በእነርሱ የዘመን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፥ (በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር፡ በታኅሣሥ ፲፮) ሲኾን፡ ኢትዮጵያውያንና ጥቂቶች ምሥራቃውያን ክርስቲያኖች ደግሞ፡ ያው፡ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን፡ በእነርሱ አቆጣጠር፡ በJanuary 7 (ጃንዋሪ ፯)፥ ሌሎቹም የቀሩት አናሳ ወገኖች፡ በእነዚህ ቀኖች መካከል ባሉ፡ የተለያዩ ኹለት ዕለታት ያከብራሉ።

በምዕራባውያን የሥነ ከዋክብት፡ ማለትም፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን፡ "በትክክል አይታወቅም" የሚለው የግምት አስተሳሰብ፡ እስከዛሬም እንደጸና ይገኛል። ከዚህ የተነሣ፡ ከቀድሞ ጀምሮ፡ የልደቱ ቀን፡ "በዚህ ዕለትና ዓመት ይኹን!" እያሉ የወሰኑት፡ በሥጋ ፍልስፍናና በዘፈቀደ፥ በምናልባትና በመላምት ብቻ መኾኑ ተረጋግጧል። እኒህ፡ የምዕራባውያን ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት፡ የዱሮውን የሮማውያንን አረማዊ ባህል አስወግደው፡ በእርሱ ሥፍራ፡ B.C. (Before the Birth of Christ) "ከክርስቶስ ልደት በፊት" እና A.D. (Anno Domini) "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" የሚለውን የዘመናት መክፈያ ሥርዓትን ለመተካትና ለመመሥረት የሚያስችለውን፡ ትክክለኛውን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን፡ ማለትም፡ አልቦ (zero ዜሮ) ቁጥር የሚኾነውን ጊዜ፡ በቁርጥ ለማግኘት ስላቃታቸው፡ ይህን ዕለት፡ ፈጥረው፡ በዘፈቀደ እንደወሰኑት ታውቋል፤ ለዚህም፡ በዋቢነት፡ ስሙ የሚጠቀሰው፡ Dionysius Exiguus ዲዮኒሲዩስ ኤክሲጉዑስ የተባለው፡ ጣልያናዊ፡ የካቶሊክ መነኩስ ነው። እርሱም ይህን አሳብ ያመነጨው፡ እንደእነርሱ አቈጣጠር፡ ከ፭፻ እስከ ፭፻፳፭ ዓመተ ምሕረት ባለው ዘመን ውስጥ ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በነቢያት ትንቢት መሠረት ይወለድ ዘንድ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ማሕፀን ኾኖ፡ በጻድቁ ቅዱስ ዮሴፍ ጠባቂነት፡ ከገሊላ ናዝሬት መኖርያቸው፡ ወደቤተ ልሔም በረት የተጓዙት፡ የሮማውያን ገዢ የነበረው፡ አውግሥጦስ ቄሣር፡ በግዛቱ ውስጥ የሚኖረው፡ ሰው ኹሉ፡ በየትውልድ ቦታው እየኼደ እንዲመዘገብ፡ ባወጀው ትእዛዝ መነሻነት መኾኑ ይታወቃል። ያ ትእዛዝ የታወጀበት ጊዜም፡ ምዕራባውያን፡ "የክርስቶስ የልደት ቀን ነው" ብለው የወሰኑትን፡ የዘመን አቈጣጠራቸውን ቀመር ተከትሎ ሲሰላ፡ "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" በ፩ኛው ዓመተ ምሕረት ላይ የዋለ ኾኖ ተገኝቷል።

ከእኒህ ኹሉ ማስረጃዎች ጋር፡ የጌታን የልደት በዓል ለማክበር ሲባል፡ የልደቱ ቀን፡ ከላይ የተጠቀሱትን ዕለታት በሚያካልለው፡ በዚህ፡ በአንድ ሰሞን፥ በተለይም፡ በእነርሱ የቀን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፡ እንዲውል የተደረገበት፡ አንድ፡ ሌላ፡ የታወቀ ዋና ምክንያት ደግሞ አለ! ይኸውም፡ በእምነታቸው፡ ገና አረማውያንና አሕዛብ የነበሩት፡ ሮማውያንና የቀሩት የአውሮጳ ሕዝቦች፡ የጣዖትና የባዕድ አምልኳቸውን ልደት፡ ወይም፡ የመመሥረቻ ቀን ምክንያት በማድረግ፡ በተመሳሳይ መልክ ይፈጽሙት ከነበረው፡ የፈንጠዚያ በዓላቸው ጋር፡ አዲሱ የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት፡ አብሮ ኾኖ በዚሁ ሰሞን እንዲከበር፡ የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች፡ በቅን ዓላማ መፈለጋቸው ነው።

ከጌታ ልደት ጋር ተመሳሳይነት ነበራቸው የተባሉት፥ በዚያው ዕለት፡ ማለትም፡ በእነርሱ የቀን አቆጣጠር፡ በDecember 25 (ዲሴምበር ፳፭)፥ ወይም በዚያው ሰሞን የሚውሉትና የሚከበሩት፡ እነዚያ፡ የአረማውያኑ በዓላት፡ ለምሳሌ ያህል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፡- ፩ኛ፡ ሮማውያን፡ ስሙን በመታሰቢያነት፡ January (ጃንዋሪ) ብለው፡ ለዓመቱ የመጀመሪያ ወር የሰጡለት፡ Janus (ጃኑስ) የተባለው ጣዖታቸው በዓል፤ ፪ኛ፡ Natalis Solis Invicti (ናታሊስ ሶሊስ ኢንቪክቲ)፡ ማለትም፡ "ያልተደፈረችው ፀሓይ የልደት ቀን" የሚለው የልደት በዓል፤ ፫ኛ፡ "ሚፅራ" የምትባለው፡ የኢራናውያን የምሥጢር ጣዖት፡ የልደት በዓል ቀን፤ ፬ኛ፡ የአረማውያኑ በዓል፡ ጥንቱኑ፡ ኾን ተብሎ፡ እንዲውል የተደረገው፡ በበረዶው ወራት መካከል ኾኖ፡ ያም ወቅት፡ አረማውያኑ፡ ለክረምትና ለፀሓይ፡ በጥድ ዛፍ የሚያቀርቡትን የባዕድ አምልኮ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙበት፥ ሐሤት የሚያደርጉበትና የመልካም ምኞት ስጦታን የሚለዋወጡበት ታላቅ በዓል።

እንግዲህ፡ እዚህ ላይ፡ በዚያን ዘመን፡ አረማውያንና አሕዛብ የነበሩት ሮማውያንና አውሮጳውያን፡ የክርስትናን እምነት እንዲቀበሉ በተደረገበት ጊዜ፡ ይህንኑ አዲስ የክርስትና ሃይማኖታቸውን በበለጠ እንዲያጸኑት ለማበረታታት ሲባል፡ በጊዜው የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ልኡካንና መሪዎች፡ የተጠቀሙበትን ዘዴ፡ በቀላሉ መመልከት ይቻላል፤ ቅዱስ ጳውሎስ፡ ጣዖት አምላኪዎች ለነበሩት ለግሪክ ሰዎች፡ በአቴና ከተማ፡ በአርዮስፋጎስ አደባባይ ተገኝቶ በሰበከላቸው አቀራረብ ዓይነት ማለት ነው። ይኸውም፡ "ያ፡ በዛፍና በልዩ ልዩ ምልክቶች ታመልኩት የነበረው አምላክ፡ እነሆ፡ ሰው ኾኖ ተወልዶ፡ ከሰይጣን ገዢነት፥ ከኃጢአት ቀምበርና ከሞት ዕዳ አዳነን! የእርሱ ልጆች የምንኾንበትን ጸጋን ሰጥቶን፡ የዘለዓለም ሕይወት ወራሾች አደረገን!" በማለት፡ በዚያው፡ የአማልክቶቻቸውን የልደት ወይም የመታሰቢያ በዓላት በሚያከብሩበት ቀንና በዚያው በጥንቱ፡ የአምልኮ ምልክታቸው፥ ባህላቸውና ሥርዓታቸው ተቀይሮ እንዲቀጥል ማድረጋቸው ነው። ይህ ኹሉ፡ በራሳቸው፡ በምዕራባውያኑ የዝክረ ነገር መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል።

በምዕራባውያን ዘንድ፡ ዛሬ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የልደቱ ቀን፡ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት እንዲውል የተወሰነው፥ ምልክቱና ሥርዓቱም፡ በተጌጠ የጥድ ዛፍ እንዲኾን የተደረገው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን ማጤን፡ በተለይ፡ ለኢትዮጵያውያን ያስፈልጋቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ከኪዳነ ኦሪት እምነትና ሥርዓት፡ ወደኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የክርስትና ሥርዓት በተሸጋገረበት ጊዜ፡ በታቦተ ጽዮን አማካይነት ያካሄድ የነበረውን አምልኮተ እግዚአብሔር፡ በዚያው ልማዱ እንዲቀጥል ለማድረግ፡ ኢትዮጵያውያን አባቶች፡ በአዲስ ኪዳኑ ሥርዓት የተቀረጸ ጽላትና ታቦት እንዲዘጋጅ ወስነው፡ ይኸው እስከዛሬ፡ በየቤተ መቅደሱ እንዲገኝ እንዳደረጉት ማለት ነው።

## የጌታ የልደቱ ቀን:
## በዚያ: በበረዶው ወራት ያለመኾኑ ማረጋገጫዎች::[፸]

ኹለተኛውን ቁም ነገር ደግሞ: እስቲ እንመልከት! ከላይ: ቀደም ብሎ የቀረበው ሐተታ: የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ: የልደት ቀን በትክክል የማይታወቅ መኾኑን፥ ከዚህ የተነሣም: እንዲከበር የተወሰነው: ወደክርስትና ሃይማኖት የተመለሱት አዲሶቹ ምእመናን: ቀድሞ በአረማዊነት ይፈጽሙት የነበረው: የበዓላቸው ቀንና ባህል ሳይፋለስ ተጠብቆ እንዲቀጥል በማድረግ: የጌታም የልደት በዓል: ከዚያ ጋር አብሮ በDecember 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፭) ቀን መከበሩ: ጠቃሚና መልካም ዘዴ ኾኖ በመገኘቱ መኾኑን በግልጽ ያሳያል::

የዚህ ሐተታ ፍሬ ነገር ሲጠቃለል: "ጌታ የተወለደበት ነው" ተብሎ የሚከበረውን ቀን: አጠራጣሪ የሚያደርግ: የስሕተት ጭብጥ መኖሩን የሚያመለክት ከመኾኑ ጋር: ወደሌላ የማስረጃ ፍለጋና ምርምር እንድናመራ የሚጋብዝ: አስተማማኝ ፍንጭን ያበረክትልናል:: ምርምራችንም: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: "ተወልዶበታል" የሚባለው: December 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፭) ቀን: ቤተ ልሔም በምትገኝበት: በሰሜኑ ክፍለ ዓለም ክልል: የክረምትና የበረዶ ወራት ውስጥ የሚገኝ ስለኾነ: "ያ: የክረምትና የበረዶ ወራት: በእርግጥ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን የያዘ ነበር ወይ?" የሚለውን ጥያቄ መልስ መስጠት የሚችል ሐተታን ማቅረብ ይኾናል::

ለዚህ ሐተታ መነሻ የሚኾነን ደግሞ: ቀጥሎ ያለው የወንጌል ቃል ነው: *"በዚያም ወራት: ዓለሙ ኹሉ እንዲጻፍ: ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች:: ቄሬኔዎስ: በሶርያ አገር: ገዥ በነበረ ጊዜ: ይህ: የመጀመሪያ ጽሕፈት ኾነ:: ኹሉም: እያንዳንዱ: ይጻፍ ዘንድ: ወደከተማው ሄደ:: ዮሴፍም ደግሞ: ከዳዊት ቤትና ወገን ስለነበረ: ከገሊላ: ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ: ቤተ ልሔም ወደምትባል: ወደዳዊት ከተማ: ወደይሁዳ: ፀንሳ ከነበረችው: ከእጮኛው ማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ:: በዚያም ሣሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ! የበኵር ልጇንም ወለደች! በመጠቅለያም ጠቀለለችው! በእንግዶች ማደሪያም: ሥፍራ ስላልነበራቸው: በበረት አስተኛችው:: በዚያም ምድር: መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ::"*

አውግስጦስ ቄሣር: ይህን ትእዛዝ ያስተላለፈው: *"አንቺ ቤተ ልሔም! የይሁዳ ምድር! ከይሁዳ ገዥዎች ከቶ አታንሺም! ሕዝቤን: እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን: ከአንቺ ይወጣልና!"* የሚለው: የእግዚአብሔር የትንቢት ቃል እንዲፈጸም ለማድረግ መኾኑ የታመነ ነው::[፹፩]

ይኹን እንጂ: አውግስጦስ ቄሣር: በዘመኑ እጅግ ሰፊ በነበረው ግዛቱ ውስጥ ይኖር የነበረው: ያ ኹሉ እልፍ አእላፋት ሕዝቡ: ዝናሙና በረዶው: በዚያ ክፍለ ዓለም በሚከፋበትና በሚበረታበት: በክረምቱ ወራት: ከያለበት እንዲንቀሳቀስ ያደረገውን: ያን የመሰለውን ትእዛዝ ያስተላልፋል ብሎ እንዴት ሊታሰብ ይችላል?

ወራቱ፡ በእርግጥ ክረምት ከኾነ፡ ቄሣራዊዉን ትእዛዝ በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ፡ በእያንዳንዱ ዜጋና ቤተሰብ፥ በመንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞችም ላይ ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን እንግልትና ጫና፡ በድንግል ማርያምና በጠባቂዋ በዮሴፍ ላይ በደረሰው ችግር፡ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ታዲያ፡ ልትወልድ እንደተቃረበችው፡ እንደእመቤታችንና እንደጠባቂዋ ዮሴፍ፡ ከመኖርያ ቀበሌያቸው ተነሥተው፥ እንደዛሬው እንኳ፡ ተሽከርካሪና መጓጓዣ ባልነበረበት ኹኔታ፡ ጓዛቸውን ጭነው ወይም ተሸክመው፡ ያን ያህል፥ ከዚያም ሊርቅ የሚችል የእግር መንገድ ጉዞ ስለሚያደርጉ ዜጎቹ፡ ያ መንግሥት አያስብምን? ለዜጎቹ የማያዝን እንኳ ቢኾን፡ ትእዛዙን ለማስፈጸም፡ መንግሥቱ ራሱ፡ የሚያደርገው ዝግጅትና ድርጅት እንዴት ሊከናወንለት ይችላል? ዛሬ፡ የመገናኛና የማጓጓዣ ዘዴዎች ተከናውነው በሚገኙበት ጊዜ እንኳ፡ የሕዝብ የምርጫ ሥርዓት የሚካሄደው፡ የወራቱ አየር ጠባይ፡ ተስማሚ መኾኑ በተረጋገጠበት፡ የበጋ ወራት እንደኾነ ይታወቃል።

የአይሁድ ሎሌዎችና የጲላጦስ ወታደሮች፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዘውና አሥረው፡ ወደሊቀ ካህናቱ ግቢ የወሰዱበት የምሽቱ ጊዜ፡ *"ብርድ ነበርና፡ አገልጋዮችና ሎሌዎች፡ የፍም እሳት አንድደው፡ ቆመው ይሞቁ ነበር፤ ጴጥሮስም ደግሞ፡ ከእነርሱ ጋር ቆሞ፡ ይሞቅ ነበር"* የሚለውን የመሰለ የወንጌላዊ አገላለጽ፡ በዚህ፡ በጌታ የልደት ጊዜ አልተወሳም። ጌታ የተወለደበት ወራት፡ እንኳንስ የክረምት ዝናምና በረዶ ይቅርና፡ ብርድ እንኳ የነበረ መኾኑን፡ የሚያስረዳ፡ አንዳችም ምልክት የለም። ቢኖርም እንኳ፡ ወራቱ፡ ምንም ዓይነት፡ የክረምት ምልክት የሌለው፡ እንዲያውም፡ ፍጹም በጋ መኾኑን የሚያረጋግጥ ኾኖ ይገኛል። ይኸውም፡ ወንጌላዊው ሉቃስ፡ ስለልደቱ ኹኔታ፥ በጊዜው ስለነበረው፡ የአየሩ ጠባይና ስለተፈጸመው ተአምራዊ ድርጊት፡ በጻፈው ዜና ውስጥ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰው፥ በተለይም፡ *"በዚያም ምድር፡ መንጋቸውን፡ በሌሊት ሲጠብቁ፡ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ።"* የሚለው ቃልና ምንም ችግር ያልነበረበት፡ የሰብአ ሰገል የመዘዋወር ጉዞ፡ ለዚህ ምስክርነት ይበቃል። ይህም፡ ወራቱ፡ በጋ እንጂ፡ ዝናምና በረዶ የሚወርድበት፡ ክረምት፡ ማለትም፡ የታኅሣሥ ወር ያለመኾኑን ያረጋግጣል። ለዚህ ጉዳይ፡

፹፪

ከወንጌላዊው ያለፈ፡ ሌላ ምስክር አያሻም።

"ቍር ወይም ብርድ ነበረ" ተብሎ የሚሰጥ የትርጓሜ ትችት ቢኖር እንኳ፡ ያ ቍር ወይም ብርድ፡ በአገራችን፡ በጥቅምትና በጥር ማታና ሌሊት የሚወርደውን የሚመስል መኾን ይኖርበታል። የሌሊት ቀዝቃዛ ነፋስ፡ ወዲያና ወዲህ በሚነፍስበት፥ ዝግ ግድግዳ በሌለውና በፍርግርግ በተከለለ በረት ውስጥ፡ ብርድ የለም እንዴት ሊባል ይቻላል? ከዚህ የተነሣም፡ በበረቱ የነበሩ እንስሳት ሳይቀሩ፡ "በእስትንፋሳቸው አሟሟቁት" ተብሎ በተጨማሪ ሓተታ ቢተረጐም፡ አያስደንቅም።

እንግዴህ፡ በዚህ ኹሉ ማስረጃ፡ ያ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ወራት፡ ቤተ ልሔምን፥ መካከለኛው ምሥራቅንና መላውን አውሮጳን ባቀፈው በሰሜኑ ክፍለ ዓለም፡ የፀሓይ ብርሃንና ሙቀት የሚሰፍንበት፡ በእኛ፡ የክረምት ወራት፥ በእነርሱ ደግሞ፡ የሓጋይ ወይም የበጋ ወራት መኾኑ አሌ ሊባል ከቶ አይቻልም።

የመስከረም ወር፡ በዚያ ክፍለ ዓለም፡ ተስማሚ የአየር ጠባይ የሚታይበት፡ የበጋው ወራት ማብቂያ ስለኾነ፡ በትክክል ሊታወቅ ያልተቻለው፣ ነገር ግን፡ በሰዎች፡ የምናልባትና የመላምት ውሳኔ፡ በDecember 25 (ዲሴምበር 'ታኅሣሥ' ፳፭) ቀን እንዲውል የተደረገው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀን፡ እውነተኛውና ትክክለኛው፡ በኢትዮጵያኑ የጊዜ አቆጣጠር፡ "መስከረም ፩ ቀን ነው!" ብለን መደምደም ይኖርብናል።

## የጌታ የልደት ጾምና በዓል፡ እንደሌሎቹ፡ የቀመር ተውሳክ የሌላቸው መኾኑ።

በመጨረሻ፡ ሦስተኛውን ቁም ነገር እንመለከታለን! ይህም፡ የእግዚአብሔር ሥነ ፍጥረት፡ ተዘርዝሮና ተጠቃልሎ የሚነገርበትን፣ ከራብዒትና ከኬክሮስ ተነሥቶ፡ እስከዓመትና ዘመናት የሚደርሰው የጊዜ አቆጣጠር፡ በሒሳብ ተሰልቶ የሚወጣበትን፡ ባሕረ ሐሳብ የሚባለውን ሥርዓት የሚመለከተው ነው። በየዓመቱ፡ ምድር ከምታበቅለው፡ የአትክልት፣ የአዝርእትና የዕፀዋት ዓይነት መካከል፡ ከፈጣሪ ለተገኘው በረከትና ለእርሱ ለሚቀርበው ምስጋና ምልክት ይኾን ዘንድ፡ ስንዴና የወይን ፍሬ (ዘቢብ)፡ ጧፍና ዕጣን፣ በመሰበ ወርቅ ኾኖ፣ የእንቍጣጣሽ አበባ ጉንጉን ጭምር፡ በቤተ ክርስቲያን ቀርቦ፡ ዐውደ ዓመት በኾነው፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ የዚያን አዲስ ዓመት፡ በዓላትና አጽዋማት፡ በዚሁ ባሕረ ሐሳብ አማካይነት፡ በአዋጅ ያሰሙበታል።

ለዚህ ባሕረ ሐሳብ ቅመራ፡ መሠረትና መነሻ ኾኖ፡ የዘመኑ፡ የሰዓትና የዕለት፣ የመዓልትና የሌሊት፣ የወርና የዓመት አቆጣጠር፤ እንዲሁም፡ የአጽዋማትና የበዓላት ቀኖች አመዳደብ የሚወሰንበት፡ የመጀመሪያው መግቢያ "መስከረም" ነው። የየአንዳንዱ ቀን፡ የመዓልትና የሌሊት ልክ ታውቆ የሚወጣበት መቀመሪያ፡ "አበቅቴ" የሚባለው መሥፈሪያ ሲኾን፤ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ዕለት የሚወስነው ደግሞ፡ "መጥቅዕ" ይባላል። ኹለቱም መሥፈሪያዎች፡ በየመልካቸው ተሰልተው ከወጡ በኋላ፡ የቀኑና የሌሊቱ ቁጥር፣ እንዲሁም፡ የዓመቱ የጾም መግቢያዎችና ማብቂያዎች ዕለታት፡ ይታወጃሉ። በዚህ አዋጅ ላይ፡ ከሰባቱ አጽዋማት መካከል፡ የገና ጾም የሚባለው፡ ጾመ ነቢያትና ከእርሱ ጋር የተያያዘው፡ "ጾመ ገሃድ" የሚባለው፡ የጥምቀት ዋዜማ ጾም፣ እንዲሁም፡ ጾመ ፍልሰታ፣ ደግሞ፡ ከዓበይት በዓላት መካከል፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የጽንሰቱና የልደቱ፣ የጥምቀቱም ዕለታት ብቻ ተለይተው ይቀራሉ። ለምን? የዚህ ምክንያት ምንድር ነው?

በባሕረ ሐሳቡ ተቀምረው ወጥተው የሚታወጁት አጽዋማት፡ ጾመ ኢትዮጵያ (ጾመ ነነዌ)፣ ዓቢይ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያት (የሰኔ ጾም)፣ ጾመ ድኅነት (ረቡዕና ዓርብ) ሲኾኑ፡ የጌታችን በዓላት ደግሞ፡ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገትና በዓለ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። ታዲያ! የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የትስብእቱ (የጽንሰቱ) እና የልደቱ፣ የጥምቀቱም በዓላት ቀኖች፣ ከእነርሱም ጋር የተያያዘው፡ የነቢያት ጾምና ጾመ ገሃድ፡ በዚህ በባሕረ ሐሳቡ ቅመራ ውስጥ ሊገቡ ያልቻሉበት ምክንያት፡ ከቶ ምንድነው?

ምክንያቱ፡ የጌታ፡ የልደቱ ቀን፡ ከመስከረም ፩ ቀን ተነሥቶ፡ ወደሌላ ዕለት ሊዛወር የማይቻል ከመኾኑ የተነሣ፡ በባሕረ ሓሳብ ውስጥ እንደተያዙት፡ እንደሌሎቹ አጽዋማትና በዓላት፡ ቀናቸው፡ የማይወርድና የማይወጣ፡ ማለትም፡ የማይነዋወጡ፥ ቋሚዎች ስለኾኑ አይደለምን? ወይስ፡ ይኸው፡ የጌታ፡ የልደቱ ቀን፡ ከእውነተኛው፡ ከመስከረም ፩ ቀን ተነሥቶ፡ አላገባብ፡ ወደታኅሣሥ ፳፱ ቀን በመቀየሩ፡ ቀውሱ ስለተፈጠረ ነው?

ለዚህ ኹሉ ጥያቄ፡ መልስ ለመስጠት፡ በኢትዮጵያውያን ባሕረ ሓሳብ ውስጥ፡ ስማቸው የሚጠቀሰውን፡ ግብፃውያኑን ድሜጥሮስንና አቡሻክርን፡ እንደተለመደው፡ እንደዋቢ አድርገን እንዳናቀርባቸው እንኳ፡ የጌታን፡ የጽንሰቱንና የልደቱን የበዓላት ቀኖች፥ ከእነርሱ ጋር የተያያዙትንም የአጽዋማት ቀኖች፡ ማለትም፡ ጾመ ነቢያትንና ጾመ ገሃድን፥ እንዲሁም፡ ጾመ ፍልሰታን ጨምረው፡ ከቅመራቸው ውጪ ስላደረጓቸው፡ እነርሱም ቢኾኑ፡ ራሳቸውን፡ ከስሕተቱ ነጻ ያደረጉ ይመስላል።

ታዲያ፥ ይኼ ኹሉ ምንን ያስረዳል? ያመለክታልስ? ለራሱ፡ ለኢትዮጵያኑ ባሕረ ሓሳብና ለአቆጣጠሩ፡ እንደመስከረሙ ወር፡ መሠረቱ እና መነሻው እርሱ፡ የጌታ፡ የልደቱ ቀን በመኾኑ አይደለምን? መሠረት ከተነዋወጸ ደግሞ፡ በእርሱ ላይ የቆመው ኹሉ ይፈርሳል። ስለዚህ፡ መሠረቱ፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ፡ በባዕዳኑ ዘንድ ሲፋለስ፥ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እስከዛሬ አልተነዋወጸም ማለት ነው። አዎን! እርሱ፡ ራሱ፡ መሠረቱ፥ ባለቤቱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዓለሙን በፈጠረባትና በተወለደባት ቀን፡ ራሱ ተመልሶ መጥቶ፡ ዓለሙን እስከሚያሳልፍባት ዕለት ድረስ፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ የጌታን የልደት በዓል የሚያደርገው፡ ይህ፡ የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተጠብቆ፡ ወደፊትም፡ ሳይነዋወጽ ጸንቶ ይቆያል።

የጌታ የልደቱ ቀን፡ በመስከረም ፩ ቀን መኾኑ፡ እንዲህ ከተረጋገጠ፡ የትስብእቱ (የጽንሰቱና የብሥራቱ) ወርና ዕለት፡ ወደኋላ፡ ፱ ወር ከ፭ ቀን መቆጠር ይኖርበታል፤ እርሱም፡ በታኅሣሥ ፩ ቀን ላይ ይወድቃል፤ በዚህ መሠረት፡ የብሥራቱ፥ የጾመ ነቢያትና የጥምቀቱ ወራትና ዕለታት፡ አሁን የሚውሉበትን ትክክለኛ ጊዜያት እንደያዙ ይቀጥላሉ ማለት ነው።

## በአረማዊነት ባህል ላይ የተመሠረተው
## የምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር፡
## ከኢትዮጵያውያኑ የሚለይበት ባሕርይና የደረሰበት ቀውስ።

ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ላይ የመሠረቱትን፡ ይህን የጊዜ አቆጣጠር ሥርዓት፡ ምዕራባውያን፥ አርቶዶክሳውያን የተባሉት አብያተ ክርስቲያናት ጭምር፡ በአረማዊው፡ ዩልዮስ ቄሣርና ጎርጎርዮስ (ግሬጎሪ) ፲፫ኛ በተባለው፡ በካቶሊካዊው ጳጳስ ስሞች እየሠየሙ፥ በየጊዜው እየለዋወጡና በመጨረሻ፡ ፰ ዓመታት ከ፲ ቀናት ያህል አክለውበት መቆየታቸው ይታወቃል። በዚህ የአቆጣጠራቸው ስልት፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን፡ ከ፬ እስከ፯ ዓመታት ለሚደርስ ዘመን፡ ከፍ አድርገው እንዲጨምሩ በመገደዳቸው፡ ይህን፡ ሰው ሠራሽ ቀውስ አስተካክለው ለማስታረቅ አቅቷቸው ሲባዝኑ ይገኛሉ። በዚህ፡ በእነርሱው አቆጣጠር፡ ጌታ፡ የተወለደው፡ "በ፬፥ በ፮ ወይም በ፯ ዓመተ ምሕረት ላይ ሳይኾን አይቀርም" ከማለት በስተቀር፡ እርግጠኛውን ቀን፡ በቁርጥ ሊወስኑ ሳይቻላቸው ቀርቷል።

ይህ ቀውስ የተፈጠረባቸው: የጌታን የልደት ዓመት: አንድ ብለው መቁጠር ከጀመሩ በኋላ: ያ: የዓመተ ምሕረት መነሻ ዘመን: በአረማዊነት ዘመናቸው: "ጁልያን" በሚል ስምና በተለያየ ስልት ይጠቀሙበት በነበረው የአቈጣጠር ሥርዓታቸው: በ፬÷ በ፮ ወይም በ፯ ዓመታት ላይ ውሎ ስላገኙት ነው:: ሌላው: ይህን ችግር የፈጠረባቸው ምክንያት: የምዕራባውያን የጊዜ አቆጣጣር: እንደኢትዮጵያውያኑ: በአንድ መሠረት ላይ ታንጾና በአንድ በተስተካከለ ሥርዓት ተቀምሮ የሚመራ ባለመኾኑ ነው:: ይህንንም: ከዚህ የሚከተለውን ማነጻጸሪያ ሓተታ ተመልክቶ መረዳት ይቻላል::

ኢትዮጵያውያን: "የእግዚአብሔር ገነት" ተተክላባት: አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት አገራቸው የምትገኘው: በምድር ማዕከል ወይም መቀነት ክልል ውስጥ ስለኾነ: የጊዜ አቈጣጠራቸው ሥርዓት: መዓልቷና ሌሊቷ: ዓመቱን ሙሉ: በ፲፪÷ በ፲፪ ሰዓታት: እኩል በተከፈለበት የአሠፋፈር ስልት ላይ ተመሥርቶ: የባሕረ ሓሳቡ ቅመራ: ሥርዓቱን ጠብቆ: ያለችግር ይካኼዳል:: ይኸውም: ወደኋላ: ወደረቂቃኑ ሳንኼድ: ከሣልሲት ተነሥተን: እስከዓመት ብንቈጥር እንኳ: ቀመሩ: የተስተካከለ ኾኖ እናገኘዋለን:: ማለትም: ፷ ሣልሲታት: ፩ ካልዕት (Second)÷ ፷ ካልዕታት: ፩ ደቂቃ÷ ፷ ደቂቃት: ፩ ሰዓት÷ ፳፬ ሰዓታት: ወይም ፷ ኬክሮስ: ፩ ዕለት ይኾናሉ፤ ፩ዱ ዕለት ደግሞ: ፀሓይ እንድትሠለጥንበት የተፈጠረችበት: ፲፪ ሰዓታትን የያዘው: የብርሃን ጊዜ: "መዓልት"÷ ጨረቃ እንድትሠለጥንበት የተፈጠረችበት: ፲፪ ሰዓታትን የያዘው: የጨለማ ጊዜ: "ሌሊት" ይባላል::

የመዓልቱ የጊዜ አቆጣጠር: የተፈጥሮውን ሥርዓት በመከተል: "ከቀትር በፊት" እና "ከቀትር በኋላ" ተብሎ: ፀሓይ: ጮራዋን በምትፈነጥቅበት: በንጋቱ ፩ ሰዓት ይጀምርና: በምትጠልቅበት: በምሽቱ ፲፪ ሰዓት ያበቃል፤ የሌሊቱም ጊዜ: እንደዚሁ: እስከእኩለ ሌሊት ድረስ: "ከማታው"÷ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ደግሞ: "ከሌሊቱ" እየተባለ: ጨረቃ ከምትታይበት: ወይም ጨለማው ከሚጀምርበት: ከምሽቱ: ፩ ሰዓት ይነሣና: ጎህ በሚቀድድበት: በንጋቱ ፲፪ ሰዓት ይቆማል:: በዚህ መሠረት የተደለደለችው: አንዲቱ ዕለት: ሰባት ስትኾን: ፯ቱ ዕለታት: ፩ ሳምንት ይኾናሉ::

የምዕራባውያኑ ግን: እንዲህ አይደለም:: ምዕራባውያን: የሰሜኑንና የደቡቡን የመሬት ዋልታ ተከትለው: በሰሜንና በደቡብ ክፍላተ ዓለማት: የሚኖሩ በመኾናቸው: ኢትዮጵያውያን: ክረምት÷ መፀው÷ በጋ፥ ጸደይ እንደሚሉት: የእነርሱም ዓመት: Winter (ዊንተር), Spring (ስፕሪንግ) Summer (ሳመር) Autumn (አተምን) በተባሉ: በአራት የተለያዩ ወራት ተከፍፍሎ: በክረምቱ: ሌሊታቸው: እስከ ፳ ሰዓታት የሚቀንስበት: በበጋው ወራት ደግሞ: መዓልታቸው: እስከ ፳ ሰዓታት የሚጨምርበት: እንዲያውም: ወደሰሜኑም ኾነ ወደደቡቡ የመሬት ዋልታ ጫፍ እየተጠጉ በኼዱ መጠን: የሚቀነሱት: ወይም የሚጨመሩት ሰዓታት እየደጉ ይኼዱና: ወደመጨረሻው ጽንፍ ላይ ሲደርስ: ከናካቴው: ፮ ወራት ሙሉ: ሌሊት ብቻ÷ ወይም መዓልት ብቻ ይኾናል::

ይህም ማለት፡ ይህ ኹኔታ፡ በሰሜኑና በደቡቡ ክፍላተ ዓለም፡ በዓመቱ ውስጥ፡ እንዲህ ስለሚፈራረቅ፡ የክረምቱ ብርዳማ ጠባይ፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ የሰሜኑን ክፍል በሚያጠቃበት ጊዜ፡ በደቡቡ ክፍል ደግሞ፡ የበጋው ፀሓያማ ጠባይ ይሰፍናል ማለት ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይኾን፡ በዓመት፡ ኹለት ጊዜያት፡ በየ፮ ወሩ፡ የሰዓት አቆጣጠራቸውን፡ እንደየክፍለ ዓለማቸው አቀማመጥ፡ በ፩ ሰዓት ያሳድጉታል፥ ወይም በ፩ ሰዓት ይቀንሱታል፡፡

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ፯ቱ የሳምንቱ ቀኖች፡ የእግዚአብሔር፡ የሥነ ፍጥረት ሥራው፡ በተራና በቅደም ተከተል የተካኼደባቸውንና በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡትን የዕለታት ስም እንደያዙ፡ የአዳምና ሔዋን ቋንቋ በኾነው፡ በግእዝ፡ "እሑድ"፡ "አንድ" ወይም "መጀመሪያ ቀን" ለማለት፡ "እሑድ"፥ ቀጥሎ፡ "ኹለተኛ ቀን" ለማለት፡ "ሰኑይ"፡ "ሰኞ"፥ ቀጥሎ፡ "ሦስተኛውን ቀን"፡ "የሰኞ ማግሥት" ለማለት፡ "ማግሰኞ"፥ ቀጥሎ፡ "አራተኛ ቀን" ለማለት፡ "ረቡዕ"፥ "አምስተኛ ቀን" ለማለት፡ "ሓሙስ"፥ "የሥራ ማካተቻ" ወይም "የሰንበት መግቢያ ፀሓይ የምትጠልቅበት ቀን" ለማለት፡ "ስድስተኛውን ቀን"፡ "ዓርብ"፥ "ከመጨረሻዋና ከዘለዓለማዊቷ ሰንበት በፊት፡ ቀድማ የነበረችው" ለማለት፡ "ሰባተዪቱን የሰንበት ቀን"፡ "ቅዳሜ" ብለው ይጠርዋቸዋል፡፡

ምዕራባውያን ግን፡ ለእነዚሁ የሳምንት ቀኖች፡ የሰጧቸውን የአረማውያን ጣዖታት አማልክቶቻቸውን ስም እንመልከት! Sunday: Sun's day (ሳንዴይ)፡ ማለት፡ የፀሓይ ቀን፥ Monday: Moon's day (ማንዴይ)፡ የጨረቃ ቀን፥ Tuesday: Tui's day (ቲዩስዴይ)፡ ማለት፡ የጦርነቱ አምላክ፡ የቲዩ ቀን፥ Wednesday: Woden's day (ዌድንስዴይ)፡ ማለት፡ የታላቁ አምላክ፡ የዎደን ቀን፥ Thursday: Thor's day (ተርስዴይ)፡ ማለት፡ የነጐድጓዱ አምላክ፡ የቶር ቀን፥ Friday: Frigg's day (ፍራይዴይ)፡ ማለት፡ የታላቁ አምላክ፡ የዎደን ሚስት፡ የፍሪግስ ቀን፥ Saturday: Saturn's day (ሳተርዴይ)፡ ማለት፡ የሰማዩ ኮከብ፡ የሳተርን ቀን፡፡

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ፴ ዕለታት፡ ፩ ወር ሲኾኑ፥ ፲፪ ወራት እና ፭ ዕለታት ተሩብ ደግሞ፡ ፩ ዓመት ይኾናሉ፡፡ ፭ቱ ዕለታት ተሩብ፡ "ጳጉሜ" ይባላሉ፡፡ "ጳጉሜ"፡ የቃል ለቃል ትርጉሙ፡ "ተውሳክ"፡ "ጭማሪ"፥ "ተረፍ"፡ "ትርፍ" ማለት ነው፡፡ ፲፪ቱ የምዕራባውያን ወሮች ግን፡ ፴፩፡ ዕለታትን፥ በየአራት ዓመቱም፡ ፳፱ ዕለታትን ከያዘውና (February ፌብሩአሪ) ከሚባለው፡ ከአንደኛው ወር በቀር፡ እኩሌቶቹ፡ በ፴፥ የቀሩትም፡ በ፴፩ ዕለታት ተመድበው፡ ይህን በመሰለ የተዘበራረቀ መልክ ይቆጠራሉ፡፡

በኢትዮጵያውያን በኩል፡ ከመስከረም እስከነሓሴ ድረስ ያሉት፡ ፲፪ቱ ወሮቻቸውና ጳጉሜ፡ እያንዳንዳቸው የሚጠሩበት ስም፡ ከእግዚአብሔር ከተሰጣቸው፡ የተፈጥሮ ጸጋቸው ጋር የተያያዘው ገጽታቸውን የሚያሳይ ትርጉም ያለው ሲኾን፡ በኢትዮጵያውያን የወራት አመዳደብ መሠረት፡ ከSeptember (ሴፕቴምበር) መስከረም እስከAugust (ኦገሥት) ነሓሴ ድረስ ያሉት፡ የምዕራባውያኑ ወሮቻቸው ግን፡ እንደሳምንቱ ቀኖቻቸው ኹሉ፡ የተሠየሙት፡ በጣዖቶቻቸውና እንደአማልክት ይሰግዱላቸው በነበሩት ገዢዎቻቸው ስም ኾኖ ይገኛል፡፡

ይኸውም: መስከረምን ከኢትዮጵያውያን፥ Augustን (አገሥትን): ነሐሴን ደግሞ: ከምዕራባውያን: ለምሳሌ ያህል ወስደን ብንመለከታቸው: "መስከረም": በኢትዮጵያኛ: "ከረመ" ወይም: "ክረምትን አሳለፈ" ከሚለው ግሥ ወጥቶ: "ክረምቱ የሚያበቃበት: ማለትም: የዝናሙ ጠል አብቅቶ: የፀሓይ ብርሃን የሚፈካበት፥ የዓባይና የሌሎቹ ወንዞች ሙላት መጉደል የሚጀምርበትና ፍጥረቱ ኹሉ: ከተሸሸገበት በዓቱ እየወጣ: እርስ በርሱ የሚገናኝበት: አዲሱ ዓመት: የሚገባበት ማለት ነው:: "መስከረም ጠባ!" የሚባለውም ለዚህ ነው:: በምዕራባውያን ዘንድ ግን: August (አገሥት): ስለወሩ ኹኔታ: ምንም ትርጉም የሌለው ኾኖ: እንደጣዖት ይመለክ ለነበረው: ለአረማዊው ርእሰ ነገሥት (Emperor): ለአውግሥጦስ ቄሣር: በመታሰቢያነት የተሰጠ ወር መኾኑን ብቻ ያስረዳል::

የኢትዮጵያውያን ዓመት የሚጀምረው: በ"መስከረም"፥ የሚያበቃውም: በ"ጳጒሜ" ሲኾን: የምዕራባውያኑ ግን: በእነርሱ January (ጃንዋሪ): ማለትም: በ"ጥር" ይጀምርና: በDecember (ዲሴምቤር): ማለትም: በ"ታኅሣሥ ይጨርሳል:: ስሙን በመታሰቢያነት: January (ጃንዋሪ) ብለው: ለዓመቱ የመጀመሪያ ወር የሰጡለት: Janus (ጃኑስ): ለሮማውያን: ታላቁ ጣዖታቸው እንደነበረ: ቀደም ብሎ ተመልክቷል::

በኢትዮጵያውያን ዘንድ: ፬ ዓመታት: ፬ ዐውደ ዘመን ይኾናሉ:: ይህም: እያንዳንዱ ዓመት: ፫፻፷፭ ከሩብ ዕለታት: ወይም ከ፮ ሰዓታት: ወይም ከ፲፭ ኬክሮስ ያለው ኾኖ: "ዘመነ ማቴዎስ"፥ "ዘመነ ማርቆስ"፥ "ዘመነ ሉቃስ" እና "ዘመነ ዮሐንስ" ተብሎ ተሠይሟል፤ እነዚህ: የ፬ቱ ዓመታት ጳጒሜዎች ሰዓታት ሲደመሩ: ፩ ዕለት ይሞሉና: በ፬ኛው ዓመት: በዘመነ ሉቃስ: ፮ ዕለታት በመኾን: የባሕረ ሐሳቡ ቅመራ ይካተታል፤[፹፫] የዘመን አቆጣጠሩም ዐውድ: እንዲህ: በየአራት ዓመታቱ ይዘጋል::

ስለዚህ: "የግሬጎሪ" ወይም "ግሬጎሪያን" ተብሎ የሚጠራው: የምዕራባውያን: የጊዜ አቆጣጠር ባህል: እንዲህ: ምስቅልቅሉ የወጣ በመኾኑ: በእርሱ ሰበብና ጠንቅ: ጽኑ የኾነው: ሃይማኖታዊና ተፈጥሮአዊ መሠረት ያለው: የኢትዮጵያ የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት: ሊቃወስ ቀርቶ: ሊነካ እንኳ: ከቶ አይገባም::

## የ"ሺሁ ዓመት" ምሥጢርና ፍጻሜው::

ከዚህ በቀር: የኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት: ትክክልና እውነተኛው መኾኑን ለመጨረሻ ጊዜ ለማረጋገጥ የሚያበቃው ከፍተኛ ነጥብ: እዚህ ላይ ሊወሳ ይገባል፤ ይኸውም: በራእየ ዮሐንስ ላይ የተጠቀሰው: የሺህ ዓመቱ ምሥጢር ነው:: ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ: ስለዚሁ ምሥጢር: በራእዩ: እንዲህ ሲል ጽፏል:- *"የጥልቁን መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት: በእጁ የያዘ መልአክ: ከሰማይ ሲወርድ አየሁ:: የቀደመውንም እባብ፥ ዘንዶውን፥ እርሱም: ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው! ሺህ ዓመትም አሠረው! ወደጥልቅም ጣለው! አሕዛብንም ወደፊት እንዳያስት፤ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ: በእርሱ ላይ ዘግቶ: ማኅተም አደረገበት! ከዚያም በኋላ: ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል::*

*“ከዚህ በኋላ፡ ዙፋኖች ተዘርግተው፡ የሰው ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በላያቸው ተቀምጠ አየሁ! ስለኢየሱስ፥ስለስሙና ስለእግዚአብሔር ቃል ሲሉ ስለተገደሉ ሰዎች ነፍሳትም፡ ቅን ፍርድን ፈረደላቸው! ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን (ያልተገዙትን)፥ ምልክቱንም፡ በግምባራቸው ላይ ያልጻፉትን (በመፈክር ሰሌዳ ያላነገቡትን)፥ በእጆቻቸውም (በአባልነት ደብተርና በደብዳቤ) ያልተቀበሉትን አየሁ! እነሆ፡ ከክርስቶስ ጋር፡ በዚህ ሺህ ዓመት፡ ሕያዋን ኾነውና ነግሠው ይኖራሉ! የቀሩቱ ሙታን ግን፡ ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፡ ተነሥተው በሕይወት አይኖሩም፡፡ ይህች፡ በመንፈስ ትንሣኤ የምትገኘው፡ የፊተኛዪቱ ሕይወት ናት! አስቀድማ በምትመጣው፡ በዚች ሕይወት፡ ዕድል ፈንታ ያለው፡ ብፁዕና ቅዱስ ነው! ኹለተኛው ሞት፡ በእነዚህ ላይ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ሥልጣን የለውምና! የእግዚአብሔርና የክርስቶስ አገልጋዮች ይኾናሉ እንጂ! ከእርሱም ጋር፡ ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ!*

*“ሺሁም ዓመት ሲፈጸም፡ ሰይጣን ከእሥራቱ ይፈታል! በአራቱም፡ በምድር ማዕዘናት ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው፥ ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል! ቁጥራቸውም፡ እንደባሕር አሸዋ የሚያህል ነው፡፡ ወደምድርም ስፋት ወጡ! የቅዱሳን መሰባሰቢያ የኾነችውንም ቅድስት አገር (ኢትዮጵያን) ከበቡ! ከዚህ በኋላ፡ ከሰማይ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ እሳት ወርዳ በላቻቸው! ያሳታቸውም ዲያብሎስ፡ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደሚገኙበት፡ ወደእሳቱና ወደዲኑ ዐዘቅት ተጣለ! በዚያም፡ ለዘለዓለም እስከዘለዓለም፡ በመዓልትና በሌሊት፡ ሲሠቃዩ ይኖራሉ፡፡”*[፹፬]

ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተረጋገጠውን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት በመከተል፡ እስከዛሬ ጠብቀውት የኖሩትን፡ መሠረታዊዉን የጊዜ አቆጣጠር ስልት፡ ምዕራባውያን፥ አርቶዶክሳውያን የተባሉትን አብያተ ክርስቲያናት ጨምሮ፡ በአረማዊው፡ ዩልየስ ቄሣርና ግሬጎሪ ፲፫ኛ በተባለው፡ በካቶሊካዊው ጳጳስ ስሞች እየሠየሙ፥ በየጊዜው እየለዋወጡና በመጨረሻ፡ ፯ ዓመታት ከ፲ ቀናት ያህል አክለውበት መቆየታቸው፡ ቀደም ብሎ ተገልጿል፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ በራእየ ዮሐንስ የተነገረው፡ የሺሁ ዓመት ምሥጢር፡ እንደእነርሱ አቈጣጠር፡ “፩ሺህኛው ዓመት ተፈጽሞ፡ ፪ ሺህኛው ዘመን በገባባትና ባለፈው የጥር ወራቸው መግቢያ እኩለ ሌሊት ላይ በነበረችው፡ በዚያች፡ የመጀመሪያ ሰዓት ይከሠታል!” ብለው፡ በታላቅ ሥጋትና ፍርሃት፥ የመንፈስ ንቃትም፡ የጠበቁት፡ “የዓለሙ ፍጻሜ” ሳይደርስ አልፏል! ታዲያ! የዚህ ምክንያት፡ ምን ይኾን? እንያ፡ በሰውኛ ፍልስፍና ታስበውና ተቀምረው የታከሉት፡ ፯ ዓመታት ከ፲ ቀናት፡ በኢትዮጵያኑ አቈጣጠር ላይ መጨመራቸው፡ ስሕተት መኾኑን ለማጋለጥ ይኾን?

እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ የሚጠበቀው፡ በእውነተኛዋ ሃይማኖት ላይ የጸናው፥ ዛሬ የሚሠራበትና ለሽሁ ዓመት ማብቂያ፡ ሰባት ዓመታት የቀረው፡ ይህ የኢትዮጵያውያን የጊዜ አቈጣጠር ሥርዓት ነው፡፡ ይኸው፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ የተመሠረተው፥ የቆመውና የተደመደመው፡ በእግዚአብሔር ቃልና አምልኮት ላይ ስለኾነ፡ ዕድሜውን ያገኘ ሰው፡ ይህ መጽሐፍ ታትሞ ከወጣበት፡ ከ፩ሺ፱፻፺፫ ዓ. ም. በኋላ፡ ለ፯ ዓመታት ቆይቶ፡ በምትገባዋ፡ በዚያች በ“ሽዋ ዓመት” ፍጻሜ የሚደርሰውን፡ የራእየ ዮሐንስን የምሥጢር ክሥተት፡ ሊያይ ይበቃል፡፡

## ስለጌታ የልደት ቀን፡ የኢትዮጵያውያን ውሳኔ፡ ምን ሊኾን ይገባል?

ታዲያ፡ በአሁኑ ዘመን ለምንገኝ ኢትዮጵያውያን፡ ያለን ምርጫ የትኛው ነው? አዎን! የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀን፥ ለእኛም በዓላችን ኾና ልናከብራት የሚገባን ዕለት፡ ከኹለቱ ዕለታት፡ የትኛዋ ናት? እውነተኛዪቱና ትክክለኛዪቱ ዕለት የትኛዋ እንደኾነች፡ በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ፡ መርጠንና ወስነን፡ አንደኛዪቱን መያዝ አለብን። ይኸውም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "በጽኑ ቀጠሮው፡ አንዲት ሰዓት እንኳ ሳያሳልፍ" ተወለደባት ወዳሰኘውና "ዓመተ ምሕረት" ብለን ዓመቱን ወደምንጀምርበት፡ ወደጥንታዊው የዘመን አቆጣጠራችን፡ ተመልሰን፡ በእግዚአብሔር አምልኮ፥ ቃልና መንፈስ ተመሥርታ፥ ጸንታና ሕያው ኾና የኖረችው፡ ያች፡ የልደቱ ዕለት፡ "መስከረም ፩ ቀን ናት" እንል እንደኾነ፥ ወይ ደግሞ፡ ይኼ፡ መለኮታዊው ሥርዓታችን ተሠርዞ፡ በጣዖት አምልኮና በአረማውያን ባህል ላይ በተመሠረተው፡ በባዕዳኑ የሰዎች ሥርዓት ተተክቶ፡ ከወገኖቻችን መካከል፡ ብዙዎች እንዳደረጉት፡ እኛም፡ የቀረነው፡ ኢትዮጵያዊነታችንን ከደንና የቀን አቆጣጠራችንን ዘይቤ ለውጠን፡ ወደባዕዳኑ ጠቅልለን እንገባ እንደኾነ፡ መወሰን የሚያስፈልግ መኾኑ ነው።

ይህ ጉዳይ፡ ሃይማኖትንና አምልኮን የሚመለከት ስለኾነ፡ በተለይ፡ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እንደሌላው ነገር፡ እንዲያው፡ በዝምታ፡ ወይም በቸልታ፡ ወይም በቀላል እይታ፡ ሊታለፍ የሚችል አይደለምና፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ በግድ አንድ ዓይነት ውሳኔን ልንሰጠው ይገባናል። የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የማንነቱ መታወቂያዎች የኾኑትን፡ ወደር የማይገኝላቸውን ፊደሎቹን፡ ከመቀናነስ አልፎ፡ አኀዞቹን (ቁጥሮቹን)፡ በንቀት ትቶ በመሻር፡ የባዕዳን በኾኑት፡ በምዕራባውያኑ ፊደሎችና አኀዞች ለመተካት፡ እያመለከተ በሚገኘው ዝንባሌው ዓይነት፡ የቀን አቆጣጠሩንም፡ ወደነዚሁ ባዕዳን ባህል ለመቀየር፡ አዝማሚያውን እየቀየሰ በመንዝ ላይ መኾኑ፡ ይኸው ይታያል። ይህን በሚመለከት የተሰጠውን ሐተታ፡ ወደፊት፡ በቦታው ይመለከቷል።

## ስለገና ዛፍ፡ የአምልኮ ታሪክ።

ባሁኑ ጊዜ፡ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን፥ ካለማወቅ የተነሣ ይመስላል፥ ኢትዮጵያዊዉን የልደት በዓል፡ በምዕራባውያን ልማድ፡ በጥድ ዛፍ ሲያከብሩት ይታያል። ዳሩ ግን፡ ይህ ድርጊት፡ የሃይማኖት አምልኮን የሚነካ በመኾኑ፡ በብርቱ ሊታሰብበትና ሊነቃበት የሚያስፈልግ፡ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በተለይ፡ ኢትዮጵያውያን ልጆች፡ ስለዛፉ በሚጠይቁበት ጊዜ፡ ጉዳዩ፡ ሃይማኖትን የሚመለከት በመኾኑ፡ ስለሚሰጠው ምላሽ፡ ወላጆችም ኾኑ መምህራን፥ አረጋውያን ወንዶችም ኾኑ ሴቶች፡ በብርቱ ሊጠነቀቁበት ይገባል። ኢትዮጵያውያን ልጆች፡ ስለገናው ዛፍ፡ ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ፡ ምዕራባውያኑ፡ ለልጆቻቸው፡ "የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበላችን በፊት፡ በዛፍ እናመልክ ስለነበር ነው!" ብለው የሚሰጧቸውን መልስ ተከትለን፡ ታሪኩን ልናብራራላቸው ይገባል።

ታዲያ፡ እኛ፡ ዛሬን፡ ለገና በዓላችን ማክበሪያ ካደረግነው፡ ልጆቻችን ሲጠይቁን፡ በምን የተነሣ ነው ብለን አከታትለን ልናስረዳቸው ይኾን? እጅግ ያስቸግራል፤ ይከብዳልም:: እንግዲህ፡ ምዕራባውያን፡ የገና በዓላቸውን፡ በተጌጠ የጥድ ዛፍ የሚያከብሩት በምን ምክንያት መኾኑን፡ ኢትዮጵያውያን ልጆቻችን፡ "በትክክል ሊያውቁት ያስፈልጋቸዋል"፥ እኛም፡ "ልናሳውቃቸው ይገባናል" የሚያሰኘው ምክንያት ይህ ነው::

እኛ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ጥንት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኪዳነ ልቦና፥ በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ እስከዛሬ የኖርነው፥ ዛሬም እየኖርን ያለነው፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፡ ስለጽላትና ስለታቦት፡ የተሰጠው ሐተታ፡ እንደተጠበቀ ኾኖ፡ ያው፡ በእውነትና በመንፈስ፡ በምንፈጽመው፡ በአምልኮተ እግዚአብሔር ብቻ መኾኑን በማስረዳት፥ የዛሬንም ታሪክ፡ ከላይ በተገለጸው መልክ በማብራራት፡ ኢትዮጵያውያን ልጆቻችን፡ የልደት በዓላችንን፡ እንደፈረንጆቹ፡ በገና ዛፍ ከማክበር እንዲታቀቡ ማስተማሩ፡ የወላጆችና የመምህራን፥ ከዚያም በላይ፡ የማናቸውም ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ግዳጅ ነው:: ስለዚህ፡ ይህ ጉዳይ፡ አምልኮን የሚመለከት በመኾኑ፡ ኢትዮጵያውያን ወላጆች፥ ብቸኞችም ጭምር፡ ኹላቸው፡ ልደትን፡ እንደባዕዳኑ፡ በጥድ ዛፍ በማክበሩና ይህን የመሰለውን እጉል ባህል፡ ለተተኪው ትውልድ በማስለመዱ ረገድ፡ በብርቱ መጠንቀቅ እንዳለባቸው፡ ሊያውቁት ይገባል::

## ኢትዮጵያ፡ ስለቅዱስ ቁርባን አቀራረብና አቀባበል፡ ካህናቷንና ምእመናኗን ስትፋረድ!

በሥርዓተ ቅዳሴ አገልግሎት መግቢያ ላይ፡ *"ሃሌ ሉያ! ወደቤተ ክርስቲያን ከገቡ ምእመናን መካከል፡ በቅዳሴ ጊዜ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማያዳምጥ፥ የቅዳሴውም ጸሎት እስኪፈጸም የማይታገሥ፥ ከቁርባኑም የማይቀበል ቢኖር፡ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ! የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና! የሥጋና የነፍስ ንጉሥ በሚኾን፡ በሰማያዊው ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃሏልና! ሐዋርያት እንዲህ ብለው በሲኖዶሳቸው አስተምረውናል::"* የሚል ትርጉም ያለው፡ *"ሃሌ ሉያ! እመቦ ብእሲ እምእመናን፡ ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን!"* በሚል ቃል ተነሥቶ፡ *"ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት፡ በአብጥሊሶሙ"* ብሎ የሚያበቃው፡ የአዋጅ ቃል፡ በቃጭልና በደወል፥ በግእዝና በዜማ ይሰማል:: ይህን የመሰለው፡ ታላቅና ኃያል የኾነው አምላካዊ የአዋጅ መልእክት፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ሊሰማውና ሊረዳው በሚችለው ልሳን፡ ማለትም፡ በኢትዮጵያኛ (በአማርኛ) ሳይኾን፡ ኾን ተብሎ፡ ሕዝቡ፡ ተምሮት እንዲያውቅ ባልተደረገው፡ በግእዝ ቋንቋ፥ ደግሞም፡ በንባብ ሳይኾን፡ ከቃጭሉ ጩኸት ጋር በሚደበላለቀው፡ በዜማ ድምፅ ተውጦ፡ የሚተላለፍ በመኾኑ፡ ራሱን፡ አዋጁን እንዳልተነገረ፥ ጨርሶም እንደሌለ አስቆጥሮታል::

እነሆም፡ ሰዎች ከፈጠሩት፡ ከዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ያጣ አሠራር የተነሣ፡ የኢትዮጵያ ምእመናን፡ ወንዶቹም፡ ሴቶቹም፥ ወጣቶቹም፡ አዛውንቱም፡ "እናት ወይም እህት" ከምትባለው፡ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን እንኳ ሳይቀር፡ ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ፡ ብቻቸውን ተለይተው፡ አብዛኞዎቹ፡ ከሥጋ ወደሙ ርቀው፡ በስም ብቻ "ክርስቲያን" እየተባሉ፡ ይኸው እስከዛሬ ድረስ፡ በዲያብሎስ ገዢነት፥ በኃጢአት ቀንበርና በሞት ፍዳ እንደተያዙ፥ እንደታሠሩና እንደተጨነቁ እንዲኖሩ ተፈርዶባቸው ይገኛሉ:: ይኹን እንጂ፡ ከእነዚሁ መካከል፡ የሃይማኖታቸውን ጽናትና የምግባራቸውን ቅንነት፥ የልቦናቸውን ንጽሕናና የፍቅራቸውን ፍጹምነት የሚያውቅ፡ የቃል ኪዳን አምላካቸው፡ እግዚአብሔር፡ ራሳቸውን፡ በንስሓ አንጽተውና አጽድቀው፡ ለሥጋ ወደሙ እንዳበቁ የሚቀጥርላቸው ብዙዎች ስላሉ፡ እነዚህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በእርሱ ዘንድ፡ ቅዱሱን ቁርባን የተቀበሉ ኾነው እንደሚቀደሱ ይታመናል::

## የካህኑ፡ የእጅ መታጠብ ሥርዓት ምክንያት::

መለኮታዊ ቁጣን፡ በሕዝቡና በአገሪቱ ላይ፡ በየጊዜው፡ እያከታተለ ከሚያመጣው፡ የኃጢአት ክምችት መካከል፡ አንዱ የኾነው፡ ይህ ግፍ፡ በዚህ ብቻ አያበቃም፤ ዲያብሎስን፥ እኒህንም ኹሉ የክፋት ኃይላትና አርእስተ ኃጣውእ፡ በከፍተኛ ገድል፥ በጀግንነትና በድል አድራጊነት አልፈውና ራሳቸውን በንስሓ አንጽተው፡ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል የሚቀርቡ ቢኖሩ፡ እነርሱን በመልካም ተቀብሎና አስተናግዶ፡ ወደቁርባኑም ገበታ ጋብዞ፡ መለኮታዊዉን ማዕድ እንዲሳተፉ በማድረግ ፈንታ፡ ተደናግጠው እንዲባረሩ በሚያደርግ አቀራረብ፡ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚመራው፡ ሠራዒው ቄስ፡ ከመቅደሱ ወደውጭ ወጥቶ፡ የሚያሰማው የአዋጅ ቃል ነው::

እርሱም፡ የአዋጁን ቃል የሚያስተላልፈው፡ በቅዳሴው ጸሎት ላይ ሲያደርግ በቆየውና ሕዝቡ በማይገባው በግእዝ ሳይኾን፡ ኾን ተብሎ፡ በተለይ፡ በዚህ ጊዜ ብቻ፡ ሕዝቡ በሚሰማው ቋንቋ፡ በትርጉም፥ ድምፁን፡ አለዝቦ ሳይኾን፡ እጅግ ከፍ አድርጎ በመኾኑ፡ አቀራረቡና መልእክቱ፡ ለልማት ሳይኾን፡ ለጥፋት መኾኑ ይታወቃል:: በዚህ መልክ፡ ካህኑ የሚያሰማው ቃል፡ "ንጹሕ የኾነ፡ ከሥጋው ከደሙ ይቀበል! ንጹሕ ያልኾነ ግን አይቀበል! ለሰይጣንና ለሠራዊቱ በተዘጋጀው፡ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል! በልቡናው ቂምን የያዘ፥ ልዩ አሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር፡ አይቅረብ!" በሚለው መግቢያ ይጀምራል:: ከዚያም፡ እጆቹን ከታጠበ በኋላ፡ "እጄን፡ ከአፍአዊው እድፍ፡ ንጹሕ እንዳደረግሁ፡ እንደዚሁም፡ ደፍራችሁ፡ ወደክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ፡ ከኹላችሁ ደም፡ ንጹሕ ነኝ፤ ከእርሱ ለመቀበላችሁ፡ መተላለፍ የለብኝም፤ ኃጢአታችሁ፡ በራሳችሁ ይመለሳል እንጂ፤ በንጽሕና ኾናችሁ ባትቀርቡ፡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ!" የሚል ነው:: ካህኑ፡ በዚህ ቃል የሚፈጽመው፡ ይህ ሥርዓት *"ደሙ፡ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይኹን!"* ላሉት፡ ለአይሁድ፡ ጲላጦስ፡ ቀደም ብሎ፡ *"እኔ፡ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም፡ ንጹሕ ነኝ! እናንተ ተጠንቀቁ!"* እያለ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ የስቅላት ፍርድ፡ ራሱን በማንጻት፡ እጁን የመታጠቡን ነገር፡ ምሳሌው ለማድረግ ነው::

ታዲያ፥ ካህኑ፡ በእርግጥ፡ የሚታጠበው፡ ራሱን፡ ከኃጢአተኛው ደም፡ ንጹሕ በሚያደርገው፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ውኃ ነውን? ወይስ፡ ለራሱ ፍዳን በሚያመጣበት፡ በኃጢአተኛው ደም ነው? ይህ ኹሉ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ አስፈላጊ ይኾን የነበረው፡ ለመቁረብ ፍላጎት ያለው ምእመን ቢኖር ነበር እኮ? መጀመሪያ ነገር፡ በድፍረትም ይኹን፡ በፍላጎት፡ ለመቁረብ የሚቀርብ ሰው የታለና! "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ!" እንደሚባለው፡ እንኳንስ፡ እስከዚህ ድረስ የጸና ኃይለ ቃል ማወጅ የሚያስፈልገው ሊኾን ይቅርና፡ ተገቢው የአዲስ ኪዳን ትምህርት፡ የቱንም ያህል፡ ለአያሌ ዓመታት ተብራርቶ ተሰጥቶም እኮ፡ ከሕፃናትና ከአረጋውያን በስተቀር፡ ለኃጢአት ማስተስረያ፥ ለመድኃኒትነትና ለሕይወት ያስፈልጋቸዋል ከሚባሉት፡ በኃጢአት የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉት ምእመናን መካከል፡ ተገቢ ብዛት ያላቸውን ወንዶችና ሴቶች፡ ወደሥጋና ደሙ ለማቅረብ ሳይቻል ቀርቷል።

ለዚህም፡ በየአፍታው፡ የሞት ጥሪ እንጠባበቅበት በነበረውና "ለንስሓ ሞት አብቃኝ!" የሚለው፡ የእውነተኛ ምእመን ምኞትና ጸሎት፡ ደርሶና መልስ አግኝቶ፡ ለፍጹም ፍሬአማነት በበቃበት፡ በደርግ እሥር ቤት ውስጥ በነበርሁበት ጊዜ፡ በዚህ ረገድ ደርሶ የነበረውን ኹኔታ፡ እዚህ ላይ፡ በጥሩ ምሳሌነቱ አቀርበዋለሁ። በዚያ እሥር ቤት ሣለን፡ ሌላው ቢቀር፡ በታላላቁ በዓላት ጊዜ፡ ሥርዓተ ቅዳሴ እንድናካኺድ የነበረኝ ሐሳብ፡ ተቀባይነት ሳያገኝ ከቆየ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ እጩጌ ቴዎፍሎስና ሌሎቹ፡ የእሥር ጓደኞቻችን፡ በየተራቸው እየተጠሩ፡ የሞት ጽዋቸውን ከተቀበሉባት ሳምንት ቀደም ብሎ በነበረው የበዓለ ትንሣኤ ሌሊት፡ እኛ እሥረኞቹ፡ ካህናቱና ምእመናኑ፡ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል የምንበቃበት የቅዳሴው ሥርዓት እንዲፈጸም፡ ፍላጎታቸው መኾኑን፡ እሥረኛው እጩጌ፡ በሕማማቱ ማለቂያ ላይ፡ ባልጠበቅሁት መልክ፡ ድንገት አስታወቁኝ። እኔም፡ "ምን ታይቷቸው ይኾን?" ብዬ ከማሰብ ጋር፡ የቆየ ምኞቴ ሊፈጸም በመኾኑ፡ እግዚአብሔርን አመስግኜ፡ እሥረኞቹን ሳማክራቸውና የእሥር ቤቱን ኃላፊዎች ስጠይቃቸው፡ ኹሉም፡ በየበኩላቸው ተስማሙ፤ የሚያስፈልገውም ዝግጅት ስለተሳካ፡ በዚያች፡ ለአንዳንዶቹ እሥረኞች፡ የመጨረሻዋ ፋሲካ በነበረችው ሌሊት፡ በእሥረኛው እጩጌ መሪነትና በእኔ ሠራዒነት፡ ቅዳሴው ተከናውኖ፡ እኛ ኹለታችን፡ ከቅዱሱ ቁርባን ተቀበልን፤ ከዚያ በኋላ የኾነው ግን፡ እጅግ የሚያሳዝን ኾነ!

በእኛ፡ በካህናቱ በኩል፡ "መቼም፡ እሥረኞቹ ምእመናን፡ በሙሉ መቀበላቸው አይቀርምና፡ መሥዋዕቱ፡ ለኹሉም ይዳረስ ዘንድ፡ እንደምንም እናብቃቃዋለን" ብለን በመሥጋት፡ እያንዳንዳቸው እንዲቀበሉ ስንጠባበቅ፡ በኹለቱ ክፍሎች ውስጥ ይገኙ ከነበሩት፡ ወደመቶ ከሚጠጉት እሥረኞች መካከል፡ አንድ ሰው እንኳ፡ ሊቀበል የቀረበ ሳይኖር ቀረ! ኃዘናችንን ያባሰው፡ የዲቁናው ሙያው ኖሮአቸው፡ በቅዳሴው ተልእኮ፡ በበጎ ፈቃድ፡ በረዳትነት ያገለገሉት፡ ቀኛዝማች አመኑ ገብረ ሐና የተባሉት ሰው ሳይቀሩ፡ ሳይቀበሉ መቅረታቸው ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ ተከታትሎ ከደረሰው የሞት ጥሪ የተረፍሁትን እኔን፡ በዚህ ረገድ፡ በኃዘን ላይ ኃዘን የጨመረብኝ ምክንያት ቢኖር፡ ለንስሓ ሞት በቅተው፡ ከፈጣሪያቸው ፊት፡ በጽድቅ ሊቀርቡ ያስችላቸው የነበረው፡ ያን የመሰለ ዕድል ቀርቦላቸው፡ ሳይጠቀሙበት፡ የማይቀረውን የሞት ጽዋቸውን ለመቀበል፡ ከእጩጌው ጋር ተጠርተው የኼዱት፡ የእነዚያ እሥረኞች ምእመናን ፍጻሜ ነው።

እንግዲህ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ከሰባት ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ በትምህርት መልክ፡ ያለማቋረጥ ሲሰጥበት በኖረውና ለእውነተኛ የንስሓ ሞት በሚያበቃው እሥር ቤት ውስጥ ተወስነው በሚገኙበት ኑሮ፡ እኒያን፡ "የተማሩ" የተባሉና የቀድሞ ባለሥልጣኖች የነበሩ፡ አዛውንት ኢትዮጵያውያን ምእመናን፡ ለሥጋ ወደሙ መብቃት ካልተቻለ፡ በሌላማ፡ እንዴት ሊሳካ ይቻላል? ታዲያ፡ እንዲህ ባለው ኅብረተሰብ መካከል፡ ታላቅ ተጋድሎ አካኺዶና ራሱን፡ በቆራጥነት ለንስሓ አብቅቶ፡ ሥጋውን ደሙን ሊቀበል የቀረበውን ጀግና፡ ያን የመሰለ፡ አስደንጋጭና አስበርጋጊ ቃል በማሰማት፡ ከግብዣው ገበታ ላይ ማስነሣትና ከአዳራሹ ገፍትሮ ማስወጣት፥ ማሳደድም፡ የዲያብሎስ እንጂ፡ እንዴት፡ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ሊባል ይቻላል? አይቻልም።

ይህን አስፈሪ ቃልና ድርጊቱን፡ በቅዳሴው መግቢያ ላይ ከታወጀው፡ ከዚያ፡ ካልተደመጠው፡ ከመለኮታዊው የግብዣ ጥሪ ጋር ሲያነጻጽሩት፡ በሕዝባዊው አነጋገር፡ "እንዳያማህ ጥራው! እንዳይበላ ግፋው!" ለሚለው ምሳሌ የተስማማ ኾኖ ይገኛል። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ፡ ጠሪውና ጋባዡ ባለቤት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በኃጢአት ምክንያት፡ የተራቡትንና የተጠሙትን፥ የታመሙትንም ተጋባዦቹን፡ በመስቀል ላይ የሠዋውን፡ የራሱን ሥጋ በልተውለት፥ ደሙንም ጠጥተውለት፡ ከረሃባቸው እንዲጠግቡለትና ከጥማታቸው እንዲረኩለት፥ ከኃጢአት ደዌያቸውም እንዲፈወሱለት ያዘጋጀውን ድግሥ አቅርቦ፡ እንዲያስተናግድለት፡ አደራ ያለውና እርሱም፡ አደራውን በመጠበቅ፡ "እባካችሁ፡ ግቡና ተጋበዙልኝ!" እያለ፡ የመጡትን እንግዶች በማስተናበር፡ ያን፡ በገበታው ላይ ተዘርግቶ የተሰናዳውን ሰማያዊ ምግብና መጠጥ፡ እንዲበሉለትና እንዲጠጡለት ሊገፋፋቸው የሚገባው፡ ያ፡ ዋና አገልጋይ ቄስ፡ ለእነዚያ ተጠርተው ለመጡትና ሊጋበዙ ለተዘጋጁት ምእመናንና ምእመናት፡ ያን የመሰለ፡ አስፈሪ፡ የቅጣት አዋጅ ብቻ፡ በድንገት ማሰማቱና ተስፋ አስቆራጭ የኾነውን፡ የእጅ መታጠብ ድርጊቱን አከታትሎ መፈጸሙ ነው። ሲኾንማ፡ ከግብዣው ለመሳተፍ የሚያመነቱ ቢኖሩ እንኳ፥ ወይም፡ በመጀመሪያ፡ ለአንድ ቀን ተጋብዘው፡ "በቃን!" ያሉ ቢኖሩ እንኳ፡ "በሥላሴ! በመድኃኔ ዓለም! በማርያም! በሚካኤል! በተክለ ሃይማኖት! ባቦ!" እያለ በመማፀን፡ ሊጫናቸው፥ ያም ቢቀር፡ ስለዚያ የአዋጅ ቃል፡ በትምህርትና በምክር መልክ፡ በቅድሚያ፡ አንዳንድ ማብራሪያዎችን ሊሰጣቸው በተገባው ነበር።

ካህኑ፡ ይህን ማድረግ የሚሳነው ቢኾን እንኳ፡ ከራሱ ጀምሮ፡ ማንም ሥጋ ለባሽ፡ በ"ንስሓ" ካልኾነ በቀር፡ ንጹሕ ኾኖ፡ ለሥጋ ወደሙ መብቃት እንደማይችል ተገንዝቦ፡ በአዋጁ ቃል መጀመሪያ ላይ፡ "ንስሓ" የምትለውን ቁልፍ ቃል በመጨመር፡ "*በንስሓ፡* ንጹሕ የኾነ፡ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ይቅረብ! *በንስሓ፡* ንጹሕ ያልኾነ ግን አይቅረብ!" ሊል ይገባው ነበር። ግብፃውያኑ ጳጳሳትና፡ የእነርሱ ሎሌዎች የነበሩት፡ ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት፡ በቅዳሴው መጽሐፍ ላይ የጻፉትና የተረጐሙት ቃል፡ "ንስሓ" የምትለውን ቃል ስላልጨመረና ቃሉ ስላልታቱ፡ ቀሳውስቱ፡ የተጻፈውን ነገር፡ እንደመቅረፀ ድምፅ፡ በቃል ብቻ ይዞ ማነብነብ እንጂ፡ ከራሱ ከሊቀ ካህናቱ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀጥታ የተሰጣቸውን መመሪያ፡ አመዛዝነውና ተገቢውን ምርጫ አድርገው የመወሰኑ ዓቅም ያላቸው፡ ብዙዎች ስላልኾኑ፡ ይህን ማድረግ፡ ሃይማኖትን እንደማፍረስ እየቆጠሩት፡ "ንስሓ" የምትለዋን ቃል እንዲጨምሩ ቢነገራቸውም፡ ሊቀበሉት የማይቻላቸው ኾነዋል።

ብዙውን ጊዜ እንደሚታየውም፡ ቀዳሹ፡ ዋና ቄስ፡ ስለቅዱስ ቁርባንና እርሱን ለመቀበል ስለሚያበቃው ስለንስሓ፡ አስቀድሞ፡ ለምእመናኑ አብራርቶ በማያስረዳበት፡ ወይም ማስረዳት በማይችልበት ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ፡ ሌላ አስተማሪ ወይም ሰባኪ፡ የእርሱን ቦታ ወስዶ፡ ይህንኑ ምሥጢር፡ በሚገባ በመግለጽ፡ የሰጠውን ሰፊ ትምህርት ባለመረዳት፡ ወይም ገሸሽ በማድረግ፡ ወይም እንደቁም ነገር ባለመቁጠር፥ ባጠቃላይ፡ ወደቅዱስ ቁርባን እንዲያደርስ፡ በዚያ ትምህርት ተመንጥሮ የተከፈተውን ጐዳና በመዝጋትና የተገነባውን ማረፊያ ሕንፃ በመገርሰስ፡ ሠራዒው ቄስ፡ በቃሉ ያጠናውን፡ ያን አስደንጋጭ፡ ማባረሪያ አዋጅ ብቻ፡ ለሕዝቡ ያሰማል።

በዚያን ጊዜ፡ በዚያች ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይኾን፡ በየቦታውና በየጊዜያቱ በተሰጠው ትምህርት፥ በዕለቱም ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ በቀረበው ጸሎት አማካይነት፡ ወደዚያ መለኮታዊ ግብዣ፥ ወደዚያ መለኮታዊ ሕክምና ቤት፥ ወደዚያ መለኮታዊ ሓኪምና ወደዚያ መለኮታዊ መድኃኒት ተጠርቶ የመጣውን፡ ረሃብተኛውንና በሽተኛውን፡ እንዲያሽጋግር፡ በእውነት የታነጸው መንፈሳዊው ድልድይ፡ ወዲያው እንዲፈራርስ ይደረግና፡ በሽተኛውም፡ በበሽታው (በኃጢአቱ)፥ ረሃብተኛውም፡ በረሃቡ (በኃጢአቱ) እንዳለ፥ ኹሉም፡ ተስፋ እየቆረጡ፡ በኀዘን ወደየቤታቸው ይመለሳሉ፤ ቆይተውም፡ በየኃጢአታቸው፡ ይሞታሉ ማለት ነው። ሥጋውን ደሙን ሊቀበል የቀረበው፡ በዚህ መልክ ሲመለስ፥ ሳለመቁረብ፡ ምክንያት እየፈጠረ፡ ቀደም ብሎ፡ ርቆ የነበረው ደግሞ፡ ይህን የመሰለውን በቂ ሰበብ ሲያገኝ፡ የበለጠ እየራቀ እንዲሄድ ይኾናል። *"እኔ ኃጢአተኛውን፡ 'በእርግጥ ትሞታለህ' ባልሁት ጊዜ፡ አንተም፡ ባታስጠነቅቀው፥ ነፍሱም እንድትድን፡ ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ፡ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፡ ያ ኃጢአተኛ፡ በኃጢአት ይሞታል! ደሙን ግን፡ ከእጅህ እፈልጋለሁ!"* የሚለው፡ የመለኮት ፍርድ፡ በካህኑ ላይ ተፈጻሚ የሚኾነው፡ በዚህ ጊዜ ነው።[፹፭]

ከዚህ ጋር፡ ምእመናኑ፡ ሥጋውን ደሙን ይቀበሉ ዘንድ፡ ልቦናቸውን በመንፈስ ቅዱስ የሚያነሣሡዋቸውን፡ "አሜን! አሜን! አሜን!"፡ ማለትም፡ "አዎን እናምናለን!" እያሉ፡ ለሥጋውና ለደሙ፡ ሦስት ሦስት ጊዜያት መላልሰው፡ መልስ በሚሰጡባቸው፡ በፍሬ ቅዳሴው፡ ዓቢይ ክፍልና ፍጻሜ ላይ ሲደርሱ፡ የተሰጥኦውን ጸሎት፡ በሚያውቁት ቋንቋ ሰምተው፥ ምሥጢሩንም አውቀውና ተረድተው፡ ቅዱሱን ቁርባን ለመቀበል እንዳይበቁ እንኳ፥ ያንኑም ቢኾን የሚሰሙት፡ በግእዙና በዜማ፥ በከፍተኛም ጥድፊያ በመኾኑ፡ ቁም ነገሩ ሳይደመጥ፡ እንዲያልፍ ይደረጋል።

## የቁርባኑን ክልከላ የሚያጠናክረው ቃል፡ ከነድርጊቱ።

ይልቁንም፡ ለምእመናኑ፡ መልካም አርአያ ሊኾኑ የሚገባቸው፡ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት፡ በተለይም፡ ደባትር የተባሉት መዘምራን፥ ሊቃውንትና መምህራን፡ በቅዳሴው መግቢያ ጊዜ፡ ከቤተ ክርስቲያን እየወጡ ሲኼዱ ከመታየታቸው ጋር፥ አንድ የቅዳሴ ማርያም የአንድምታ ትርጓሜ የፈጠረው ጠንቅ ተዳምሮ፡ በዚህ ረገድ ያደረሰው ጉዳት፡ በቀላል የማይገመት ኾኖ ተገኝቷል።

ይኸውም፡ "እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን፤ ወስቴ ሕይወት ዘበአማን"፤ "እውነተኛውን ምግብ፥ እውነተኛውንም መጠጥ አስገኝተሽልናልና!" ለሚለው ኃይለ ቃል፡ "የዚህ ዓለም ምግብ፡ ጧት በልቶ ለማታ፥ ማታ በልቶ ለጧት ያሻል፤ ሥጋ ወደሙን ግን፡ በሚገባ ከተቀበሉት፥ በኃጢአት ካላሳደፉት በቀር፡ ሕማሙን ሞቱን ለማዘከር ነው እንጂ፡ አንድ ጊዜ ከተቀበሉት፡ በሌላ ጊዜ አያሻምና!" ተብሎ የተሰጠው፡ የትርጓሜ ሐተታ ነው። በተለይ፡ በቅኔ ማኅሌትና በሰዓታት ጸሎት ተወስነው፡ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉት ካህናት፡ ይህን ትርጓሜ ምክንያት እያደረጉ፡ እየራሳቸውን፡ ከሥጋ ወደሙ ማራቃቸው ይታወቃል። የዚህም ጠንቅ፡ ምእመናንን ከሥጋ ወደሙ በማራቅ ረገድ፡ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረጉና ለደረሰው ችግር፡ ተጨማሪ ክብደትን ማስከተሉ ሊታበል አይቻልም።

ከላይ በቀረበው የትርጓሜ ጥቅስ፡ ለሥጋ ወደሙ፡ ማድረግ የሚሳነው ነገር እንደሌለ ቢታመንም፡ "አንድ ጊዜ ከተቀበሉት" በኋላ፥ ያውም፡ በሕፃንነት፡ "በኃጢአት ካላሳደፉት በቀር" ለሚለው ኃይለ ቃል በቅቶ ሊገኝ የሚችል ሥጋ ለባሽ፡ ከድንግል ማርያምና ከልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፡ ሌላ ፍጡር፡ ከቶ፡ "ይኖራል!" ብሎ ማሰብ እንኳ ስለሚያዳግት፡ ይህ ኹኔታ፡ በሕዝባዊው አነጋገር፡ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ!" እንደሚባለው፡ በምእመናን ላይ ያለውን ይህንኑ ችግር ያባባሰ ኾኖ ለመኖሩ ግልጽ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚገባው፡ ሌላ ምክንያት ደግሞ አለ፤ ይኸውም፡ ምእመናን፡ ከእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የቃል ኪዳን በረከቷን ለመቀበል፡ ዘወትር በማለዳ በመፋጠን ወደቤተ ክርስቲያን እየኼዱ፡ ባለማስታጐል በሚያዳምጡት፡ በተአምረ ማርያም የንባብ ሥርዓተ ጸሎት ጊዜ፡ በመቅድሙ ውስጥ፡ በግብፃውያን ጳጳሳት የውግዘት ትእዛዝ የጸናው፡ "የታወቀ ምክንያት፥ ኃጢአትና ደዌ ካልከለከለው በቀር፡ በዚች ቀን፡ ተአምሩዋን ሰምቶ፡ የሚቻለው፡ ሥጋውን ደሙን ይቀበል! ሥጋውን ደሙን መቀበል ካልተቻለው፡ ተአምሩዋን ሰምቶ ወደቤቱ ይኺድ! ሥጋውን ደሙን እንደተቀበለ ይኾንለታል፤ 'ይደረግልኛል!' በማለት ቢሰማ!" የሚለው፡ ኃይለ ቃል ነው። የዚህ ቃል ትክክለኛ ትርጓሜ፡ በካህናቱ፡ በሚገባ ተብራርቶ፡ ለምእመናን ባለመነገሩ፡ እያንዳንዱ ምእመን፡ ግብፃውያኑ የጻፉትን፡ የተአምሩዋን የመቅድም ቃል፡ በየራሱ በመተርጐም፡ ሃይማኖታዊ ግዳጁን፡ "እንግዴህ፡ በኃጢአተኛነቴና በሌሎችም ነገሮች ምክንያት፡ ሥጋውን ደሙን መቀበል ስለማልችል፡ ራሴን፡ ተአምሩዋን ብቻ ሰምቼ፡ ወደቤቴ ብኼድ፡ ሥጋውን ደሙን እንደተቀበልኩ ስለሚያስቆጥረኝ፡ ለእኔ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡ ይኸው ይበቃኛል!" ብሎ ወደቤቱ ይመለሳል። ይህ፡ የግብፃውያን መመሪያ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ መለኮታዊ የወንጌል ቃል በልጦ፡ የኢትዮጵያን ምእመናን፡ ከሥጋ [illegible] ወደሙ ለማራቅ፡ አንዱ ዋነኛ ምክንያት ኾኖ መኖሩ አያጠያይቅም።

እንግዴህ፡ ይህ ኹሉ ምክንያት ባስገኘው ውጤት፡ ዲያብሎስ በደስታ ሲፈነጭ፥ ራሱን፡ እንደፋሲካ በግ፡ በመስቀል ላይ ሠውቶ፡ ሥጋውን በመቁረስና ደሙን በማፍሰስ፡ "በእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከእናቴና ከእኔ ጋር፡ አብራችሁን ለዘለዓለም ትኖሩ ዘንድ፡ ሰውነታችሁን በንስሓ እያጸዳችሁ፡ ሥጋዬን ብሉ! ደሜንም ጠጡ!" ያለን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከነእናቱ፡ የቱን ያህል እንደሚያዝን መገመቱ አያዳግትም።